Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ


የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና የኮምዩኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ፍተሻ፤ በአዋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት


በ ወይኒቱ ገ/ህይወት



ጥቅምት 2016 ዓ. ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ፍተሻ፤ በአዋሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት


**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና የኮምዩኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት**

**ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**


የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአርት ማስተር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ


በ ወይኒቱ ገ/ህይወት

አማካሪ

አማኑኤል አለማየሁ ( ዶ/ር )



ጥቅምት 2016 ዓ. ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የማፅደቂያ ወረቀት

**"በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ፍተሻ፤ በአዋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት"** በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና የኮምዩኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የማስትርስ ዲግሪ ማሟያ በወይኒቱ ገ/ብረሕይወት የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈታኞች ቦርድ አባላት

አማካሪ ------------------------------------- ፊርማ -------------------- ቀን ------------------

የውጪ ፈታኝ ------------------------------- ፊርማ -------------------- ቀን ------------------

የውስጥ ፈታኝ ------------------------------ ፊርማ -------------------- ቀን ------------------

# ማረጋገጫ

**"በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ፍተሻ፤ በአዋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተተኳሪነት"** በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና የኮምዩኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የተገለገልኩባቸውን መጻሕፍት እና የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ሥራዎች በዋቢ መጻሕፍት ስር መጥቀሴን እና ስራውም የራሴ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ ፡፡

ፊርማ----------------------------

ስም. ወይኒቱ ገ/ህይወት

ሐምሌ 2015 ዓ. ም.

# ምስጋና

በመጀመሪያ ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ ለማዘጋጀት የረዳኝን ልዑል እግዚአብሔርንና እናቱን ድንግል ማርያምን አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠልም ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ትልቁን ድርሻ በመውሰድ የገንዘብ ድጋፍ ያደረገልኝን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን አመሰግናለሁ፡፡ የዚህን ጥናታዊ ጽሑፍ ረቂቁን በማንበብ፣ ሙያዊ እርማት እና እገዛ በመስጠት ውድ ጊዜያቸውን ለሰውልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር አማኑኤል አለማየሁ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የትምህርት ጊዜያቸውን ሰውተው የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላትና ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው ለተባበሩኝ ለአዋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ፤መጠይቁን በማስሞላት ሂደት ለተባበሩኝ ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በጥናቱ ሂደት መረጃዎችን በማጠናቀር፣ ጥናታዊ ጽሑፉን በኮምፒውተር በመጻፍ ለተባበሩኝና ያላሰለሰ ድጋፍ ላደረጉልኝ  ለእህቴ ለመ/ት መርሻ ገ/ህይወት እና ለኢየሩሳሌም አለማየሁ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገፅ**


የማፅደቂያ ወረቀት ........ i
ማረጋገጫ ........ ii
ምስጋና ........ iii
ማውጫ ........ iv
የሠንጠረዥ ማውጫ ........ vii
አጠቃሎ ........ viii
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3 የጥናቱ አላማ ........ 4
1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 4
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 5
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.7. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........ 5
ምዕራፍ ሁለት ........ 6
ክለሳ ድርሳናት ........ 6
2.1 ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነት ........ 6
2.2. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ክፍፍል ገጽታዎች ........ 9
2.2.1. ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ........ 15
2.2.1.1. የትውስታ ብልሃቶች / Memory strategies / ........ 15
2.2.1.2. አዕምሮታዊ ብልሃቶች (Cognitive Strategies) ........ 16
2.2.1.3. አካካሽ ብልሃቶች (Compensation strategies) ........ 16
2.2.2. ኢ- ርቱዕ የመማር ብልሃቶች (Indirect learning strategies) ........ 16
2.2.2.1. ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች (Metacognitive strategies):- ........ 17
2.2.2.2. ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች (Affective strategies) ........ 17
2.2.2.3. ማህበራዊ ብልሃቶች (Social Strategies) ........ 18
2.3. ቃላትን የመማር ብልሃቶች ........ 18
2.4. በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ሚና ........ 20
2.5. ቃላትን የመማር ብልሃቶች አከፋፈል ........ 23

2.5.1. ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ..... 24
2.5.1.1. የትውስታ ብልሃቶች ..... 24
2.5.1.2. አዕምሮታዊ ብልሃቶች ..... 25
2.5.1.3. አካካሽ ብልሃቶች ፡- ..... 26
2.5.2. ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች ..... 26
2.5.2.1. ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ..... 27
2.5.2.2. ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ..... 27
2.5.2.3. ማህበራዊ ብልሃቶች ..... 28
ምዕራፍ ሦሥት ..... 31
የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ ..... 31
3.1 የጥናቱ ንድፍ ..... 31
3.2. የጥናቱ ዓይነት ..... 31
3.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች ..... 31
3.4. የጥናቱ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ..... 31
3.3 የመረጃ ምንጮች ..... 32
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎችን ..... 32
3.4.1. የጽሁፍ መጠይቅ ..... 32
3.4.2. ቃለ መጠይቅ ..... 33
3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 33
ምዕራፍ  አራት ..... 34
የመረጃ  ትንተናና ውጤት ማብራሪያ ..... 34
4.1. የርቱዕ የመማር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 34
4. 1. 1. የትውስታ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 34
4.1.2. የአዕምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 41
4.1.3. የአካካሽ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 48
4.2 የኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 50
4.2.1 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 50
4.2.2. የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 55
4.2.3 የማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት ..... 58
ምዕራፍ አምስት ..... 62
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና አስተያየት ..... 62
5.1. ማጠቃለያ ..... 62
5.2. መደምደሚያ ..... 65
5.3. አስተያየት ..... 66

ሙዳየ ቃላት ........................................................................................................ 68
ዋቢ ጽሁፎች........................................................................................................ 69
አባሪ 1 ........................................................................................................ 71
አባሪ 2 ........................................................................................................ 78
አባሪ 3 ........................................................................................................ 79
አባሪ 4 ........................................................................................................ 79

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ርዕስ ገፅ

ሠንጠረዥ 4.1 የትውስታ ብልሀቶች ጥቅል መረጃ ………………………………………… 31

ሠንጠረዥ 4.2 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ……………………………………… 37

ሠንጠረዥ 4.3 የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ …………………………………........... 44

ሠንጠረዥ 4.4 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ……………………………….. 46

ሠንጠረዥ 4.5 የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ጥቅል መረጃ …………………………….. 50

ሠንጠረዥ 4.6 የማህበራዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ ……………………………………….. 53

# አጠቃሎ

ጥናቱ  በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች  የአማርኛን  ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ቃላትን የመማር ብልሃቶች የሚፈትሽ ነው፡፡ በአምቦ ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከሚሰጥባቸው አምስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል  በቀላል የእጣ ናሙና ዘዴ በተመረጠው የአዋሮ 2ኛ ደረጃ  ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል የሚማሩ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ 60 ተማሪዎችን በተመጣጣኝ  ናሙና ዘዴ በመውሰድ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ያካሄደ ገላጭ ጥናት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የሁለተኛን ቋንቋ ቃላት በቀላሉ ለመማር በተለያየ መንገድ እገዛ በሚያደርጉ ( የትውስታ ፣ አእምሮታዊ፣ አካካሽ ልዕለ አዕምሮታዊ ፣ ስሜት ነኪ ቁጥጥር እና ማህበራዊ ) ብልሃቶች ስር በተካተቱ ዝርዝር ብልሃቶች ላይ በማተኮር  ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የተጠቀሱትን የመማር ብልሃቶች ምን ያህል እንደሚገለገሉባቸው ለመፈተሽ ተሞክሯል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ ሲሆን ፣ በጽሑፍ አማካይነት የተገኙ መረጃዎችም በስድስት ንዑሳን የመማር ብልሃቶች ስር በሰንጠረዥ ተደራጅተው ፣ በቁጥርና በመቶኛ ተጠቃልለው እንዲታዩ በማድረግ በቃለ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ጋር እየተደጋገፉ ተተንትነዋል፡፡ በሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤት መሰረትም፣ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ የሁለተኛን ቋንቋ ቃላት በቀላሉ ለመማር በተለያየ መንገድ ዕገዛ የሚያደርጉ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ሆኖ አልተገኘም ፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላት በአእምሮአቸው መዝግበው የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዟቸውን የትውስታ ብልሃቶች ፣በትምህርቱ ሂደት የሚሰማቸውን የፍርሃት፣ የጭንቀት ፣ አሉታዊ አመለካከትና ዝንባሌ ለመቆጣጠር የሚረዷቸውን ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችን፣ የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተረዳዱ ፣ መምህሮቻቸውን እየጠየቁ የመማር ፣ ማህበራዊ ብልሃቶችንና ለቃላት ትምህርት የክንውን ዕቅድ በማዘጋጀት፣ ዓላማና ግብ በመንደፍ ፣ ስህተታቸውን በራሳቸው በመለየትና በመገምገም እንዲማሩ የሚያግዟቸውን ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉባቸው የተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት ያመለክታል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሁለተኛ ቋንቋ መማር በዋናነት የቋንቋውን ቃላት የመማር ጉዳይ ነው፡፡ Wallace (1982:9) ይህንን አሰመልክቶ እንደሚገልጹት፤ ሁለተኛን ቋንቋ ለመማር በቅድሚያ ለቃላት ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ እንደ እርሳቸው አባባል በሌላ ቋንቋ ራሳችንን ለመግለጽ ፈልገን መግለጫ ቃላት ማጣት በንግግር ሂደት የሚያሳድረው የፍርሃት ስሜት ነው፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በንግግር እና በጽሁፍ ለሌሎች ለማስተላለፍም ሆነ ከሌላ አቅጣጫ የሚሰነዘሩ ሀሳቦችን አዳምጠውና አንብበው ለመረዳት ይችሉ ዘንድ የቃላት ዕውቀት ሊኖራቸው እንደሚገባ
ይታመናል፡፡ ይህንን አስመልክቶ Mecarthy (1990:viii) ፤ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር በጥሩ ሁኔታ የመማሩ ጉዳይ ምንም ማለት አይደለም፤ የንግግር ድምጾችን በሚገባ መናገሩም የማይፈይደው ነገር የለም፤ ዋናውና ትልቁ ቁም ነገር ትርጉም ያለውተግባቦት ለማካሄድ የቃላት ዕውቀት መኖሩ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋርም በተያያዘ Wilkins(1972) እንዳብራሩት፣ እንደ እውነቱ ከሆነ ያለ ሰዋስው ዕውቀት በትንሹም ቢሆን ሃሳብን መግለጽ ይቻላል፤ ያለ ቃላት ዕውቀት ግን ምንም ነገር መግለጽ አይቻልም፡፡ የቃላት እውቀት የንባብ አላማዎችን ለማሳካት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ Tonjes (1991፣ 143) እንደሚገልጹት፤ በቃላት ዕውቀትና በጽሁፍ ተነባቢነት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የቃላት ኃይል በአንብቦ መረዳት ፣ በአንብቦ መዝናናትና በመማር ስኬታማነት ለይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል፤ ቃላት አንድን ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት ወይንም ለማደናቀፍ የቆሙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በቃላት እውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ጥብቅ ቁርኝት መኖሩ ማንንም ሊያስደንቅ አይገባም፤ እውነቱን ለመናገር አንድ አንባቢ በርካታ እንግዳ ቃላት ያሉበትን ጽሁፍ አንብቦ እንዴት መረዳት እንደሚችል መገመት ያስቸግራል፡፡

እንደ Atikins (1995፣199) አገላለጽ ብዙዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ የመጠቀም ሰፊ ዕድል የላቸውም፡፡ በቋንቋው የሚጠቀሙበት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚማሩበት ወቅት ላይ የተወሰነ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ተማሪዎቹ ቋንቋውን ለተለያዩ ጉዳዮቻቸው ሲጠቀሙ በጣም ይቸገራሉ፡፡ በዚህም በጣም ውስን ከሆነ አጋጣሚ

ተማሪዎች የቋ ንቋ ትምህርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ በራሳቸው ጥረት ቋንቋውን መማራቸው ወሳኝነት ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በተለያዩ መንገዶች ራሳቸውን ለመርዳት መነሳሳት አለባቸው፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ከሚያግዟቸው በርካታ ነገሮች መካከል ቋንቋን የመመር ብልሃቶች፤ በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በብቃት መጠቀም ነው፡፡ ይህንን አስመልክተው oxford እና scarcella (1994፡ 236) እንደሚገልጹት ፣ የተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃት፣ ዕውቀትና ልምድ እየዳበረ ሲሄድ ከመምህሩ ቁጥጥር ወይም ጥገኝነት ተላቀው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ቃላትን ለመማር ያግዛቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Rubin (1987፡15)፣ ሁሉም ሁኔታዎች እኩል ቢሆኑም ጥቂት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ከሌሎች ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የተማሪዎቹ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም ልዩነት ሊሆን ይችላል፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጭ ያለ መምህራቸው እገዛ በራሳቸው ጥረት ለመስራትና ራሳቸውን በራሳቸው ለመርዳት ያስችላቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ተግባቦታዊና ተማሪ - መር የትምህርት አቀራረብ ተማሪው ለቃላት ዕውቀቱ መዳበር የድርሻውን እንዴት ማበርከት አለበት? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡ በእርግጥ በትምህርቱ ሂደት የሚማረው አካል ቀደሚውን ሚና ካልተጫወተ የቃላት ዕውቀቱ ሊዳብር አይችልም፡፡ የተማሪው የቃላት ዕውቀት ማደግ የሚችለው የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ተዋናይ በመሆን በንቃት ሲሳተፍ ብቻ ነው፡፡ የዚህ የተማሪው ንቁ ተሳትፎ ማድረግም ጠቀሜታው፤ ለትምህርቱ ኃላፊነት የመቀበል ልምድን እንዲያጎለብትና፤ ሥራውን በራሱ እየተቆጣጠረ የቃላት ዕውቀቱን ከዕለት ወደዕለት እንዲያዳብር ማድረግ ነው፡፡

(Garins እና Redman 1986: 76-77)፡፡ ሁለተኛ ቋንቋን መማር በዋናነት የቋንቋውን ቃላት የመማር ጉዳይ ነው፡፡ በተተኳሪው ቋንቋ በብቃት ለመገልገልም ሆነ ሌሎች የቋንቋውን ገጽታዎች ለመማር የቃላት ዕውቀት መዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይሁን እንጂ (oxford እና scarcella 1994) እንደገለጹት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ እንደማይበረተቱ፤

በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ መማር - ማስተማር ሂደት ውስጥ ላለፉት ሁለት አስርት አመታት የቃላት ትምህርት ትኩረት እንዳልተሰጠውና ተዘንግቶ እንደነበረ ይገልፃሉ፡፡

ልማዳዊው ቃላትን የመማር ማስተማር ሂደት ለትችት ከዳረጋቸው ምክንያቶች አንዱ የተማሪው ንቁ ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ አለማስገባቱ ነው፡፡ የትችቱም ዋና ነጥብ የትምህርቱ አቀራርብ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት ዕውቀታቸውንም ሆነ ሌሎች ክሂሎችን እንዲያዳብሩ ከማበረታታት ይልቅ መምህራን በሚያቀርቡላቸው ቃላት ላይ እንዲወሰኑ እና በመምህሮቻቸው ጥገኛ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ነው (oxford እና scarcella 1994)፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ሃሳባቸውን በንግግርም ሆነ በጸሁፍ ሲገልጹ ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች መካከል አንዱ በቂ የቃላት ዕውቀት አለመኖር ነው(wallce 1982)፡፡ የዚህ ጥናት አጥኚም በመምህርነት ሙያ በቆየችባችው አመታት ባካበተችው ልምድ መሰረት ይህ ችግር አማርኛን በሁልተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ፣ በተለይም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችም ችግር ነው የሚል እምነት አላት፡፡ ተማሪዎቹ አማርኛን በአብዛኛው የሚጠቀሙበት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው ፡፡ ወደ ትምህርት ሲመጡ እና ሲመለሱ፣ በቤታቸው እና በአካባቢያቸው የሚጠቀሙት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመሆኑ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት የመለማመድ ሰፊ ዕድል አይኖራቸውም ፡፡ ከዚ በተጨማሪ ተማሪዎች እራሳቸው የቃላትን አስፈላጊነት ካለማወቅ የተነሳ ለቃላት ትምህርት ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በብቃት አለመጠቀም ለተማሪዎች የቃላት ዕውቀት ማነስ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡ ጥናቱ ከላይ የተጠቀሱትን አነሳሽ ምክንያቶች መሠረት በማድረግ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ የአዋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን ብልሃቶች ይፈትሻል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አጥኚ በመምህርነት ሙያ በቆየችባቸው ዓመታት ባካበተችው ልምድ መሠረት ይህ ችግር አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ፣ በተለይም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችም ችግር ነው የሚል እምነት አላት፡፡ ተማሪዎቹ አማርኛን በአብዛኛው የሚጠቀሙበት በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው፡፡ ወደ

ትምህርት ቤት ሲመጡና ሲመለሱ ፣ በቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚጠቀሙት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመሆኑ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት የመለማመድ ሰፊ ዕድል አይኖራቸውም። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎቹ ራሳቸው የቃላትን አስፈላጊነት ካለማወቅ የተነሳ ለቃላት ትምህርት ተገቢውን ትኩረት አለመስጠትና በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶችን በብቃት አለመጠቀም ለተማሪዎቹ የቃላት ዕውቀት ማነስ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህም መሠረት አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ተነሳስታለች።

ጥናቱ ከላይ የተጠቀሱትን አነሳሽምክንያቶች መሠረት በማድረግ በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ በአዋሮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን ብልሃቶች ይፈትሻል።

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ በአዋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸውን ብልሃቶች መፈተሽ ነው። በመሆኑም ጥናቱ ይህንን ዋና አላማ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

1. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላት የመማር ብልሃቶችን በብቃት በመገልገል ላይ የተመሰረተ መሆኑን አለመሆኑን መፈተሽ ፣
2. ቃላትን የመማር ብልሃቶችን አስመልክቶ ካሉት የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መካከል በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የትኞቹን ብልሃቶች እንደሚገለገሉ መለየት።

## 1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን የጥናቱ ጥያቄዎችን ይመልሳል።

1. በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላት የመማር ብልሃቶችን በብቃት በመገልገል ላይ የተመሰረተ መሆኑን አለመሆኑን በምን ይፈተሻል?
2. ቃላትን የመማር ብልሃቶችን አስመልክቶ ካሉት የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መካከል በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል

ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የትኞቹን ብልሃቶች እንደሚገለገሉ በምን ይለያል?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች ለመፈተሽ የሚሞክር ሲሆን ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል ፤

- ✓ የሁለተኛ ቋንቋ ቃላትን በመማር ሂደት አጋዥ የሆኑ ቃላትን የመማር ብልሃቶች እንዲዘወተሩ ሐሳብ /ጥቆማ/ ይሰጣል ፤ለቋንቋ መምህሮቻቸው ጥገኛ ከመሆን ይልቅ የራሳቸውን ቃላትን የመማር መንገድ ተከትለው ለውጤት መድረስ እንዲችሉ አስተዋጽኦ ያበረክታል፤
- ✓ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን ቃላትን የመማሪያ ብልሃቶች ለይቶ ያሳያል፤
- ✓ ለወደፊቱ በቃላት መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ዙሪያ ጥናት የሚያደርጉ ተመራማሪዎችም ካሉ ይህ ጥናት እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ ካሉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ካለው የጊዜ ጥበት እና የገንዘብ አቅም ውስንነት የተነሳ በአዋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም. በዘጠነኛ ክፍል በሚማሩ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ በፈቱ ተማሪዎች ላይ በመወሰን ተማሪዎቹ የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸውን ቃላትን የመማር ብልሃቶች ብቻ መፈተሽ ነው፡፡

## 1.7. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ ውስጥ በሚካሄድበት ወቅት በአካባቢው የጸጥታ መታወክ ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ደግሞ የክፍለ ጊዜ መጣበብ የመሳሰሉት ችግሮች ያጋጠሙ ቢሆንም ፤ አጥኚዋ ለችግሩ መፍትሔ ይሆናሉ ያለቻቸውን መንገዶች ለምሳሌ የጸጥታው ሁኔታ ወቅታዊ ስለሆነ ወቅቱን በመከተልና ለክፍለ ጊዜው መጣበብ ደግሞ ከፈረቃቸው ውጭ እንዲመጡና መጠይቆቹን እንዲሞሉ በማድረግ ጥናቱን አካሂዳለች፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነት

በርካታ ምሁራን እንደሚሰጡት ብያኔ ከሆነ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች የቋንቋ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደታቸው ቋንቋ ነክ ስራዎቸችን ለመስራት የሚጠቀሙባቸው የተወሰኑ ክንዋኔዎች፣ ልምዶች ወይም ስልቶች ሲሆኑ፣ በቋንቋው ትምህርት ያገኟቸውን አዳዲስ ሃሳቦች ወደ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ ትውስታ ለማስገባት እና ባስፈለገ ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም የሚያግዟቸው ልዩ ልዩ ስልቶች(መንገዶች) ናቸው፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን አስፈላጊነት በተመለከተ ብያኔ ከሰጡት ምሁራን መካከል የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

O'malley  እና Chamot (1990: 20) እንደገለጹት ፣ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በእያንዳንዱ ግለሰብ አዕምሮ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የአሰራር ባህሪያት ናቸው፡፡ Stem (1983፣ 405) እንደሚያብራሩት ፣ ቋንቋን የመማር ብልሃት የሚለው እሳቤ በሁሉም ምሁራን ዘንድ ወጥ በሆነ መንገድ ሲገለጽ እና በአገልግሎት ላይ ሲውል አይታይም፡፡ ነገር ግን ቋንቋን የመማር ብልሃት በቋንቋ ተማሪዎች በጥቅም ላይ የሚውሉ አጠቃላይ ዝንባሌዎችን ወይንም ሁሉንም ባህሪያት የሚያካትት የተማሪው የአሰራር ቴክኒክ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Wharton(2000 ፣204) እና Oxford(1989: 235) ይህንን ጉዳይ አስመልክተው ሲገልጹ ደግሞ ፣ የመማር ብልሃቶች በተማሪዎች የሚከናወኑ እና መልመድን፣ ዕውቀት ማጠራቀምን ፣ ሃሳብብ አስታውሶ መጠቀምን ፣የሚያፋጥኑ የአሰራር ባህሪያት ተግባራዊ ደረጃዎች ወይም አካሄዳዊ ቴክኒኮች ናቸው በማለት ይገልጹታል፡፡ እነዚህ እንግዲህ የቋንቋ ተማሪው እነዚህን ባህርያት እና ትግበራዎች በመገልገል  የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት የተሳካ፣ ራስ አገዝ ወይም ራስ መር እና አስደሳች በሆነ መንገድ እንዲወጣው የሚያስችሉት መሳሪያዎች  ናቸው፡፡

Tudor (1996: 38) ፣ Oxford እና Ehman (1995: 362) እንደሚገልጹት ፣ቋንቋን የመማር ብልሃቶች የመማር ዓላማን መሰረት ባደረገ መልኩ ተማሪዎች ተተኳሪውን ቋንቋ የሚማሩበትን ሂደት ለማሻሻል እና በቋንቋው ላይ ያላቸውን እውቀት ለማዳበር በሚያደርጉት ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ናቸው፡፡ ብዙ

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ፣ እነዚህን ብልሃቶች በአይነት እና በተደጋጋሚ መጠቀም ከተማሪዎች የቋንቋ ብቃት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡

Cole እና Chan (1994: 212) ፣ Stem (1983: 414) ፣Richards እና Lockhart (1996:63) የሰጡትን ብያኔ ጠቅለል አድርገን ስንመለከተው የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች የሚያካሂዱትን ትምህርት በብዙ አቅጣጫ በመመልከት በራሳቸው ምርጫ እና በሚቀላቸው መንገድ እንዲማሩ የሚረዷቸው በተለይ ደግሞ መምህሮቻቸውን ሁልጊዜ ሊያገኟቸው ስለማይችሉ ማንኛውንም ትምህርታዊ ተግባር በራሳቸው ኃይል እየሰሩ እንዲማሩ የሚያግዟቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ አንድ ትምህርታዊ ክንውን ሲያጋጥሟቸው (ምንባብን አንብበው እንዲረዱ ፣ንግግርን አዳምጠው እንዲገነዘቡ፣ የአንድን ምንባብ ጭምቅ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ፣በምንባቦች ውስጥ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ እንዲሰጡ ወዘተ. ቢደረጉ) የተለያየ አይነት የአሰራር አካሄዶችን ሊከተሉ ይችላሉ፡፡ ይህን የአሰራር አካሄድም የተማሪዎች የመማር ብልሃት ብለን ልንበይነው እንችላለን፡፡

Weden እና Rubin (1987:6) የተማሪዎች ቋንቋን የመማር ብልሃቶች የሚያመለክቱት ፣ የቋንቋ ተማሪው በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርቱ ተሳትፎ ወቅት ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የመማር ባህሪዎችን ነው፡፡ እነዚህን ቋንቋን የመማር ባህሪዎችንም የመማር ብልሃቶች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን፡፡ እነዚህ የመማር ብልሃቶች ተማሪው የራሱን ኃይል ተጠቅሞ ቋንቋውን በሚማርበት ጊዜ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የሚረዱትን ልዩ ልዩ መንገዶችን ለመከተል ያለውን ብቃት የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሁለተኛ ቋንቋውን ሲማር ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆዎች ምንድን ናቸው? አንድን ሰዋስዋዊ ይዘት ለመማር ቀላሉ መንገድ የቱ ነው? ልዩ ልዩ ቋንቋ ነክ ተግባራትን እንዴት ባለ መንገድ ማከናወን ይሻላል? ወዘተ. የሚሉ ጉዳዮችን የሚወስንበት ዘዴ የመማር ብልሃቶች ሊባሉ ይችላል፡፡ Rubin(1987:19) እንደገለጹት ቋንቋን የመማር ብልሃቶች መረጃዎችን ለማግኘት ለማከማቸት ፣አስታውሶ ለመጠቀም እና ለትምህርቱ ሂደት ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በተማሪዎች የሚተገበሩ ማንኛውም ክንውኖች ፣እርምጃዎች እና እቅዶች ናቸው፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጭ ያለ መምህሩ እገዛ በራሳቸው ጥረት ለመስራት እና ቋንቋን ለመማር ያግዛቸዋል ፡፡

Rubin (1987:88) እንደገለጹት በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ለመሆን የመማር ብልሃቶች ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣሉ፡፡

- በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቋቋም እና የቋንቋ ትምህርት ፈተናዎችን ለማለፍ ያግዛሉ፤
- መማር ራስ-መር እንዲሆን ይረዳሉ፤
- የቋንቋ ችሎታ እና የአጠቃቀም ብቃት እንዲዳብር ያደርጋሉ፤
- በተግባቦት ሂደት የችሎታ ማነስ ቢኖር ተግባቦቱ እንዳይደናቀፍ የማካካሻ ዘዴ ይጠቀማሉ፤
- ቋንቋን በመገልገል ሂደት አብይ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችል ልምምድ ለመፍጠር ያግዛሉ፡፡

Stem (1983: 401-405) ፣O'mally እና Chamot (1990:120)፣ Rubin (1975) እና Chamot (1987) እንደገለጹት ፣ውጤታማ የቋንቋ ተማሪዎች የትምህርታቸውን ሂደት የሚያደናቅፉ ፣ የሚያሳዩትን ለውጥ እና መሻሻል የሚገቱ ችግሮችንና እንቅፋቶችን ለመቋቋምና ለትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በበርካታ ብልሃቶች ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም በቋንቋ ትምህርታቸው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ትኩረት የሚሰጡና ሃላፊነትን የሚቀበሉ ፣ ስራቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩና በመማርያ ክፍል ውስጥም ውጭም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለመማር የሚሹ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥረቶች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ብቻ ሳይሆን ከጥገኝነት ተላቀው ፣በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ ይረዷቸዋል፡፡

Oxford(1990) እንደገለጹት ደግሞ ፣የመማር ብልሃቶች ተማሪው በራሱ ጥረት ቋንቋን የመማር ብቃቱን ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ምክንያቱም መምህሮቻቸውን ሁልጊዜ ማግኘት ስለማይችሉ በተለይም ከመማርያ ክፍል ውጭ በቋንቋው በሚጠቀሙበት ወቅት ያለማንም ዕገዛ በራሳቸው ጥረት ለመጠቀም ያስችላቸዋል፡፡ ቀደም ሲል ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን አስፈላጊነት አስመልክቶ በተለየዩ ምሁራን ከተሰጡት(ከቀረቡት) ብያኔዎች ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ፣የሁለተኛ ቋንቋን ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት በተለያየ መልኩ እገዛ የሚያደርጉ መሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ የተማሪውን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎትን ማዳበር ነው፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ተማሪው የቋንቋ ክሂሎቹን እድገት እና ለውጥ ለማሻሻል

በሚል ዓላማ በትምህርቱ ሂደት በራስ-መር በንቃት ለመሳተፍና ተግባቦታዊ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚወስዷቸው የተወሰኑ እርምጃዎች ወይም የአሰራር ዘዴዎች በመሆናቸው የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሌላው ዓላማ፣ ተማሪው መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ቃላትን ለይቶ በተለያዩ አውዶች ውስጥ እንዲጠቀም ማስቻል ነው፡፡ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኝ ቃል በፊት ለፊት ንግግርም ሆነ በመደበኛ ጽሁፍ ውስጥ አይካተትም፡፡ በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ እንደ ነውር ተቆጥረው በግልጽ በአገልግሎት ላይ የማይውሉ ቃላት በየቋንቋው ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ህብረተሰቡም በእነዚህ ቃላት ምትክ ሌሎች ቃላትን ተክቶ ወይም አለዝቤን ተጠቅሞ በተዘዋዋሪ መንገድ ሀሳቡን ይገልጻል፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ተናጋሪ ህብረተሰብ ባህልና የአኗኗር ስርዓት ዕውቀት ለመጨበጥና በተገቢው መንገድ በቋንቋው ለመጠቀም ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ መሳሪያዎች በመሆናቸው ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡ የተማሪዎችን የስነ-ልሳንና የስነጽሁፍ ዕውቀት ማዳበር የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አንዱ አላማ ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካት ቋንቋን የመማር ብልሃቶች የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ተማሪው የአዲሱን ቋንቋ ዕውቀት ለማዳበር ለማስታወስ፤ ለምሳሌ ከጓደኞቹ ጋር የሀሳብ ልውውጥ በማድረግ መለማመድን ፣ ቃላትን ለማስታወስ በሚያመች መንገድ ማደራጀትን፣ የተለያዩ የስነ- ጽሁፍ ስራዎችን ማንበብን፣ የተማሩትን ቃላት ተጠቅሞ አጭር ድርሰት መጻፍን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸውም ሀሳባቸውን በጽሁፍ መግለጽ ለሚፈልጉ ካሰቡት ግብ የሚያደርሷቸው መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች የቋንቋ ትምህርትን ሂደት ቀላልና ውጤታማ ለማድረግ የሚያግዙ መሳሪያዎች መሆናቸውንና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት የራሳቸው የሆነ ጉልህ ሚና እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡

## 2.2. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ክፍፍል ገጽታዎች

በተለያየ ወቅት ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች አስመልክቶ ተመራማሪዎች በልዩ ልዩ የክፍል ደረጃ ላይ ባሉ የቋንቋ ተማሪዎች እና ከመማሪያ ክፍል ውጭ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ በሚያሳዩት የመማር

ክንዋኔዎች ላይ ምርምር በማድረግ የተለያዩ የመማር ብልሃቶች እንደተገኙ ድርሳናት ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ Mcdanough (1999፡ 2 ) እንደሚገልጹት Tarone(1977) የተባለ ተመራማሪ ሶስት ዓይነት ብልሃቶች እንዳሉ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም Ellis (1994፡530) Tarone (1980፡ 419 ) ን በመጥቀስ እንዲሁ ሦስት ዓይነት አጠቃላይ ብልሃቶች እንዳሉ ያስረዳሉ ፡፡ ሁለቱም ምሁራን ያቀረቧቸው ብልሃቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. **አፍልቆታዊ ብልሃቶች፡-** እነዚህ ብልሃቶች ተቀባይና አፍላቂ ክሂሎችን በመጠቀም ቋንቋውን ለመማር (ለመልመድ) የሚጠቅሙ ናቸው፡፡
2. **ቋንቋ የመማር ብልሃቶች፡-** እነዚህ ብልሃቶች የተተኳሪውን ቋንቋ ስነ-ልሳናዊ እና የማህበራዊ ስነ-ልሳን ብቃቶችን ለማሳደግ የቋንቋ ዕውቀትን ለማስፋፋት የሚረዱ ብልሃቶች ናቸው፡፡
3. **ተግባቦታዊ ብልሃቶች፡-** እነዚህ በመግባባት ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቋቋም የሚረዱ ናቸው፡፡

O' mally እና Chamot (1990 : 137-139 ) በአሜሪካ ውስጥ በሚገኝ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አካባቢ "በጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች" ላይ ጥናት በማካሄድ ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ሶስት አይነት አጠቃላይ ብልሃቶች አሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡ እነሱም ቀጥለው የቀረቡት ናቸው፤

1. **ልዕለ አዕምሮአዊ ብልሃቶች (Meta Cognitive strategies ) ፡-** እንደ ምሁራኑ አባባል ልዕለ አዕምሮአዊ ብልሃቶች ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ነክ ትምህርት በመቆጣጠር ፣ በማቀድና በመገምገም ለቋንቋው ይዘትና ለትምህርቱ ክንውን ሂደት የሚያግዟቸው ስልቶች ናቸው፡፡ የሚከተሉትን በምሳሌነት የቀረቡ ልዕለ አዕምሯዊ ንዑሳን ክፍሎች በዝርዝር እንመለከታለን፤

- **ቀጥተኛ የሆነ ትኩረት መስጠት፡-** ትኩረትን የሚበታትኑና አላስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች አዕምሮን ነጻ በማድረግ የተተኳሪውን ቋንቋ ትምህርት በቀጥታ የመከታታል ብልሃት ነው፤
- **መርጦ ማተኮር፡-** በየትኛውም የቋንቋው ትምህርት ሂደት የሚባለውን ነገር ሁሉ ከመከታተል ይልቅ በራስ ግምገማ ለቋንቋው ትምህርት ( ለመዳ ) ጠቃሚ ናቸው በተባሉ ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት የመስጠት ብልሃት ነው፤
- **ራስን መምራት ፡-** ተማሪዎቹ በራሳቸው መንገድ ተተኳሪውን ቋንቋ ለመልመድ የሚያግዙ ሁኔታዎችን እና አጋጣሚዎችን የሚያመቻቹበትና የመለማመጃ ሁኔታዎቹ ወይም አጋጣሚዎቹ በትክክል መፈጠራቸውን የሚያረጋገጡበት እና

በቋንቋው የመግባባት ብቃታቸውን ማሳደግ አለማሳደጋቸውን ራሳቸውን የሚከታተሉበት ብልሃት ነው፤

- **ችግርን መለየት፡-** በቋንቋ ትምህርት ሂደት ለለመዳው ውጤታማነት የሚያግዘው የትሚህርቱ ዋና አላማ ምን እንደሆነ እና በትምህርቱ ሂደት ለለመዳው እንቅፋት የሆኑ ችግሮች ካሉ ለይቶ በማጣራት ለመፍትሔ የሚዘጋጅበት ብልሃት ነው፤
- ***ማደራጀት፡-*** *ተማሪዎች ወደ ፊት የሚማሩባቸውንና የሚሰሯቸውን ዋና ዋና ሀሳቦችና ይዘቶች የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመፈለግ ቅድመ ዝግጅት የማድረግ ስራ ያከናውናሉ፤*
- ***ራስን መገምገም፡-*** በትምህርቱ ሂደት *ተማሪው የራሱን የለመዳ ሂደት* ከሌሎች ውጤታማ ከሆኑ ለማጆች ጋር በማስተያየት የራሱን ሁኔታ የሚገመገምበት ስልት ነው፤
- ***ራስን መቆጣጠር፡-*** በቋንቋው ትምህርት ሂደት ተማሪዎች የተማሩትን ነገር በትክክል መረዳታቸውን፤ የቋንቋውን ሰዋስው እና ቃላት መረዳቱን፣ የቋንቋውን ንበት በተገቢው መንገድ መጠቀሙን ፣ በቋንቋው አማካይነት በትክክል ማዳመጡን፣ መናገሩን፣ ማንበቡንና መጻፉን ቀደም ሲል ያቀዳቸውን ዕቅዶች በትክክል እየተገበሯቸው መሆኑን… ወዘተ ሁሉ ራሱን በማነቃቃት የሚቆጣጠርበት ብልሃት ነው። ለምሳሌ በቋንቋው የመጠቀም ብቃቱን በቋንቋው አፍልቆ መገልገሉን ፣ የቋንቋ ችሎታውን፣ በትምህርቱ ሂደት የመማር ብልሃት አጠቃቀሙን በተጨማሪም በሁለተኛ ቋንቋው በቃል ደረጃ፣ በሐረግና በዓረፈተ ነገር ደረጃ ብሎም በሀሳብ ደረጃ ያለውን ዕውቀት የመገምገም ብልሃት ነው።

2. **አዕምሮታዊ ብልሃቶች** (Cognitive strategies ):- የተማሪውን የአዕምሮ ስራ ጣልቃ ገብነት የሚጠይቁ ናቸው። ይህም ሲባል ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ወደፊት ሊያገኙት በሚችሉት አዲስ ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን በትምህርቱ ሂደት ላይ መነቃቃት እንዲያሳይ ይረዳቸዋል። በተጨማሪም ተማሪዎቹ አዕምሮአቸውን በመጠቀም ቋንቋን ለመማር የሚረዱ ቁሳቁሶችን ወይም አጠቃላይ ሁኔታዎችን ሀሳባዊ ወይም ነባራዊና ተጨባጭ በሆነ መንገድ የመጠቀም ብልሃቶች ናቸው። የሚከተሉት የእነዚህ ብልሃቶች ንዑሳን ክፍሎች ናቸው፤

- ***ምንጭ መጠቀም፡-*** የቋንቋ ትምህርት ሂደቱን ለማጠናከር የሚጠቅሙ የማጣቀሻ ምንጮችን ( ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችን፣ መዝገበ ቃላትን፣ የተለያዩ

መጽሐፎችን፣ ጥናታዊ ጽሁፎችንና የመገናኛ ብዙሃንን ለሚሳሌ፡- ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን … ወዘተ ) የመገልገል ብልሃት ነው፤

- **መቦደን፡-** ሐረጋትን፣ ቃላትን፣ ስያሜዎችን …ወዘተ ባጠቃላይ በቋንቋ ትምህርታቸው የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች እንደ የጋራ ባህሪያቸውና ፍቻቸው በአንድ ላይ በመቦደን እና በማጥናት ትውስታ ውስጥ የማስገባት ብልሃት ነው፤
- **በማጠቃለል ፡-** በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት በየትኛውም መልክ ፣ በማዳመጥ ወይም በማንበብ የተገኘውን ዕውቀት ወይም ቋንቋ ነክ ጽንሰ ሀሳብ በቃል ወይም በአዕምሮ፣ በጽሁፍ መልክ በማሳጠር ጭምቅ ሀሳብ የማዘጋጀት ብልሃት ነው፤
- **መተርጎም፡-** በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የቀረበውን አዲስ ጽንሰ ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ወይም ደግሞ ጽንሰ ሀሳቡን ለመገንዘብ ሲያቅታቸው ወደ ሚያውቁት ቋንቋ( ብዙ ጊዜ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተርጉሞ የመረዳት ብልሃት ነው፤ )
- **ማስታወሻ መያዝ፡-** በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ቁልፍ ቃላትን ፣ ዋና ዋና ሀሳቦችን ወይም ዝርዝር ጉዳዮችን አስፋፍቶ ወይም አሳጥሮ በቃል ወይም በአዕምሮ፣ በጽሁፍ ወይም በአሃዝ መልክ በማስታወሻ ደብተር በመያዝ የቋንቋ ትምህርቱን ተግባራዊነትና ውጤታማነት ለማገዝ የሚረዳ ብልሃት ነው፤
- **መሸጋገር፡-** በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተገኘውን አዲስ ነገር ( ጽንሰ ሀሳብ ) ለመረዳት ከዚህ በፊት ያካበተውን ስነ ልሳናዊ ዕውቀት የመጠቀምና በእያንዳንዱ ሂደት የሚሰጠውን ቋንቋ ነክ ተግባራት በብቃት ለማከናወን ከዚህ ቀደም ያለውን ክሂላዊ ዕውቀት የመጠቀም ብልሃት ነው፤
- **ምስላ፡-** እንግዳ ቃላትንና ጽንሰ ሀሳቦችን በቀላሉ ለመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር ከሚታወቅ ተጨባጭ ነገር (ምሳሌ፡- ስዕል፣ ዕቃ ) ጋር በማያያዝ አዕምሮአዊ ስዕል የመፍጠር ብልሃት ነው፤
- **አውድን መጠቀም፡-** በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦችን ፍቺ ለመገመት በቋንቋው የሚቀርቡ ምሳሌዎችን፣ ፈሊጦችን፣ ቅኔዎችን ወይም ባጠቃላይ ያልተለመዱ አባባሎችን ፍቺና የአጠቃቀም ስርዓት ለመገመት፣ ቋንቋውን መሠረት በማድረግ ፣ የቀረበን ጽሁፍ አንብቦ ለመረዳት፣ በጽሁፍ ስራው ውስጥ አንባቢው እንዲያሚላው ተቆርጦ ፣ ሳይካተት ወይም ሳይቋጭ የቀረበውን የድምዳሜ ሃሳብ ገምቶ የተሟላ ግንዛቤ ለማሳደር… ወዘተ ሁሉም ጉዳዮች የገቡበትን አውድ የመፈተሽ ብልሃት ነው።

3 **የማህበራዊ ብልሃቶች** ( Social strategies) :- ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ ከአካባቢውና አብረው ከሚኖሩት ማህበረሰብ ጋር በመገናኘት ፣ በመግባባት፣ በመተባበርና በመስራት፣ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን በመጠየቅ ፣ ራሳቸውን በራሳቸው በማበረታታት ቋንቋን የሚማሩበት ብልሃት ነው። በምሳሌነት ለማየት በተማሪዎች የሚተገበሩ የሚከተሉት ናሙና ንዑሳን ክፍሎች ቀርበዋል፤

- ✓ **ማብራሪያ መጠየቅ፡-** የቋንቋ መምህራንን ፣ ወላጅን፣ ጓደኛን፣ ወይም ሌሎች የአካባቢ ግለሰቦችን በተማሩት ቋንቋ ነክ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ፣ በምሳሌ የተደገፈ በቂ ማስረጃ ወይም አጠቃላይ መረጃ ገለጻ እንዲያደርጉላቸው የመጠየቅ ብልሃት ነው፤
- ✓ **ከራስ ጋር መማከር፡-** ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የተሰማውን ስጋትና ጭንቀት በመቀነስ የትኛውንም ስራ በራሱ ኃይል መስራት እንደሚችል እራሱ ለራሱ በመንገር የጠንካራነት ስሜት እንዲሰማው የሚያደርግበት ብልሃት ነው፤
- ✓ **ራስን ማበረታታት፡-** ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ባካሄደ ቁጥር እና ለመዳው ስኬታማ በሆነ መንገድ በተከናወነ ቁጥር ተማሪው ራሱን በመሸለምና በማነቃቃት ለቀጣይ ትምህርቱ ምቹ ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት መንገድ ነው፤
- ✓ **ኅብረት/ መተባበር :-** በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ሀሳብና ልምድ ለመለዋወጥ ፣ የቋንቋ ነክ ስራውን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ፣ ቋንቋ ነክ ስራውን እንዴት እንደሚሰራ ሞዴል ለማግኘት ወይም በስራው ሂደት መጋቤ ምላሽ ለማግኘት ሲባል ከተለያዩ ሰዎች ጋር በህብረት/በመተባበር የመስራት ብልሃት ነው።

በሌላ መልኩ Stem (1983: 411-412 ) እንደገለጹት፤ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው አራት መሠረታዊ የሆኑ የመማር ብልሃቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ✓ **ማህበራዊ የመማር ብልሃት፡-** ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ማህበራዊ የመማር ብልሃትን እንደ ሁኔታው (እንደ አስፈላጊነቱ ) ይገለገላሉ። በመጀመሪያ ደረጃ በቋንቋ ዕውቀታቸው አለመብሰላቸውን ተገንዝበው በጥገኝነት መንፈስ በትምህርቱ ሂደት የሚሳተፉ ሲሆን ለውጥ እያመጡ ሲሄዱ ግን ራሳቸውን ችለው ለመማር ጥረት ያደርጋሉ። ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ከተተኳሪው ቋንቋ ተናጋሪ (ተጠቃሚ) ህብረተሰብ ጋር ተግባቦታዊ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ያደርጋሉ። ብቃት በሌላቸው ሁለተኛ ቋንቋ ለመግባባት ጥረት ማድረጋቸው ችግሮቻቸውን መቋቋሚያ ዘዴ ነው። ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የችሎታ መለኪያ ወይም የብቃት ደረጃ መለኪያ ፈተና ካልገታቸው በስተቀር በሁለተኛ ቋንቋ እንደ

ቋንቋው ተናጋሪ በንቃት ይሳተፋሉ። ይህ ደግሞ የቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ይረዳቸዋል።

- ✓ **ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች፡-** የቋንቋ ተማሪዎች ሁለተኛን ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋማሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጭ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በሚፈጥሩት ግንኙነት የቋንቋው ዕውቀት ማነስና በንቃት የመሳተፍ ስሜት ላይ በተወሰነ ደረጃ ጫናና የስሜት መረበሽ ማሳደር የማይቀር ቢሆንም ጥሩ የቋንቋ ተመሪዎች በውስጣቸው የተፈጠረውን የመረበሽ ስሜት ለመቋቋም ይጥራሉ። ራሳቸውን እንደ አንድ የቋንቋ ተማሪ በመቁጠር በተተኳሪው ቋንቋ ፣ በቋንቋ ትምህርቱ፣ በህብረተሰቡና በባህሉ ላይ ቀና አመለካከት ይፈጥራሉ። እነዚህን ባህርያትም አስቀድሞ በመለየት ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃትን በተገቢው መንገድ ወደ መጠቀም ይሄዳሉ።
- ✓ **የክንውን ዕቅድ የማዘጋጀት ብልሃት፡-** ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ከቀረበላቸው ልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ተግባራት አብይና ንዑሳን ግቦች ይመርጣሉ፣ ደረጃቸውንና ዕድገታዊ ቅደም ተከተላቸውን ይገነዘባሉ፣ በትምህርቱም ሂደት በንቃት ይሳተፋሉ፤
- ✓ **አጠቃላይ የቋንቋውን ስርዓት የመማር ብልሃት ፡-** ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች አጠቃላይ የተተኳሪውን ቋንቋ ስርዓት የመማር ብልሃትን የጠቀማሉ። የቋንቋ ትምህርት በተወሰነ ደረጃ ስሜታዊ እና አዕምሮአዊ ስራ በመሆኑ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ለማጥናትና ለመለማመድ ዝግጁዎች ናቸው። ከተተኳሪው ቋንቋ ስርዓትና ህጎች ፣ ከቅርጽና ከትርጉም ግንኙነት ጋር ይጋፈጣሉ። እነዚህን ባህርያት ከመጀመሪያው ቋንቋቸው ጋር በማነጻጸር ወይም በተናጠል ትኩረት ሰጥተው የትምህርቱ ሂደት እስኪፈጸም ድረስ በተደጋጋሚ በመከለስ ሁለተኛ ቋንቋውን ያዳብራሉ፣ ቋንቋውን በመተንተን፣ ተገቢ የመለማመጃ ቴክኒኮችን በመቀየስ ስራቸውን በራሳቸው ይቆጣጠራሉ። ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሁለተኛን ቋንቋ ውስጣዊ መዋቅር በትክክል እስከሚያውቁ ድረስ የመጀመሪያ ቋንቋቸውን መጠቀም እንደሌለባቸው ተረድተው ተተኳሪውን ቋንቋ እንደ ዕውቀትና ክሂል በራሳቸው ለመማር ጥረት የሚያደርጉ ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ጠቃሚዎች ናቸው፤ ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች አራቱን ቋንቋ የመማር ብልሃቶች በተመሳሳይ መልኩ ሁል ጊዜ ይገለገሉባቸዋል ማለት ሳይሆን እንደ ተማሪዎቹ ባህላዊ

ዳራ፣ የዕውቀት ደረጃ፣ ዕድሜና የብስለት ደረጃ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች፣ ለእያንዳንዱ ብልሃት የሚኖራቸው ትኩረት እና የአጠቃቀም ችሎታቸው ይለያያል። በሌላ መልክ ደግሞ Richard እና Lockhart (1996 ፣ 63-65፤ Tudor 1996፣ 202-204 ፤ Oxford 1990 ) ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን ርቱዕ እና ኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች በማለት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል በእያንዳንዳቸውም ስር ሦስት ሦስት ንዑሳን ብልሃቶችንና ሌሎች ዝርዝር የመማር ብልሃቶችን አካትተው እንደሚከተለው አቅርበዋል።

### 2.2.1. ርቱዕ የመማር ብልሃቶች

ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ልዩ ልዩ ተግባራት በቀጥታ ለማከናወን የሚያግዙት መሳሪያዎች ናቸው። Oxford (1990፡ 37 ) እንደገለጹት ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ተማሪው በቀጥታ በታላሚው ቋንቋ እየተጠቀሙ ፣ በትምህርቱ ሂደት በንቃት እየተሳተፈ ቋንቋውን እንዲማር የሚያግዙት ናቸው።

በርቱዕ የመማር ብልሃቶች ስር የትውስታ ብልሃቶች ፣ አዕምሮታዊ ብልሃቶች እና አካካሽ ብልሃቶች የተካተቱ ሲሆን በእያንዳንዳቸውም ስር ተማሪዎች ትምህርቱን ሲማሩ መጠቀም የሚገባቸው ዝርዝር ብልሃቶች ቀርበዋል። እነሱም፡-

#### 2.2.1.1. የትውስታ ብልሃቶች / Memory strategies /

እንደ ምሁራኑ አባባል የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ያገኛቸውን ጽንሰ ሀሳቦች እና የትምህርት ይዘቶች በአዕምሮው መዝግቦ የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው። ተማሪው የትምህርት ይዘቶችን በቀላሉ ለመጨበጥና የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር ቋንቋውን ሲማር የሚከተሉትን ብልሃቶች መጠቀም ይጠበቅበታል። እነሱም፡-

- በትምህርቱ ሂደት የሚያገኛቸውን መረጃዎችና ጽንሰ ሀሳቦች እንደየባህርያቸውና ተጠየቃዊ ዝምድናቸው አኳያ በቡድን በመደራጀት (በመቦደን ) ወይም ቀደም ሲል በአዕምሮ ከተመዘገበ ሌላ ነገር ጋር በማገናኘት አዕምሮአዊ ትስስር መፍጠር ፤
- የተማሩትን ወይም የሰሩትን የትምህርት ይዘቶች ለዘለቄታው ለመጨበጥ በሚል አላማ በተወሰነ ጊዜ ክለሳ ማድረግ ፤
- ልዩ ልዩ ተግባራትን አካላዊ ምላሽ ( Acting out physically ) በመስጠት መፈጸም፤
- አዕምሮአዊ ምስል መፍጠር ( ለምሳሌ በአዕምሮ ውስጥ ሀሳባዊ ምስሎችን በመግለጽ ሊሆን ይችላል።)

### 2.2.1.2. **አዕምሮታዊ ብልሃቶች** (Cognitive Strategies)

አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት በቀጥታ በመስራት ፣ በቋንቋው በመጠቀምና ከራሱም አፍልቆ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው ። ይህም ዕውን ሊሆን የሚችለው ተማሪው ቋንቋውን ሲማር የሚከተሉትን ብልሃቶች የተጠቀመ እንደሆነ ነው ።

- ህጎችንና ቀመሮችን በማውጣት ደጋግሞ ማጥናት ፣ መለማመድና በታላሚው ቋንቋ መገልገል፤
- በቋንቋው የሚተላለፉ መልዕክቶችን በፍጥነት ለመረዳትና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት በዋናው መልዕክት ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት ፤
- ራሱን ከሌሎች ጋር በማወዳደር የቋንቋ አጠቃቀሙን መገምገም፤
- ታላሚውን ቋንቋ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ተርጉሞ ማገናዘብ ፤
- ልዩ ልዩ ማስታወሻዎችን መያዝ ፤
- የተለያዩ አገላለጾችን በደንብ በመመርመር በጥልቀት መረዳት ፤
- የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም የቋንቋ ዕውቀትን ማዳበር ፤

### 2.2.1.3. **አካካሽ ብልሃቶች** (Compensation strategies)

አካካሽ ብልሃቶች የተማሪው የቋንቋ ዕውቀት ብቃት ማነስ ምክንያት የተግባቦት ሂደቱ እንዳይቋረጥና የተግባቦት ሂደቱን እንዲቀጥል የሚያስችሉት ብልሃቶች ናቸው ። እነዚህም ብልሃቶች ፡-

- ❖ ብልህነትን የተላበሰና ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ግምት መጠቀም ፤
- ❖ ስነ-ልሳናዊ ያልሆኑ (non Linguistic) መረጃዎችንና ምልክታዊ ፍንጮችን (ለምሳሌ የእጅ እንቅስቃሴ ፣የግንባር መኮሳተር ፣ጥቅሻ...) በመጠቀም መገመት ፣ወይም መገንዘብ፤
- ❖ አንድን ሀሳብ በንግግርም ወይም በጽሁፍ መግለጽ ሲያዳግት ተመሳሳይ ሃሳብ ባለው በሚታወቅ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ልምምድ ማድረግ፤
- ❖ ሃሳብን በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ሲገለጽ የሚያጋጥሙ ችግሮችን እየለዩ መቅረፍ ፣ ሃሳብና ስሜትን በተለያየ መንገድ እየገለጹ መለማመድ።

### 2.2.2. **ኢ- ርቱዕ የመማር ብልሃቶች** (Indirect learning strategies)

ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት ሲሰራ በቀጥታ የሚገለገልባቸው ሳይሆኑ የትምህርቱን ሂደት እንዴት ማስኬድ እንዳለበት የሚጠቁሙና፣ ሁኔታዎችን የሚያመቻችበትን ልዩ ልዩ መንገዶች የሚያመለክቱ

ብልሃቶች ናቸው፡፡ በ ኢ- ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ስር ሶስት ንዑሳን ብልሃቶች ይካተታሉ፡፡ እነሱም፡-

### 2.2.2.1. **ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች** (Metacognitive strategies):-

ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት በዕቅድ በመምራት ፣በመቆጣጠርና በትምህርቱ ያሳየውን ለውጥ በራሱ በመገምገም እንዲማር የሚያግዙት ብልሃቶች ናቸው፡፡ ተማሪው የሚያከናውናቸው ተግባራትም ፡-

- በትምህርቱ ሂደት የሚያከናውናቸውን ተግባራት አስቀድሞ ማቀድ፤ የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት ቅደም ተከተል ማስያዝ ፤
- የትምህርቱን አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎች ን መንደፍ ፤
- የንግግር አፍልቆት በዘገየ ጊዜ በማዳማጥ ላይ ማተኮር ፤
- ቅድሚያ ለሚሹ (ይበለጥ ጠቃሚ ለሆኑ ) ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት ፤
- ማስታወሻ ስለመያዝና ስለ ቋንቋ ስርዓት መማር ፤
- የሰራውን ስራ እና በትምህርቱ ያሳየውን መሻሻል በራሱ መገምገም

### 2.2.2.2. **ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች** (Affective strategies)

እነዚህ ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት ፣ ዝንባሌና ተነሳሽነት (መነቃቃት) ጋር የሚገናኙ ናቸው ፡፡ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች በቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት ፣ መጥፎ አመለካከት (አስተሳሰብና) ዝንባሌ ለመቆጣጠር የሚገለገልባቸው ብልሃቶች ናቸው ፡፡ እንደ Oxford ( 1990፣ 140 ) አባባል ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የሚያድርባቸውን ስሜት እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው ያውቃሉ ፣ መጥፎ ስሜት ለውጥን ያደናቅፋል ፤ ጥሩ ስሜት ደግሞ የትምህርቱን ሂደት የሚያደናቅፉ ስሜቶችን ለመቆጣጠር የሚያግዙት ብልሃቶችም ፡-

- የተፈጠረውን ችግር እንዳልተፈጠረ መርሳት፤
- ብልህነት በተመላበት መንገድ ድክመትን መቀበል የራስን ጠንካራነት በሙገሳ ቃላት መግለጽ፤ ራስን በማበረታታት በራስ የመተማመን ስሜት ማጎልበት ፤
- በንቃት መከታተል ፤ ችግርን ለሌሎች ማጋራት ፤
- በትምህርቱ ሂደት ለሚፈጠሩ ችግሮች ቀልድ ፈጥሮ ወይም በሌሎች ዘዴዎች ጭንቀትን መቀነስ፡፡

#### 2.2.2.3. ማህበራዊ ብልሃቶች (Social Strategies)

ማህበራዊ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተረዳዱ እንዲሰሩ ፣ ግልጽ ያልሆነላቸውን መምህራቸውንና ሌሎች በታላሚው ቋንቋ ብቃት ያላቸውን ሰዎች እየጠየቁና ግንኙነት እየፈጠሩ የሚማሩበት ብልሃት ነው ፡፡ ተማሪው የሚያከናውናቸው ተግባራትም፡-

- ✓ ከክፍል ጓደኞቹ ጋር ህብረት ፈጥሮ መስራት ፤
- ✓ መምህሩን ወይም ይረዱኛል ብሎ የሚገምታቸውን ወይም በቋንቋው ብቃት ያላቸውን ሰዎች ገለጻ ፣ ማብራሪያ ፣ መጠየቅ ፣ በማስረጃ የተደገፉ የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት አሰራር ፣ ስህተትን ማስተካከያ እርምት ፣ … የሚመለከቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ ፤

## 2.3. ቃላትን የመማር ብልሃቶች

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የቃላት ትምህርት አቀራረብ ከጥንታዊው መምህር- መር ወደ ተማሪ ተኮር አቀራረብ እየተቀየረ መጥቷል ፡፡ ጥንታዊው የቃላት ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት አቀራረብ ከሚተችባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በትምህርቱ ሂደት የተማሪው ንቁ ተሳትፎ ያለውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ አለማስገባቱ ነው ፡፡ ( Oxford እና Scarcella 1994 )፡፡ የዚህ ነጥብ ዋና መሰረተ ሀሳብም የትምህርቱ አቀራረብ ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት የቃላት ዕውቀታቸውንም ሆነ ሌሎች ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ ከማበረታታት ይልቅ መምህሮቻቸው በሚያቀርቡላቸው ላይ እንዲወሰኑ የሚያደርጋቸው መሆኑ ነው፡፡

በአንጻሩም ተግባቦታዊና ተማሪ መር አቀራረብ ተማሪው ለቃላት ዕውቀቱ መዳበር የራሱን ድርሻ እንዴት ማበርከት አለበት? ለሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ ነው ፡፡ የሚማረው አካል በትምህርቱ ሂደት ቀዳሚውን ሚና ካልተጫወተ የቃላት እውቀቱ ሊዳብር አይችልም ፡፡ በሌላ አባባል የተማሪው የቃላት ዕውቀት ማደግ የሚችለው የመማር ማስተማሩ ሂደት ዋና ተዋናይ ሆኖ በንቃት ሲሳተፍ ብቻ ነው ፡፡ በትምህርቱ ሂደት የተማሪው ንቁ ተሳትፎ አንዱ ጠቀሜታው ለትምህርቱ ኃላፊነትን የመቀበል ልምድ እንዲያጎለብት ፣ ራሱን በራሱ እየተቆጣጠረ የቃላት ዕውቀቱን እንዲያዳብር ማበረታታቱ ነው ፡፡ የዚህ አቀራረብ ሌላው ጠቀሜታ ተማሪው ከፍላጎቱና ከትምህርት ልምዱ ጋር የሚጣጣሙ የቃላት ዓይነቶችን መርጦ እንዲያተኩር የሚጋብዘው መሆኑ ነው ( Gairns እና Redman 1986፣ 76-77 )፡፡ ለተማሪው ከጊዜ ወደ ጊዜ የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ከማስተማር ይልቅ በራሱ ጥረት እንግዳ የቃላት

አይነቶችን የሚማርበትን መንገድ እንዲያጎለብት መርዳት ይበልጥ ጠቀሜታ እንዳለው የዘርፉ ምሁራን በአጽንኦት ይገልጻሉ ።

Atikins እና ሌሎች ( 1995 ፣ 199 ) እንደ ገለጹት አብዛኞዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከመማርያ ክፍል ውጭ ለታላሚው ቋንቋ የመጋለጥና በቋንቋው የመጠቀም ዕድል የላቸውም። ለቋንቋው የመጋለጡ ሁኔታ በመማርያ ክፍል ውስጥ በሚማሩት ላይ የተወሰነ ነው። በዚህም የተነሳ ቋንቋውን ለተለያዩ ጉዳዮች ሲጠቀሙ ችግር ይገጥማቸዋል። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች አኳያ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለትምህርታቸው ውጤታማነት የራሳቸው ጥረት የጎላ ድርሻ ይኖረዋል። ስለዚህ ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶችን መሰረት አድርገው በራሳቸው ጥረት ታላሚውን ቋንቋ እንዲማሩ ማበረታታት ሊተኮረበት ይገባል። ይህን ነጥብ አስመልክተው Oxford እና Scarcella (1994 ፣ 236) እንደገለጹት የተማሪው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ዕውቀት እና ልምድ እየዳበረ በሄደ ጊዜ ከመምህሩ ቁጥጥር ወይም ጥገኝነት ተላቆ በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሱ ጥረት ቃላትን ለመማር ያግዘዋል።

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት እውቀት መዳበር ስለሚችልበት ሁኔታ አስመልክቶ የተካሄዱ ጥናቶች ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት ለተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃቶች ነው። ተማሪዎች የቃላት ትምህርታቸውን በብቃት ለመወጣት በርካታ ብልሃቶችን ይጠቀማሉ። ሆኖም ግን አንዳንድ ተማሪዎች ከሌሎች ይበልጥ የመማር ብልሃቶችን በአጥጋቢ ሁኔታ ይጠቀማሉ (Mecarthy 1990 ፣ 124)። ቃላትን የመማር ብልሃቶች በቃላት ትምህርት ውስጥ ጉልህ ሚና እንዳለባቸው የዘርፉ ምሁራን በአጽንኦት ይገልጻሉ። ሆኖም ግን ለብልሃቶቹ የሚሰጡት ግምትና ደረጃ ይለያያል። ለምሳሌ Oxford(1990)፤ Thempson(1987) የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው የተማራቸውን ቃላት በቀላሉ ለመጨበጥና በአዕምሮው መዝግቦ ለማቆየት እንደሚረዱት ሁሉም ይስማሙበታል።

ሌሎች በርካታ ምሁራን ደግሞ የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው የመገመት ብልሃት ለቃላት እውቀት መዳበር የላቀ ድርሻ እንዳለው ያስምሩበታል ( Mecarthy 1990፤ Oxford እና Scarcella 1994፤ Oxford 1990)።

ይህንን ነጥብ አስመልክተው Oxford እና Scarcella (1990: 125) አባባል ደግሞ የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው መገመት ከሌሎች ቃላትን የመማር ብልሃቶች ብዙ

ተማሪዎች እንግዳ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉበት ብልሃት ነው፡፡ Lawson እና Hogben (1996 ፣105) በበኩላቸው እንደገለጹት ደግሞ ከአገባብ መገመት ወደ ቃላት ፍቺ ሁል ጊዜ ላይመራ ይችላል፡፡ እኚሁ ምሁራን አያይዘው እንደጠቀሱት የቃላትን ፍች ከአገባብ መልመድ መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት መቀመጥ አለበት፡፡ ከዚሁ ነጥብ ጋር በተያያዘ Nation እና Coady (1988 ፣ 103) በበኩላቸው የእንግዳ ቃላትን ፍች ከአገባባቸው በመገመት በርካታ ቃላትን ለመማር ይቻላል ማለት አዳጋች እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡

ታላሚውን ቋንቋ በልዩ ልዩ መንገዶች መለማመድ ቃላትን ለመማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ እንደ Oxford(1990፣ 43-44) አባባል ከአዕምሮታዊ ብልሃቶች መካከል የመለማመድ ብልሃት ለቋንቋ ተማሪዎች ከሌሎቹ ይበልጥ ጠቃሚ ነው፡፡የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ቃላት የመጋለጥ እድላቸው በመማርያ ክፍል ውስጥ የተወሰነ ከመሆኑም ባሻገር ጥንታዊው የቃላት ትምህርት አቀራረብም ተማሪው የመማር ብልሃቶችን በመጠቀም ለቃላት ዕውቀቱ መዳበር የድርሻውን እንዲያበረክትና በራሱ ጥረት እንዲማር የሚያበረታታ በመሆኑ ለተማሪው የቃላት ዕውቀት መዳበር የመማር ማስተማሩ ሂደት አቀራረብ ቃላትን እንዲማር ማበረታታት... እንደሚገባ የዘርፉ ምሁራን ያስምሩበታል፡፡ ይህንን ነጥብ አስመልክተው Oxford እና Scarcella(1994፣ 236) እንደገለጹት ቃላትን የመማር ብልሃቶች ተማሪው ከመምህሩ ጥገኝነት ተላቅቆ በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በራሱ ጥረት ቃላትን እንዲማር የሚረዱት ጠቃሚ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መምህራን ተማሪዎቻቸው መማር የሚፈልጉትን ሁሉንም እንግዳ ቃላት ካለው ጊዜ ፣ከእያንዳንዱ ተማሪ ፍላጎትና የሚማርበት መንገድ መለያየት የተነሳ በብቃት ማስተማር ይችላሉ ማለት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የመምህራን ሚና ተማሪዎቻቸው ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በተለይም ቃላትን የመማር ብላሃቶች ዕውቀትና ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ፣ እያንዳንዱም ተማሪ ይበልጥ የሚስማማውን የመማር ብልሃት በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ እንዲጠቀም መምራትና ማበረታታት የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

## 2.4. በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቃላት ሚና

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለቃላት ተገበውን ትኩረት እንዳልተሰጠ የተለያዩ ምሁራን ይጠቅሳሉ ፡፡ ለምሳሌ፡- Carter እና Mccarthy (1988፡ 1 ) ይህን ነጥብ አስመልክተው እንደገለጹት ተግባራዊ ስነ-ልሳናውያን እና የ ቋንቋ መምህራን ላለፉት

ሁለት አስርት ዓመታት በቃላት ትምህርት ላይ ያተኮረ ጥናት ለማካሄድ ፍላጎት አላሳዩም ። Gairns እና Redman (1986 ፡ 1 ) ይህንኑ ሀሳብ ይጋራሉ ። ምሁራኑ እንደገለጹት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቃላት ትክክለኛ ቦታቸውን አልተሰጣቸውም፤ ይህም ከብዛት አኳያ ሳይሆን ከምርጫ ፣ ከአደረጃጀትና ከአቀራረብ አንጻር ነው ። እንደ ምሁራኑ አባባል የቃላት ትምህርት ብዙውን ጊዜ የሚቀርበው በሌሎች ክሂሎች ውስጥ ነው ። የቃላት ትምህርት ለብቻው ትኩረት ተሰጥቶት አይቀርብም ። Oxford እና Scarcella (1994 ፣ 232 ) በበኩላቸው በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ የቃላት ትምህርት ትኩረት እንዳልተሰጠውና ተዘንግቶ እንደ ነበር ይገልጻሉ ። ነገር ግን ቃላትን መማር በተለይም በሁለተኛ ወይም በውጭ ቋንቋ ትምህርት ቀላል ተግባር እንዳልሆነ ፣ ከሌሎች የቋንቋው ገጽታዎች ይልቅ ፈታኝ ና የመምህሩንም ሆነ የተማሪውን ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ ። ለምሳሌ Rudzka እና Channell ( 1986 ፣ 75-76 ) እንደ ገለጹት ተማሪዎች ሁለተኛ ወይም የውጭ ቋንቋ ሲማሩ የቃላት ትምህርት ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቶት አይቀርብም ፤ በዚህም የተነሳ ለብዙዎቹ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ሂደት ለሚገጥማቸው ችግር ምንጩ ቃላትን የመማር ችግር ዋነኛው ነው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የምሁራን ሀሳቦች ቃላትን መማር ቀላል ተግባር እንዳልሆነ የሚያመለክትና በተለይም በሁለተኛ ወይም በውጭ ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ለቃላት ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለበት የሚያስገነዝቡ ናቸው ። በሌላ መልኩ Channel (1988 ፣ 83 ) ከቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለቃላት ትምህርት ተገቢውን ትኩረት እየሰጠ መጥቷል ። ቃላት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከመዘንጋት ወደ ጥናትና ምርምር መስክነት ተለውጠዋል ። በዚህም የተነሳ በአሁኑ ወቅት የሁለተኛ ቋንቋ ቃላት ለመዳ ትውረቶች ና የማስተማሪያ ቴክኒኮች መንጭተዋል። በመምህራንና በተማሪዎች ዘንድም ቋንቋን ለመማር የቃላት እውቀት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው እየታወቀ መጥቷል ። በማለት ገልጸዋል ።
ሁለተኛን ቋንቋን ለመማር በቀዳሚነት ለቃላት ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ምሁራኑ ያስረዳሉ ። ለምሳሌ ፡- Wallace (1982 ፣ 9 ) እንደ ገለጹት ሁለተኛን ቋንቋ መማር በዋናነት የቋንቋውን ቃላት የመማር ጉዳይ ነው ። እንደ እርሳቸው አባባል በሌላ ቋንቋ ራሳችንን ለመግለጽ ፈልገን መግለጫ ቃላት ማጣት በንግግር ሂደት የሚያሳድረው የፍርሃት ስሜት ከፍተኛ ነው ።

ቋንቋን ለመማር ቃላት መሰረታዊ ነገሮች መሆናቸውን Wilkins (1972) ይጠቅሳሉ፡፡ ቋንቋን በመማር ሂደት ውስጥ ቃላት ያላቸውን ጠቀሜታ አስመልክተው እንደገለጹት እንደ እውነቱ ከሆነ ያለ ሰዋስው ዕውቀት በጥቂቱም ቢሆን ሀሳብን መግለጽ ይቻላል ፣ ያለ ቃላት ዕውቀት ግን ምንም መግለጽ አይቻልም ፡፡ ይህም ቋንቋን ለመማር ቃላት ዋነኛ የትምህርቱ መሰረቶች መሆናቸውን ከገለጹት ምሁራን ሀሳብ ጋር ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው ነው ፡፡ ማንኛውም ቋንቋ የቃላት ድምር ውጤት ነው ፡፡ በእያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ የተለያዩ ነባራዊ ነገሮችንና እሳቤዎችን ወክለው የሚገኙትም ቃላት ናቸው ፡፡ ሰዋስዋዊ መዋቅር የቋንቋውን አጽም ቢመሰርትም ቃላት ደግሞ ወሳኝ የሆኑትን የቋንቋውን ብልቶች ማለትም ሥጋና ደም ሆነው ህይወት እንዲዘራ ያደርጉታል ፡፡ የቃላት ዕውቀት ደግሞ መደበኛና ኢ- መደበኛ በሆነ መንገድ ሊገኝ ይችላል ኢ- መደበኛ በሆነ መንገድ የሚገኝ የቃላት ዕውቀት ከማህበረሰቡ ጋር በሚኖረው መስተጋብር የሚገኝ ሲሆን መደበኛ በሆነ መንገድ የሚገኝ የቃላት ዕውቀት ደግሞ በመርሃ ትምህርት ውስጥ ተቀርጸው ፣ በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሚያስተምር እና የሚማር አካል ተገናኝተው በሚያካሂዱት የመማር- ማስተማር ሂደት የሚገኝ ዕውቀት ነው ፡፡ በሁለቱም መንገዶች የቃላት ዕውቀት የሚገኝ ቢሆንም መደበኛ በሆነ መንገድ ( በትምህርት ቤት ) የሚማሩት ቃላት ካላቸው መደበኛ አጠቃቀም አንጻር በተሻለ ሁኔታ ሀሳብን ለመግለጽ ያግዛሉ ( Harmer 1991 ፣ 151-153 )፡፡

ሀሳብን በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ለመግለጽ ፣ ከሌላ አቅጣጫ የሚሰነዘሩ ሀሳቦችን አዳምጦ እና አንብቦ ለመረዳት ፣ ባጠቃላይ ለተግባቦታዊ ክንውን መሳካት የቃላት ዕውቀት መኖር ወሳኝ ነው፡፡ MeCarthy ( 1990 - viii ) የቃላት ዕውቀት በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያለውን ጉልህ ሚና አስመልክተው እንደገለጹት ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር በጥሩ ሁኔታ የመማሩ ጉዳይ ምንም ማለት አይደለም፤ የንግግር ድምጾችን በሚገባ በመናገሩ የሚፈይደው ነገር የለም ፤ ትርጉም ያለው ተግባቦት ለማከናወን ዋናውና መሠረታዊው ነገር የቃላት ዕውቀት መኖር ነው፡፡

Mezynski (1983 ፣ 253) በቃላት ዕውቀትና በአንብቦ መረዳት መካከል ያለውን ጥብቅ ግንኙነት አስመልክተው በግልፅ እንዳስቀመጡት በቃላት ዕውቀት እና በአንብቦ መረዳት መካከል ጥብቅ ትስስር መኖር ማንንም ሊያስደንቅ አይገባም፤ ምክንያቱም አንድ አንባቢ የማያውቃቸው በርካታ እንግዳ ቃላት ያሉበትን ጽሁፍ አንብቦ መረዳት ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራልና፡፡ Tonjes (1991፣ 143) በበኩላቸው በቃላት እውቀትና በጽሁፍ

ተነባቢነት መካከል ያለውን ግንኙነት በማብራራት እንደጠቆሙት የቃላት ኃይል በአንብቦ መረዳት እና በትምህርት ስኬት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከተጠቀሱት ነጥቦች አዲስ ቋንቋ ለመማር የቃላት ዕውቀት መዳበር ወሳኝነት እንዳለው እንረዳለን ፡፡ በተለይም ከሌሎች የሁለተኛ /የውጭ/ ቋንቋ ገጽታዎች የቃላት እውቀት መዳበር የተማሪዎች በራስ የመተማመን ስሜት ጎልብቶ ቋንቋውን ለተለያዩ ጉዳዮች እንዲገለገሉ ያነሳሳቸዋል፡፡ ስለዚህ የተማሪውን የቃላት ዕውቀት ለማዳበር የሚደረግ ጥረት፣ የመማር ማስተማር ክንውን ጥናትን መሰረት ያደረገ ፣ ቃላትን የመማር ብልሃቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ አቀራረብ መከተል እንዳለበት ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

## 2.5. ቃላትን የመማር ብልሃቶች አከፋፈል

ቀደም ሲል “ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች አከፋፈል “ በሚል ንዑስ ርዕስ ስር ለመቃኘት እንደተሞከረው ቋንቋን የመማር ብልሃቶች አከፋፈል አንድ ወጥ መንገድ የተከተለ አይደለም፡፡ ምሁራኑ የመማር ብልሃቶችን የከፋፈሏቸው በተለያዩ መንገድ ነው፡፡ Stern (1983 ፣ 411-412) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሚገለገሉባቸውን ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በአራት ጎራ በመክፈል በእያንዳንዳቸው ስር በተማሪዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ Cook (1991፣ 127) ደግሞ Naiman እና ሌሎች (1995)ን በመጥቀስ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የሚያጋሯቸውን ስድስት የመማር ብልሃቶችን ከዝርዝር ማብራርያ ጋር አስቀምጠዋል፡፡ O’mally እና Chamot (1990፣ 137-139) በበኩላቸው በጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ላይ ጥናት በማድረግ ተማሪዎቹ የሚገለገሉባቸውን ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ልዕለ አዕምሮታዊ ፣ አዕምሮታዊ እና ማህበራዊ ስሜት ነኪ ቁጥጥር በማለት በሶስት በመክፈል በእያንዳንዳቸውም ስር ሌሎች ዝርዝሮችን አካተው አቅርበዋል፡፡

ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት መንገዶች በተለየ መንገድ ከከፋፈሉት ምሁራን መካከል Oxford (1990) ተጠቃሽ ናቸው ፡፡ Oxford (1990) ቋንቋን የመማር ብልሃቶችን በሁለት ታላላቅ ጎራዎች (ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ና ኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች) በመክፈል በእያንዳንዱም ስር ሦስት ንዑሳን ብልሃቶችን ከሌሎች በርካታ ዝርዝር ብልሃቶች ጋር በማካተት አቅርበዋል ፡፡ የ oxford (1990) አከፋፈል ከሌሎች ጥናቶች የቀረቡ የመማር ብልሃቶችን አካትቶ የያዘ ፣ ብልሃቶቹንም በጥቅል መረጃዎች እና በምሳሌዎች አስደግፎ የሚያቀርብ ነው ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቃላትን የመማር ብልሃቶችን አተገባበር እንደ አስፈላጊነቱ ምሳሌዎችን በመስጠት

በግልጽ የሚያሳይና የቋንቋ ክሂሎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው ። በመሆኑም ይህ ጥናትም በ Oxford (1990) የቀረበውን አከፋፈል መሰረት ያደረገ ነው ። ቃላትን የመማር ብልሃቶቹም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

## 2.5.1. ርቱዕ የመማር ብልሃቶች

እንደ Oxford (1990 ፣ 37) አባባል ርቱዕ የመማር ብልሃቶች ተማሪው በቀጥታ የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት እየሰራና በትምህርቱ ሂደት እየተሳተፈ ታላሚውን ቋንቋ እንዲማር በቀጥታ እገዛ የሚያደርጉ ናቸው ። ቃላትን ለመማር ተገቢ የሆኑ ርቱዕ ብልሃቶችም የትውስታ ብልሃቶች ፣ አዕምሮታዊ ብልሃቶች እና አካካሽ ብልሃቶች ናቸው።

### 2.5.1.1. የትውስታ ብልሃቶች

ስያሜው እራሱ እንደሚያመለክተው እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ቃላትን በአዕምሮው መዝግቦ ለመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዙት ብልሃቶች ናቸው። እንደ (Oxford 1990 ፣ 39 ) አባባል የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች አንዱ መሰረታዊ ችግር በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት ወይም አገላለጾች በሌላ ጊዜ መርሳት ነው። ይኸውም ተማሪዎቹ ለተለያዩ ጉዳዮች በጣም የሚጠቅሟቸውን ልዩ ለዩ የቃላት ዓይነቶች እና አገላለጾችን አስታውሰው መጠቀም አለመቻል ችግር ያጋጥሟቸዋል ። የትውሰታ ብልሃቶችም የቋንቋ ተማሪዎች ይህንን ችግር በብቃት እንዲቋቋሙ ያግዟቸዋል።

የትውስታ ብልሃት የሚከተሉትን ዝርዝር ብልሃቶች ያካትታል ።

- ***መቦደን*** ፡- ቃላትን ለማጥናት በሚያመች ትርጉም ባለው መንገድ (ለምሳሌ ፡- በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸውን ፣በቃል ክፍላቸው ፍቺ ተመሳሳይነታቸው ወይም ተቃራኒነታቸው ወዘተ ) መሰረት ማደራጀት ፤
- ***ማያያዝ*** ፡- አዲሱን ቃል በአዕምሮ ውስጥ ከተመዘገበ ነገር ጋር ማያያዝ ፣ ትርጉም ባለው መንገድ ግንኙነት በመፍጠር ለትውስታ ማመቻቸት (ለምሳሌ ፡- እንግዳ ቃላትን ከሚገኙበት ገጽ፣ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከተጻፉበት ቦታ ጋር በማያያዝ ትውስታን መፍጠር )፤
- ***እንግዳ ቃላትን በአውድ ውሰጥ ማስገባት*** ፡- እንግዳ ቃላትን ትርጉም በሚሰጡ ቃላዊ እና ጽሁፋዊ አፍልቆት ውሰጥ በማስገባት ፣ቃላቱን በሀሳብ ልውውጥ ውሰጥ በመጠቀምና የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ከቃላቱ ጋር ለተከታታይ ረጅም ጊዜያት መዝለቅ ፤

- **ምስል መፍጠር ፡-** ታላሚዎቹን ቃላት ከተጨባጭ ነገሮች (ቁሳቁሶች ፣ ስሎች ፣ቦታዎች ወዘተ ) ማገናኘት፤
- ***ሥነ ፍቻዊ ካርታ ፡-*** የፍች ግንኙነት ያላቸውን ውስን ቃላት በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ሊያሳይ በሚችል ስዕል ላይ መደርደር (ለምሳሌ፡- ከ"ጸጉር" ጋር የተገናኙ ቃላትን በሰው ጭንቅላት ስዕል ላይ በማደራጀት ግንኙነታቸውን ማሳየት ) ፤
- **በትውስታ ውስጥ ድምጽን መወከል ፡-** የአዲሱን ቃል ድምጽ በማንኛውም ቋንቋ ውስጥ ከሚያውቁት ተመሳሳይ ድምጽ ካለው ቃል ጋር በማያያዝ ታላሚውን ቃል ለመያዝ መሞከር ፤
- **ክለሳ ማካሄድ ፡-** የተማሩትን ቃላት የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር በሚል ዓላማ በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ መከለስ ፤
- **አካላዊ ምላሽ መጠቀም ፡-** የእንግዳ ቃላትን ፍቺ በአካል እንቅስቃሴ ማሳየት ፤

#### 2.5.1.2. አዕምሮታዊ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ተግባራት ላይ በቀጥታ በሚሰራበት ጊዜ የሚገለገልባቸው ብልሃቶች ናቸው ። Rubin (1987፣ 23 ) እንደገለጹት አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማሩ በቀጥታ የሚተገብሯቸው የአሰራር መንገዶች ወይም የሚወስዷቸው እርምጃዎች ወይም ችግር ማቃለያዎች ናቸው ።

ተማሪው በታላሚው ቋንቋ ቃላት ተግባራት ላይ በቀጥታ የሚገለገልባቸው አዕምሮታዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው ።

- ✓ **መደጋገም ፡-** እንግዳ ቃላትን ደጋግሞ መጻፍ ወይም ደጋግሞ ማለት ቃላቱን ለብዙ ጊዜ ማዳመጥ ፣ በአዕምሮ ውስጥ ማመላለስና በታላሚው ቋንቋ የመጠቀም ችሎታ ያላቸውን ሰዎች አጠቃቀም መኮረጅ ፤
- ✓ **ድምጾችን በመደበኛነት መለማመድ ፡-** የንበት ፣ የመጥበቅና መላላት ወዘተ. ልምምድ ማድረግ ፣ በአንድ ዓይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ ፣ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ ማድረግ ፤
- ✓ **ምንጭ መጠቀም ፡-** የታላሚውን ቋንቋ ማጣቀሻ መጻህፍት መጠቀም ፣ ለምሳሌ የእንግዳ ቃላትን ፍቺ መዝገበ ቃላት መመልከት ወይም ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ ፤
- ✓ **መተርጎም ፡-** የታላሚው ቋንቋ ቃል ፍቺ አቻ ፍቺ ወዳለው አፍ መፍቻ ቋንቋ ቃል መተርጎም ፤
- ✓ **መሸጋገር ፡-** ቀደም ሲል ከአንድ ቋንቋ የጨበጡትን የቃላት ዕውቀት የአዲሱን ቋንቋ ቃላት ፍቺ ለመረዳት መጠቀም፤

- ✓ **ድግመ-ቅንብር** :- ቀደም ሲል የተማሩትን ቃላት በአዲስ መንገድ በማቀናበር ትርጉም የሚሰጡ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት ፤
- ✓ **ማስታወሻ መያዝ** :- እንግዳ ቃላትን በአንድ ዓይነት መንገድ (ለምሳሌ በአንድ የቃላት ማስታወሻ ደብተር ) መዝግቦ መያዝ ፤
- ✓ **ትኩረታ ቃል ድምቅታ** :- (high lighting ) :- በንባብ ሂደት የሚያጋጥሙ እንግዳ ቃላትን በማስመር ፣በመክበብ ወይም በማቅለም ፍቻቸውን መፈለግ ፤

#### 2.5.1.3. አካካሽ ብልሃቶች :-

አካካሽ ብልሃቶች ተማሪዎች በቃላት ዕውቀት ማነስ የተነሳ በተግባቦት የሚያጋጠሟቸውን ችግር ለመቋቋም የሚገለገሉባቸው ብልሃቶች ናቸው ። Oxford (1990፣ 47) እንደጠቀሱት እነዚህ ብልሃቶች የሰዋስው ዕውቀት በተለይም የቃላት እውቀት ክምችት እጦትን ለማካካስ የሚያስችሉ ብልሃቶች ናቸው።

ለቃላት ትምህርት ይበልጥ ተገቢነት ያላቸው አካካሽ ብልሃቶች የመገመት (guessing) ወይም የመፈልፈል (inferencing) ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች ተማሪውን ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመጠቀም የእንግዳ ቃላትን ፍቺ ለመገመት የሚያስቸችሉት ናቸው። ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በንባብ ወይም በደመጣ ጊዜ እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሟቸው ብልህነትን የተላበሰ እና ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ግምት ይሰጣሉ ( Naiman እና ሌሎች 1978 ፤ Oxford 1990፤ Mecarthy፣ 1990) ለምሳሌ Mecarthy(1990፣ 125)መፈልፈል (inferencing) ሂደት ነው፤.... ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በንባብ ሂደት ፣ወይም በቴስት ወቅት ፣ወይም በማንኛም ሁኔታ ለሚያጋጥሟቸው ከባድ ቃላት ወደ መዝገበ ቃላት መሮጥ ወይም ሰው መጠየቅ በማይችሉበት ወይም ተገቢ በማይሆንበት ወቅት የሚከተሉት ሂደት ነው በማለት ገልጸዋል።

### 2.5.2. ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች

በዚህ ጎራ የሚመደቡ ብልሃቶች ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ለቃላት እውቀት መዳበር እገዛ የሚያደርጉ ናቸው። ተማሪው ዘውትር የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት በቀጥታ መስራትን የሚጠይቁ አይደሉም። ነገር ግን በተለያዩ መንገዶች ለትምህርታቸው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር የትምህርታቸውን ሂደትለመምራት እና ለማመቻቸት የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው። በ ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች ስር ሶስት ብልሃቶች (ልዕለ አዕምሮታዊ፣ ስሜት ነኪ ቁጥጥር እና ማህበራዊ) ብልሃቶች ይካተታሉ።

#### 2.5.2.1. ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት፣ የትምህርቱን አካሄድና አሰራሩን ለመቆጣጠር ፣ በአጠቃላይ ያሳየውን መሻሻል እና የትምህርቱን ውፀአት(out come) ለመገምገም የሚገለገልባቸው ብልሃቶች ናቸው። በልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች በተማሪው የሚከናወኑ ብላሃትም፡-

- **ትኩረት መስጠት፡-** ለቃላት ትምህርት በአጠቃላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመማር አስቀድሞ መወሰን (ቀጥተኛ ትኩረት) እና በራስ ግምጋሜ ተገቢ የቃላት ተግባራትን መርጦ ትኩረት ለመስጠት መወሰን (መርጦ ማትኮር)
- **ቋንቋን እንዴት መማር እንደሚቻል መገንዘብ፡-** መጻህፍት በማንበብ ወይም ከሰዎች መረጃዎችን በማሰባሰብ ቋንቋን እንዴት መማር እንደሚቻል ጥሩ ግንዛቤ መጨበጥ።
- **ማደራጀት፡-** ለቃላት ትምህርት አመቺ ተፈጥሯዊ አካባቢ ሁኔታ መፍጠር ፤ ለቃላት ትምህርት ወይም ጥናት ፕግራም ማዘጋጀት።
- **ዓላማ እና ግብ ማስቀመጥ፡-** ለቃላት ትምህርት የራስን ግብ ማስቀመጥ፣ ከቃላት ትምህርቱ ምን እንደሚጠብቅ / እንደምትጠብቅ / አስቀድሞ መወሰን ።
- **የቋንቋ ተግባራትን ዓላማ መለየት ፡-** አንድ የቃላት ተግባር በተወሰኑ ሁኔታዎች ውሰጥ ለራስ አላማ ያለውን ተገቢነት መለየት ፣
- **የልምምድ አጋጣሚዎችን ለማገናኘት መጣር ፡-** የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ ተፈጠሯዊ በሆነ መንገድ ለመለማመድ መጠቀም ፣
- **ራስን መቆጣጠር ፡-** ቃላትን በትክክለኛው ወይም በተሳሳተ መንገድ እየተማረ መሆኑን በራስ በመከታተል በቃላት ትምህርት ሂደት የራስን ስህተት በራስ መለየት፤
- **ራስን መገምገም ፡-** የቃላት ትምህርቱን ዉጽኣት በመመርመር ካለፈው የበለጠ ለውጥ /መሻሻል/ ማሳየት አለማሳየቱን ራስን በራስ መገምገም ፤

#### 2.5.2.2. ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች

እነዚህ ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት ፣ ዝንባሌና መነቃቃት ጋር የተያያዙ ናቸው ። ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት እንዲሁም አሉታዊ ዝንባሌ ለመቋቋም (ለመቆጣጠር ) የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው ። Oxford (1990 ፣ 140 ) ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ስለ መማር ስሜታቸው እና ዝንባሌያቸው እንዴት እንደሚቆጣጠሩ የሚያውቁ ናቸው በማለት አያይዘውም መጥፎ

ስሜት ለውጥን ሊገታ ይችላል ፤ ጥሩ ስሜት ደግሞ መማርን ይበልጥ ውጤታማና አስደሳች ሊያደርግ ይችላል በማለት ገልጸዋል፡፡

ለቃላት ትምህርት ውጤታማነት ዕገዛ የሚያደርጉ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ***ራስን ማዝናናት*** ፡- ከቃላት ተግባራት ስራ በፊት የድካም እና የመጫጫን ስሜት ለመቀነስ አካልና አዕምሮን ማዝናናት ፤
- ***አወንታዊ ገለጻ መስጠት*** ፡- ለራስ ችሎታ ጥሩ ግምት እና አወንታዊ መግለጫ መስጠት ፤ በተለይም ከባድ የቃላት ተግባራትን ከመስራት በፊት የራስን ችሎታ ማድነቅ ፤
- ***ኃላፊነትን መቀበል*** ፡- በትምህርቱ ሂደት መሳሳት እንደሚኖር በማመን ከባድ ተገባራትን ስሜትን ተቆጣጥሮ ለማከናወን ኃላፊነትን ተቀብሎ መሳተፍ ( ለምሳሌ በሀሳብ ልውውጥ ሂደት እሳሳታለሁ የሚል ስጋት አስወግዶ ያለ ፍርሃት በንቃት መሳተፍ )፤
- ***ራስን መሸለም*** ፡- በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ ራስን መሸለም ፤ ( ለምሳሌ በቃላት ቴስት ወይም ፈተና ጥሩ ውጤት ሲያመጡ ራስን ማድነቅ )፤
- ***ስሜትን ማጋራት*** ፡- በቃላት ትምህርት ላይ ያደረብንን ስሜት ለሌላ ማካፈል ፣ ( ለምሳሌ በትምህርቱ መደሰት አለመደሰትን ፣ ከክፍል ጓደኞች ወይም ከመምህራን ወይም ከሌሎች ጋር መወያየት፡፡ )

### 2.5.2.3. ማህበራዊ ብልሃቶች

Oxford ( 1990 ) እንደ ገለጹት ማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪው ከክፍል ጓደኞቹ ጋር ማህበራዊ ተራክቦ በማድረግ ቃላትን እንዲማር የሚያግዙት ብልሃቶች ናቸው ፡፡ ቋንቋን ለመማር የሌላ ሰው ተሳትፎ አስፈላጊ እስከ ሆነ ድረስ ተማሪዎችም ለቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት በጋራ ሊሰሩ ይገባል ፡፡ በመሆኑም ማህበራዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተረዳዱ ፣ ግልጽ ያልሆኑላቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን እንግዳ ቃላት ፍቺ መምህሮቻቸውን ወይም ሌሎች ሰዎችን እየጠየቁ እንዲማሩ የሚረዷቸው ናቸው ፡፡ በተማሪዎች የሚተገበሩ ማህበራዊ ብልሃቶችም የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ***ማብራሪያ መጠየቅ*** ፡- የእንግዳ ቃላትን ፍቺ ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ፣ ወይም ስህተትን ማስተካከያ የእርምት ትብብር መጠየቅ፤
- **ከብጤ ጋር መተባበር** ፡- ለጋራ ዓላማ ከብጤ ጋር በቡድን መስራት ፣ የቃላት ዕውቀትን ለማሻሻል ከብጤ ጋር በጋራ መለማመድ፤

- **በቋንቋው የመጠቀም ብቃት ካላቸው ሰዎች ጋር መተባበር፡-** ታላሚውን ቋንቋ በብቃት ከሚናገሩ ሰዎች ጋር ጓደኝነት በመመስረት የቃላት ዕውቀትን ማሻሻል፤
- **ባህላዊ ግንዛቤን ማዳበር ፡-** ስለ ታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል እና አኗኗር ያለንን ግንዛቤ ማሳደግ፣

ከዚህ በላይ በሁለት ዓብይ እና ስድስት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍለው የቀረቡት ቃላትን የመማር ብልሃቶች ለተማሪው የቃላት ትምህርት ውጤታማነት በተለያየ መንገድ እገዛ እንደሚያደረጉ ይታመናል ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ተማሪዎች ብልሃቶቹን በእኩል ደረጃ ይጠቀማሉ ብሎ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ ምናልባትም የብልሃቶቹ አጠቃቀም ተማሪው ስለ ብልሃቶቹ ያለው እውቀት ፣ ባህላዊ ዳራ ፣ የትምህርት ልምዱ፣ ለታላሚው ቋንቋ የመጋለጥ ሁኔታ . . . ሊወሰን ይችላል፡፡

አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮኖዊያዊ . . . ዳራ የተለያየ ነው ፡፡ መናገር፣ ሃሳብ መስጠት ገና በልጅነት ባህል በሆነበት ማህበረሰብ ውሰጥ የሚያድጉ ተማሪዎች እንዳሉ ሁሉ ማዳመጥ እንጂ መናገር በማይፈቀድበት ባህል ውሰጥ የሚያድጉ ይኖራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አብዛኛው ተማሪ ቋንቋውን የሚገለገለው ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ነው፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡና ከትምህርት ቤት ሲወጡ እንዲሁም በቤታቸውና በአካባቢያቸው የሚጠቀሙት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ነው፡፡ በቤተሰብና በአካባቢያቸው በአማርኛ ለመጠቀም ዕድል የሚያገኙት በጣት የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ የእነዚህ ሁኔታዎች አወንታዊነትና አሉታዊነት በተማሪው የቃላት ትምህርት ሂደትና ውጤታማነት ላይ የራሳቸው የሆነ ድርሻ አለቸው፡፡ በመሆኑም በተማሪው የቃላት ትምህርት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን ተቋቁሞ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በራሱ ጥረት እንዲማር ቃላትን የመማር ብልሃቶች ዕውቀትና ልምድ ማዳበር ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡

አማርኛ በትምህርትና በስራ ቋንቋነት ሲያገለግል በመቆየቱና የስነ- ጽሁፍ ቋንቋ በመሆኑ መዝገበ ቃላቱ ሰፊ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በዚህም የተነሳ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህሩ በሚያቀርብላቸው የቃላት ትምህርት ብቻ ዕውቀታቸውን ማሳደግ አዳጋች ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በተለይም ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሠረት አድርገው የአማርኛን ቃላት በራሳቸው ጥረት እንዲማሩ ማበረታታት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተለያዩ ምሁራን ቃላትን የመማር ብልሃቶች ምንነትና አስፈላጊነት አስመለክቶ ከተሰጡት ብያኔዎችና ሃሳቦች ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ከዕለት ወደ ዕለት የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ከማስተማር ይልቅ ተማሪው ለትምህርቱ ውጤታማነት የድርሻውን ማበርከት እንዳለበት ፣ ለዚህም ቃላትን የመማር ብልሃቶች ጉልህ ሚና እንዳላችው የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላት በአዕምሮው መዝግቦ የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠርና በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ ለመጠቀም፣ ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ስርዓት እንግዳ በመሆኑ የተነሳ በትምህርቱ ሂደት የሚያድርበትን የፍርሃት፣ የጭንቀት ፣አሉታዊ ዝንባሌ . . . ተቆጣጥሮ በትምህርቱ ሂደት በንቃት እንዲሳተፍ የሚያነሳሱት ከመሆናቸውም በላይ ትምህርቱን በዕቅድ እና በዓላማ እንዲመራ ፣ ለውጥ ወይም መሻሻል ማሳየት አለማሳየቱን ራሱን በራሱ እንዲገመግም ፣ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለይቶ በራሱ እንዲያቃልል ፣ ለመምህሩ ጥረትና ለትምህርቱ ውጤታማነት የድርሻውን እንዲያበረክት ቃላትን የመማር ብልሃቶች ዋነኛ መሳሪያዎች መሆናቸውን ከምሁራኑ ሀሳብ እንገነዘባለን፡፡

ይህም በመሆኑ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውሰጥ የሌሉ ድምጾችን በታላሚው ቋንቋ ውሰጥ ሲያጋጥሟቸው ደጋግመው በመለማመድ በተናጋሪው ማህበረሰብ ውስጥ ተነውረው አገልግሎት ላይ የማይውሉ ቃላትን ለይተው በተተኪ ቃላት መጠቀም እንዲችሉ ፣ የተለያዩ አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማጥናትና ለማስታወስ በሚያመቻቸው መንገድ አደራጅተው በማስታወሻ ደብተራቸው እንዲይዙ፣ በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሳደግ የድርሻቸውን ማበርከት እንዲችሉ የመማር ማስተማሩ ሂደት ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሠረት ያደረገ መሆን እንዳለበት ጭምር እንረዳለን ፡፡

# ምዕራፍ ሦሥት

# የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምያ ክልል፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ አምስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በመማር ላይ የሚገኙ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበትን መንገድ ከመማር ብልሃቶች አንፃር መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የተማሪዎቹን የመማር ብልሃቶች አጠቃቀም ይመረምራል፡፡

## 3.2. የጥናቱ ዓይነት

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አጥኚዋ ዓይነታዊ (Qualitative) እና ፍትነታዊ (Quantitative) የጥናት ዓይነቶችን ተጠቅማለች፡፡

## 3.3. የጥናቱ ተሳታፊዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ በኦሮምያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ ከሚገኙ አምስት የመንግስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች መካከል የአዋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ ተመረጦ እንዲሳተፍ ተደርጓል፡፡

## 3.4. የጥናቱ ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ በምዕራብ ሸዋ ዞን በአምቦ ከተማ ከሚገኙ አምስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል አጥኚዋ መረጃዎችን በቀላሉ ለማግኘት፣ ከትምህርት ቤቱ ቅርበትና የምታስተምርበት ቦታ በመሆኑ የአዋሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጦ እንዲሳተፍ ተደርጓል፡፡

ከአዋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በተገኘው መረጃ መሰረት ስድስት የ9ኛ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ክፍሎች መካከል በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም 9ኛ "C" እና "E" ክፍሎች ተመርጠው በጥናቱ ውስጥ ታቅፈዋል፡፡ በእነዚህም ክፍሎች ከሚማሩት ተማሪዎች መካከል ተተኳሪዎችን ለመለየት ታልሞ የተዘጋጀ ቅፅ (አባሪ 3 ይመልከቱ) ተማሪዎቹ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ እንዲሞሉ በማድረግ የእያንዳንዱን ተማሪ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚመለከት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ (አባሪ 4 ይመልከቱ)፡፡ ከተሰበሰበው መረጃ ውስጥም አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተማሪዎችን የመለየት ስራ ተከናውኗል

በዚሁም መሰረት ከ9ኛ “C” ወ:20 ፣ ሴ:44፣ ድ:64 ከ9ኛ “E” ወ:22፣ ሴ: 38፣ ድ:60፣ ከሁለቱም ክፍሎች ወ:42፣ ሴ: 82፣ ድ: 124 ተማሪዎች ተለይተው በጥናቱ ውስጥ እንዲታቀፉ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህም ተማሪዎች መካከል አጥኚዋ በጥናቱ ውስጥ 60 ተማሪዎች ለማቀፍ በወሰነችው መሰረት በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም ከ9ኛ “c” ወ:13 ፣ ሴ:17 ፣ ድ:30፣ 9ኛ ”E” ወ 12፣ ሴ 18፣ ድ :30 በአጠቃላይ ወ :25፣ ሴ: 35፣ ድ: 60 ተማሪዎች ከሁለቱም ክፍሎች አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ ተለይተው በቀላል የዕጣ ናሙና ዘዴ ከየክፍሉ የተወሰዱ ተጠኚዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

## 3.3 የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አጥኚዋ ሁለት የመረጃ ምንጮችን ተጠቅማለች፡፡ እነሱም አንደኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ የሚባሉት ናቸው፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች

አንደኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች የሚባሉት ከመስክ መረጃን በመሰብሰብ እና በማጠናከር ረገድ ያግዛሉ ተብለው የሚጠቀሱ ስልቶች በርካታ መሆናቸው ቢታወቅም፣ በቋንቋ ነክ ጥናቶች ተዘውትረው የሚሰራባቸው እና በስፋት የሚታወቁት ዋነኛቹ ስልቶች

1. የጽሁፍ መጠይቅ
2. ቃለ መጠይቅ
3. ምልከታ
4. ልዩ ልዩ ፈተናዎችና የመሳሰሉት ይሆናሉ ( ዓለም፣ 1997፣ 43)፡፡

   ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናት አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ተገቢ ሆኖ የተገኘው የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የጽሁፍ መጠይቅ በዋናነት፣ ቃለ መጠይቅ በአጋዥነት አጥኚዋ ተጠቅማለች፡፡

ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች የሚባሉትን እንደ ኢንተርኔት፣ መጽሐፍ፣ ጆርናል እና የመሳሰሉትን ወዘተ. ተጠቅማለች፡፡

### 3.4.1. የጽሁፍ መጠይቅ

ለጥናቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በ Oxford (1990) የቀረቡ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሰረት ያደረጉ 34 የጽሁፍ መጠይቆች ተዘጋጅተዋል፡፡ የመጠይቆቹም አብይ ትኩረት በትውስታ፣ አዕምሮታዊ፣ አካካሽ ልዕለ አዕምሮታዊ፣ ማህበራዊና ስሜት ነኪ ቁጥጥር

ብልሃቶች ስር ተማሪዎች በቃላት ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ቃላትን ሲማሩ መገልገል በሚገባቸው ዝርዝር ብልሃቶች ላይ ነው፡፡ መጠይቆቹም የተማሪዎቹን ቃላትን የመማር ብልሃት ዕውቀትና አጠቃቀም ለመፈተሽ የሚያስችሉ መረጃዎችን ያስገኛሉ ተብሎ ይታመናል፡፡

የመጠይቆቹም አቀራረብ የመማር ብልሃቶቹን የሚገልጹ ዓ/ነገሮች ከአራት አማራጭ መልሶች( ሁል ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ፣ አልፎ አልፎ እና በጭራሽ) ጋር በማቅረብ ተጠኚ ተማሪዎች የተጠቀሰውን ብልሃት አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ከቀረቡ አማራጭ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መርጠው በቁጥሩ ትይዩ ባለው ባዶ ሳጥን ውስጥ “X” ምልክት በማድርግ እንዲመልሱ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ የጽሁፍ መጠይቆቹም በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ ተሰብስበዋል፡፡

### 3.4.2. ቃለ መጠይቅ

የቃለ መጠይቁ ዓላማ በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥና ተጠኚዎቹ ስለ መማር ልምዳቸው አስመልክተው በሚሰጡት ማብራርያ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሠረት ያደረጉ 14 ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ከሁለቱም ክፍሎች የጽሁፍ መጠይቁን ከሞሉ ተጠኚዎች መካከል በነጠላ ናሙና ዘዴ ከ9ኛ ''C'' 4 ከ9ኛ ''E'' 4 በአጠቃላይ 8 ተጠኚዎች በክፍል ደረጃቸው ወይም ከ 1-4ኛ የወጡ ተማሪዎች ተመርጠው ቃለ መጠይቁ ተካሂዷል፡፡

## 3.5. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ በመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮች የተሰበሰበውን መረጃ ዓይነታዊ (Qualitative) የመረጃ ዘዴን በቁጥር፣ በመቶኛ ና በሠንጠረዥ በመተንተን፤ ፍትነታዊን (Quantitative) የትንተና ዘዴን በአጋዥነት በመጠቀም በቃለ መጠይቅ አማካይነት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር እየተደጋገፉ ተተንትነዋል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና ውጤት ማብራሪያ

ቃላትን የመማር ብልሃቶች ርቱዕ ( direct ) እና ኢ- ርቱዕ ( indirect ) በመባል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነዚህም ዋና ዋና የመማር ብልሃቶች በስራቸው ሦስት ሦስት ንዑሳን ብልሃቶችንና ሌሎች ዝርዝር የመማር ብልሃቶችን ያካትታሉ ( oxford 1990 ) :: በመሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት የሚማሩበት መንገድ እነዚህን የመማር ብልሃቶች በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ቀጥሎ በቅደም ተከተል ይቀርባል።

## 4.1. የርቱዕ የመማር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

Oxford (1990 ፣ 37) እንደገለጹት ርቱዕ የመማር ብልሃቶች የታላሚውን ቋንቋ ልዩ ልዩ ተግባራት በቀጥታ እየሰሩ ቋንቋውን እንዲማሩ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የሚያግ ዟቸው ብልሃቶች ናቸው ። ቃላትን ለመማር ተገቢ የሆኑ ርቱዕ ብልሃቶችም የትውስታ፣ አዕምሮታዊና አካካሽ ብልሃቶች ሲሆኑ እያንዳንዳቸውም በስራቸው ሌሎች ዝርዝር ብልሃቶችን ያካትታሉ ።

### 4.1.1. የትውስታ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት የሚያገኛቸውን ጽንሰ ሀሳቦች በአዕምሮው መዝገቦ የረጅም ጊዜ ትውስታ በመፍጠር ፣ በአስፈላጊው ጊዜ ትውስታ በመፍጠር፣ በአስፈላጊው ጊዜ አስታውሶ መገልገል እንዲችል የሚያግዙት ብልሃቶች ናቸው። ስያሜው እንደሚያመለክተው የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው ቃላትን በአዕምሮው መዝገቦ በመያዝ የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዙት ብልሃቶች ናቸው ።

አዳዲስ መረጃዎችን ማከማቸትና በተፈለገ ጊዜ አስታውሶ ለመገልገል ማስቻል የትውስታ ብልሃት ሁለት ዋና ዋና ቁልፍ ጠቀሜታዎች ናቸው ። እነዚህን ብልሃቶች ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ የተጻፉ ጽሁፎችን በማንበብ እና ንግግሮችን በማዳመጥ የሚያገኙትን ጠቃሚ ሀሳብ በትውስታ ውስጥ ለማከማቸት የሚያግዟቸው ናቸው ። ይህም ዕውቀታቸውን ለማስፋፋት መሰረት ይሆናቸዋል ። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ በሚያነቡበት ጊዜ በአዕምሮአቸው ውስጥ ያከማቹትን መረጃ አስታውሰው በመጠቀም ጽሁፉን ለመረዳት ወይም ሀሳባቸውን ለመግለጽ ያስችላቸዋል።

አዳዲስ ቃላትን በአዕምሮ መዝግቦ የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዙ የትውስታ ብልሃቶችም ቃላትን እንደየባህርያቸውና ዝምድናቸው መሰረት መቦደን ፣ በትውስታ ውስጥ ድምጽን መወከል ፣ ቃሉን ከሚገኝበት ቦታ ጋር ማያያዝ ፣ ቃሉን በንግግርና በጽሁፍ ውስጥ በማስገባት መለማመድ ፣ ከስዕሎች ወይም ከተጨባጭ ነገሮች ጋር ማያያዝ፣ በተወሰነ ጊዜ ክለሳ ማድረግ ና የቃሉን ፍቺ በድርጊት ማሳየት የሚሉት ናቸው።

ከተራ ቁጥር 1-8 በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ የተካተቱት ጥያቄዎችም ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የትውስታ ብልሃቶች መሰረት ያደረጉ ናቸው ። ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በአዕምሮአቸው መዝግበው የረጅም ጊዜ ትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀማቸውን ለመፈተሽ የቀረቡ ናቸው። ከዚሁ ነጥብ ጋር በተያያዘ በጽሁፍ መጠይቆቹ መሳሪያነት የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ቃለ መጠይቆች ለተጠኚዎች ቀርበዋል ። በእነዚህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 4.1 ተደራጅተው በመቅረብ ይተነተናሉ ።

**ሠንጠረዥ 4.1- የትውስታ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ**

| ተ/ቁ. | ብልሃቶች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 1 | መቦደን<br>1.1.በቃል ክፍላቸው | 7 | 12 | 8 | 13 | 30 | 50 | 15 | 25 |
| | 1.2. በፍቺ ተመሳሳይነት | 18 | 30 | 24 | 40 | 12 | 20 | 6 | 10 |
| | 1.3. በፍቺ ተቃራኒነት | 18 | 30 | 24 | 40 | 13 | 22 | 5 | 8 |
| | 1.4. በርዕሰ ጉዳይ | 10 | 17 | 12 | 20 | 20 | 33 | 18 | 30 |
| 2 | ድምፅን በመወከል | 6 | 10 | 9 | 15 | 16 | 27 | 29 | 48 |
| 3 | መገናኘት | 8 | 13 | 28 | 47 | 18 | 30 | 6 | 10 |
| 4 | መለማመድ<br>4.1. በንግግር ውስጥ | 5 | 8 | 6 | 10 | 27 | 45 | 22 | 37 |
| | 4.2. በጽሑፍ ውስጥ | 7 | 12 | 12 | 20 | 26 | 43 | 15 | 25 |
| 5 | ከስዕሎች ጋር ማዛመድ | 18 | 30 | 20 | 33 | 15 | 25 | 7 | 12 |
| 6 | አዕምሮአዊ ስዕል መፍጠር | 13 | 22 | 15 | 25 | 26 | 43 | 6 | 10 |
| 7 | ክለሳ ማድረግ | 10 | 17 | 35 | 58 | 10 | 17 | 5 | 8 |
| 8 | በድርጊት ማሳየት | 5 | 8 | 5 | 8 | 18 | 30 | 32 | 54 |

ከጥያቄ 1.1-1.4 ተማሪዎች የተለያዩ ጽሁፎችን ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ የሚያገኟቸውን አዳዲስ ቃላት በቀላሉ ለማስታወስ በሚያመች መንገድ በቡድን በቡድን በቃል ክፍላቸው ፣ በፍቺ ተመሳሳይነታቸው፣ በፍቺ ተቃራኒነታቸውና በርዕስ ጉዳይ ግንኙነታቸው ይከፋፍሉ እንደሆን ተጠይቀዋል።

በጥያቄ 1.1 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ በቃል ክፍላቸው ይመድቡ እንደሆን ተጠይቀዋል። ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው 30(50 በመቶ(%)) ተማሪዎች ጽሁፎችን ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት አልፎ አልፎ በቃል ክፍላቸው እንደሚመድቡ ሲገልጹ 15 (25 በመቶ(%)) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል። በአንጻሩም 8 (13 በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመስታወስ በቃል ክፍላቸው የመመደብ ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ ይህን ብልሃት 7(12 በመቶ)(%) ተጠኚዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው።

በጥያቄ 1.2 ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለመስታወስ በፍቺ ተመሳሳይነታቸው መሰረት የማደራጀት ብልሃት አጠቃቀማቸውን አስመልክተው በሰጡት ምላሽ 24 (40 በመቶ)(%) ተተኳሪ ተጠኚዎች ብልሃቱን አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 18 (30 በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ብልሃቱን ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ለመሆናቸው የጥናቱ መረጃ ውጤት ያመለክታል። በአንጻሩም 12 (20 በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በፍቺ ተመሳሳይነታቸው መሰረት አልፎ አልፎ የሚያደራጁ ሲሆን 6( 10 በመቶ)(%) ተጠኚዎች ይህን ብልሃት በጭራሽ የማይጠቀሙ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ጥያቄ 1.3 አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ ተቃራኒ ፍች ያላቸውን ቃላት አንድ ላይ የማደራጀት ብልሃት 24(40 በመቶ)(%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆኑ፣ 18(30 በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው። በአንጻሩም 13(22 በመቶ)(%) ተማሪዎች ቃላትን በፍቺ ተቃራኒነታቸው መሰረት የማደራጀት ብልሃት አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ 5(8 በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ለማወቅ ተችሏል።

ጥያቄ 1.4 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ በርዕስ ጉዳይ ግንኙነታቸው መሰረት የማደራጀት ብልሃት አጠቃቀማቸውን ተጠይቀዋል። ከላይ በሰንጠረዥ 4. 1 እንደሚታየው ፣ 20(33 በመቶ)(%) ተጠኚዎች ይህን ብልሃት አልፎ

አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 18(30 በመቶ)(%) ደግሞ ብልሃቱን በጭራሽ እንደማይገለገሉ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በአንጻሩም 12(20በመቶ)(%) ተጠኚዎች ቃላትን በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸው መሰረት የማደራጀት ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን 10(17በመቶ)(%) ተጠኚዎች ይህን ብልሃት ሁልጊዜ እንደሚገለገሉ ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ ከጥያቄ 1.1—1.4 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማር ይረዳቸው ዘንድ እንደየባህርያቸውና ተጠየቃዊ ዝምድናቸው መሰረት በቡድን በቡድን የመከፋፈል ብልሃት አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ የተገኘው መረጃ በሰንጠረዥ 4. 1 እንደሚታየው ቃላትን በፍቺ ተመሳሳይነትና ተቃራኒነት የመቦደን ብልሃት 48(80በመቶ)(%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ የሚገለገሉ ሲሆኑ በቃል ክፍልና በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነት የመቦደን ብልሃት 50(83በመቶ)(%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 36(60በመቶ)(%) ተጠኚዎች ቃላትን በፍቺ ተመሳሳይነትና ተቃራኒነት የመቦደን ብልሃትን ሁልጊዜ የሚገለገሉ ሲሆን 33(55በመቶ)(%) ተማሪዎች ቃላትን በቃል ክፍላቸውና በረዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸው መሰረት በጭራሽ የማይከፋፈሉ ናቸው፡፡ 42(70በመቶ)(%) ተጠኚዎች ቃላትን በፍቺ ተመሳሳይነት አልፎ አልፎ ሲቦድኑ 11(18በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህንን ብልሃት የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በጥቅሉ አብዛኞዎቹ ተመሪዎች ቃላትን በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነትና በቃል ክፍል የመቦደን ብልሃቶችን አልፎ አልፎ እና በጭራሽ እንደማይገለገሉባቸው ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ የመቦደን ብልሃቶችን አስመልክቶ ለተጠኚዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅም የተገኘውን ምላሽ በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክር ነው፡፡

ጥያቄ 2 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወይም በሌላ ቋንቋ ውስጥ በንበት ከሚቀራረብ ቃል ጋር አያይዞ የማስታወስ ብልሃት አጠቃቀማቸውን ራራ /ርኣርርኣ / የሚለውን የአማርኛ ቃል በቀላሉ ለማስታወስ ራራ / ርኣ ርኣ / ከሚለው የኦሮምኛ ቃል ጋር ፣ ቆላ /ቅኦልልኣ/ የሚለውን ደግሞ /ቅኦልልኣ/ ወይም ቅኦልኣ / ከሚሉት ጋር በማያያዝ ለማስታወስ መሞከር ለመመርመር ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ4. 1 እንደሚታየው ይህን ብልሃት 29(48በመቶ)(%) ተጠኚዎች በጭራሽ የማይገለገሉ ሲሆን፣ 16(27በመቶ)(%) ደግሞ አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 9(15በመቶ)(%) ተማሪዎች አዲሱን ቃል በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወይም በሌላ ቋንቋ በንበት ከሚቀራረብ ቃል ጋር አያይዞ የማስታወስ ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ

ሲጠቀሙ 6(10በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አዲሱን ቃል በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ወይም በሌላ ቋንቋ በንበት ከሚቀራረብ ቃል ጋር አያይዘው የማስታወስ ብልሃትን ሁልጊዜ እንደሚገለገሉበት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ኣዳዲስ ቃላትን በአዕምሮ ውስጥ መዝግቦ የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር ከሚያግዙ ብልሃቶች መካከል አንዱ ቃሉን ከሚገኝበት ገጽ፣ የማስታወቂያ ሰሌዳ . . . ጋር በማያያዝ በትውስታ ውስጥ ማስገባት ነው፡፡

በጥያቄ 3 ለቀረበው ጥያቄ 28(47በመቶ)(%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ ብልሃቱን እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 8(13በመቶ)(%) ተማሪዎች አዲሱን ቃል ከሚገኝበት ገጽና ቦታ ጋር አያይዞ የማስታወስ ብልሃትን ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 6(10በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 4.1 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ በንግግር ውስጥ በማስገባት የመለማመድ ብልሃት አጠቃቀማቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት ጥያቄ ቀርቧል፡፡ በሰንጠረዥ4. 1 እንደሚታየው ይህን ብልሃት 27 (45በመቶ)(%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 22(37በመቶ)(%) ደግሞ በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በኣንጻሩም 6(10በመቶ)(%) ተጠኚዎች አዳዲስ ቃላትን በንግግር ውስጥ በማስገባት የመለማመድ ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ ሲጠቀሙ 5(8በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ አዳዲስ ቃላትን በንግግር ውስጥ በማስገባት የመለማመድ ብልሃትን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያረጋግጣል፡፡ ይህንኑ ብልሃት አስመልክቶ ተጠኚዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ይህንኑ ውጤት የሚያጠናክር ነው፡፡ ይኸውም አብዛኞቹ ቃለ መጠይቁ የቀረበላቸው ተማሪዎች በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት የሚያገኟቸውን አዳዲስ ቃላት ሆን ብለው በንግግር ውስጥ በማስገባት ለመለማመድ ጥረት እንደሚያደርጉና በአማርኛ ቋንቋ ለመግባባት እንደሚጥሩ ገልጸዋል፡፡

ጥያቄ 4.2 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ በቃላቱ ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ኣጫጭር ጽሁፎችን በመጻፍ የመለማመድ ብልሃት አጠቃቀማቸውን ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው 26(43በመቶ)(%) ተማሪዎች በቃላት ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት አጫጭር ጽሁፎች በመጻፍ የመለማመድ ብልሃትን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ 15(25በመቶ)(%)

ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 12(20በመቶ)(%) ተጠኚዎች ይህን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲያመለክቱ 7(12በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ ትርጉም ያላቸው ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ሁል ጊዜ እንደሚለማመዱ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ጥያቄ 5 አዳዲስ ቃላትን ከስዕሎች ወይም ከተጨባጭ ነገሮች ጋር የማያያዝ ብልሃት አጠቃቀማቸውን ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው 20 (33በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለመስታወስ ከስዕሎች ወይም ከተጨባጭ ነገሮች ጋር የማያያዝ ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ በማለት ሲመልሱ 18(30በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁልጊዜ እጠቀማለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩም 15(25በመቶ)(%) ተጠኚዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ ከተጨባጭ ነገሮች ወይም ከስዕሎች ጋር የማያያዝ ብልሃትን አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ በማለት ሲመልሱ፣ 7(12በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ አንጠቀምም በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 6 አዲሱን ቃል በቀላሉ ለማስታወስ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በንበት ከሚቀራረብ ቃል ጋር በማገናኘት በአዕምሮ የመቅረጽ ብልሃትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው 26(45በመቶ)(%) ተጠኚዎች አዳዲስ ቃላትን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በንበት ከሚቀራረብ ቃል ጋር በማገናኘት አዕምሮአዊ ብልሃትን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ 13(22በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 6(10በመቶ)(%) ተማሪዎች ብልሃቱን በጭራሽ አልጠቀምም በማለት ምላሽ ሲሰጡ 15(25በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ በንበት የሚቀራረብ ቃል ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ፈልገው በማገናኘት አዕምሮአዊ ስዕል የመፍጠር ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 7 ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በቀላሉ ለማስታወስ ቀጣይነት ያለው ክለሳ ያደርጉ እንደሆን ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው 35(58በመቶ)(%) ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በመጠቀም ወይም በቃላቸው በመደጋገም ወይም በሌላ መንገድ አንዳንድ ጊዜ እንደሚመልሱ ሲገልጹ ፣ 10(17በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ የተማሯቸውን ቃላት አልፎ አልፎ እንደሚከልሱ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 10(17በመቶ)(%) ተጠኚዎች የተማሯቸውን ቃላት ሁል ጊዜ እንደሚከልሱ ሲያመለክቱ 5(8በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ በጭራሽ

ክለሳ እንደማያደርጉ የተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት ያሳያል፡፡ በተገኘው መረጃ መሰረትም አብዛኞቹ ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት በቀላሉ ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ክለሳ የማድረግ ብልሃትን የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ ይህንኑ አስመልክቶ ለተጠኚዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅም 7 ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት ለዘለቄታው ለማስታወስ ቀጣይነት ያለው ክለሳ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

ጥያቄ 8 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለመማርናለመስታወስ ፣ ፍቻቸውን በድርጊት የማስታወስ ብልሃት ይጠቀሙ እንደሆነ ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ በሰንጠረዥ4. 1 እንደሚታየው 32(54በመቶ)(%) ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ በድርጊት የማሳየት ብልሃትን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ሲገልጹ፣ 18(30በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 5(8በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ ፍቻቸውን በድርጊት የማሳየት ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ ሲጠቀሙ፣ 5(8በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ብልሃቱን ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዓላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት መጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ ነው፡፡ ለተማሪው ከጊዜ ወደ ጊዜ የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ከማስተማር ይልቅ በራሱ ጥረት እንግዳ የቃላት አይነቶችን የሚማርበትን መንገድ እንዲያጎለብት መረዳት ይበለጥ ጠቀሜታ እንዳለው የዘርፉ ምሁራን በአጽንኦት ይገልጻሉ፡፡ Oxford እና Scarcella (1994፣ 236) እንደገለጹት የተማሪው ቃላትን የመማር ብልሃት እውቀትና ልምድ እየዳበር በሄደ ቁጥር ከመምህሩ ጥገኝነት ተላቅቆ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ በራሱ ጥረት ቃላትን ለመማር ያግዘዋል፡፡ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በቃላት ትምህርት ውስጥ ጉልህ ሚና እንዳላቸው የዘርፉ ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡ ሆኖም ግን ለብልሃቶቹ የሚሰጡት ትኩረትና ደረጃ ይለያያል፡፡ ለምሳሌ Oxford (1990)፣ Thempson (1987 ) የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው የተማራቸውን ቃላት በቀላሉ ለመጨበጥና በአዕምሮው መዝግቦ ለማቆየት እንደሚረዱት ይስማሙበታል፡፡

በአጠቃላይ በሰንጠረዥ 4.1 ከተራ ቁጥር 1-8 የትውስታ ብልሃቶችን አስመልክቶ ለተጠኚ ተማሪዎች ከቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች በተገኘው መረጃ መሰረት አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ የትውስታ ብልሃቶችን በብቃት መገልገል ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ ለምሳሌ

ቃላትን በቃል ክፍላቸው መቦደን 45(75 በመቶ)(%) በርዕሰ ጉዳይ 38(63በመቶ)(%) ተጠኚዎች አልፎ አልፎ የሚጠቀሙና በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም እንግዳ ቃላትን ለረጅም ጊዜ ለማስታወስ በሚል ዓላማ በቃላዊና በጽሁፋዊ አፍልቆት ውስጥ በማስገባት ትርጉም ያላቸው ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ፣ በሃሳብ ልውውጥ እየተጠቀሙ የመለማመድ ብልሃትን አልፎ አልፎ የሚገለገሉና በጭራሽ የማይጠቀሙ 45(75በመቶ)(%) ተጠኚዎች መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

Oxford (1990፣ 39) እንደገለጹት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች መሰረታዊ ችግር በአንድ ወቅት የተማሯቸውን ቃላት ወይም አገላለጾች በሌላ ጊዜ አስታውሶ መጠቀም አለመቻል ነው፡፡ የትውስታ ብልሃቶችም የቋንቋ ተማሪዎች ይህን ችግር በብቃት እንዲቋቋሙ ያግዛቸዋል፡፡ Oxford (1990፣ 40 ) አያይዘው የቋንቋ ተማሪዎችን የትውስታ ብልሃቶች አጠቃቀም አስመልክተው እንደገለጹት የትውስታ ብልሃቶች ለቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ካላቸው ሚና አኳያ የቋንቋ ተማሪዎች በተለይም ከአንደኛ ደረጃ በላይ ያሉ እነዚህን ብልሃቶች አልፎ አልፎ ብቻ እንደሚጠቀሙ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

ከፍ ሲል የተገለጸው መረጃም ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ለረጅም ጊዜ ለማስታወስ ከሚያግዙ የትውስታ ብልሃቶች መካከል ክለሳ የማድረግ፣ በፍቾ ተመሳሳይነታቸው እና በፍቾ ተቃራኒነታቸው መሰረት መቦደን እና ከተጨባጭ ነገሮች ጋር የማያያዝ ብልሃቶችን አብዛኛዎቹ እንደሚጠቀሙና ሌሎች ከርዕሰ ጉዳይ ግንኙነትና በቃል ክፍል የመቦደን ፣ በአዕምሮ ውስጥ ድምጽን መወከል፣ አዕምሮአዊ ስዕል መፍጠር ፣ የቃሉን ፍቺ በድርጊት የማሳየት ብልሃቶችን አብዛኞቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉባቸው የተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት ያመለክታል፡፡

## 4.1.2. የአዕምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

አዕምሮታዊ ብልሃቶች የታላሚውን ቋንቋ የቃላት ተግባራት በቀጥታ መስራትን የሚጠይቁ ብልሃቶች ናቸው፡፡ እንደ Oxford (1990፣ 43) አባባል አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ የቃላት ተግባራት ሲሰራ የሚገለገልባቸው ልዩ ልዩ ብልሃቶች ሲሆኑ ፣ በቋንቋ ተማሪዎች በስፋት የሚተገበሩ ብልሃቶች ናቸው፡፡ በአዕምሮታዊ ብልሃቶች ስር መደጋገም፣ የንበት ልምምድ ማድረግ፣ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም፣ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎም ፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ድግመ ቅንብር ማድረግና ተፈጥሮአዊ ልምምድ ማድረግ የሚሉት ዝርዝር ብልሃቶች ይካተታሉ (Oxford ፣1990)፡፡

Rubin (1987፣ 23) በበኩላቸው እንደገለጹት አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ሲማሩ በቀጥታ የሚተገብሯቸው የአሰራር መንገዶች ወይም የሚወስዷቸው እርምጃዎች ወይም ችግር ማቃለያዎች ናቸው፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ ከተራ ቁጥር 9-16 የቀረቡ ሃሳቦች ተማሪዎች ስለ ልዩ ልዩ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ያላቸውን ዕውቀትና የአጠቃቀም ሁኔታ ለመመርመር ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ብልሃት አስመልክቶ ከተጠኚዎች የተገኘ መረጃ ከዚህ ቀጥሎ በሰንሰጠረዥ 2 ተደራጅቶ በመቅረብ ይተነተናል፡፡

**ሠንጠረዥ 4.2 የአዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ**

| ተ/ቁ. | ብልሃቶች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 9 | መደጋገም<br>9.1 መጻፍ | 21 | 35 | 32 | 53 | 4 | 7 | 3 | 5 |
| | 9.2 በአዕምሮ ማመላለስ | 30 | 50 | 24 | 40 | 4 | 7 | 2 | 3 |
| | 9.3 ማዳመጥ | 5 | 8 | 18 | 30 | 27 | 45 | 10 | 17 |
| 10 | ንበትን መለማመድ | 26 | 43 | 26 | 43 | 4 | 7 | 4 | 7 |
| 11 | ምንጭ መጠቀም<br>11.1 መዝገበ ቃላት | 28 | 47 | 23 | 38 | 6 | 10 | 3 | 5 |
| | 11.2 ሰዎችን መጠየቅ | 22 | 37 | 23 | 38 | 11 | 18 | 4 | 7 |
| 12 | መተርጎም | 23 | 38 | 15 | 25 | 16 | 27 | 6 | 10 |
| 13 | ማስታወሻ መያዝ | 32 | 53 | 21 | 35 | 4 | 7 | 3 | 5 |
| 14 | ትኩረተ ቃል ድምቅታ | 3 | 5 | 5 | 8 | 19 | 32 | 33 | 55 |
| 15 | ድግመ ቅንብር | 6 | 10 | 33 | 55 | 16 | 27 | 5 | 8 |
| 16 | ተፈጥሮአዊ ልምምድ<br>16.1 በማንበብ | 9 | 15 | 21 | 35 | 19 | 32 | 11 | 18 |
| | 16.2 በማዳመጥ | 3 | 5 | 16 | 27 | 27 | 45 | 14 | 23 |

ተማሪው አዳዲስ ቃላትን ደጋግሞ በመጻፍ ፣ በአዕምሮው ውስጥ በማመላለስ እና ደጋግሞ በማዳመጥ ቢለማመድ ለቃላት ዕውቀቱ መዳበር ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡ ከተራ ቁጥር 9.1-9.3 መጠይቆችም የተማሪዎቹን የእነዚህን ብልሃቶች አጠቃቀም አስመልክቶ መረጃዎችን ለማግኘት የቀረቡ ናቸው፡፡

በጥያቄ 9.1 ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ደጋግመው በመጻፍ ወይም በመናገር ይለማመዱ እንደሆነ ለመፈተሽ ተጠይቋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው 32(53በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ደጋግሞ የመጻፍ ወይም የመናገር ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 21 (35በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 4 (7በመቶ)(%) ተጠኚዎች አዳዲስ ቃላትን ደጋግሞ በመጻፍ ወይም በመናገር የመለማመድ ብልሃትን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን 3(5በመቶ)(%) ተማሪዎች ይህንን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 9.2 አዳዲስ ቃላትን በአዕምሮ የማመላለስ ብልሃት አጠቃቀማቸውን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ቀርቧል ፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው 30(50በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን በአዕምሮአቸው ውስጥ ደጋግመው በማመላለስ ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 4(7 በመቶ)(%) ተጠኚዎች አዳዲስ ቃላትን በተደጋጋሚ በአዕምሮአቸው ውስጥ በማመላለስ አልፎ አልፎ እንደሚለማመዱ ሲገልጹ፣ 2(3በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9.3 ተማሪዎች አዳዲስ ቃላት ደጋግመው በማዳመጥ ለመማር ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ ለመፈተሽ የሚያግዝ መረጃ ለማግኘት ቀርቧል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.2 እንደሚታየውም 27(45በመቶ)(%) ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን ደጋግሞ የማዳመጥ ብልሃትን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን 18(30በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 10 (17በመቶ)(%) ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላት ደጋግመው በጭራሽ እንደማያዳምጡ ሲገልጹ 5(8በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡

በጥያቄ 10 ተማሪዎች የቃላትን ንበት (pronounciation)፣ የድምጽ መጥበቅና መላላት፣ በአንድ ዓይነት ወይም በተመሳሳይ ፊደል በተገነቡ፣ ነገር ግን በንበት በሚለያዩ ቃላት ላይ ልምምድ የማድረግ ብልሃት አተገባበራቸውን ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ4. 2 እንደሚታየው፣ 26 (43በመቶ)(%) ተጠኚዎች ባንድ ቃል ውሰጥ ጠብቀውና ላልተው በሚነበቡ ድምጾች ላይ መደበኛ ልምምድ አንዳንድ ጊዜ እንደሚያደርጉ ሲገልጹ 26(43በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ በቃላት ንበት ላይ ሁል ጊዜ ልምምድ

እነደሚያደርጉ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 4(7በመቶ)(%) ተማሪዎች ጠብቀውና ላልተው የሚነበቡ ድምጾችን ለመለየት አልፎ አልፎ ልምምድ እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 4(7በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ በጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት በቀላሉ ለመማር ከሚያግዟቸው አዕምሮታዊ ብልሃቶች መካከል አንዱ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ነው፡፡ በሠንጠረዥ4. 2 እንደሚታየው ይህን ብልሃት አስመልክቶ በተራ ቁጥር 11.1 መጽሐፍ ፣ ጋዜጣ ፣ መጽሔት ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ ፍቻቸውን የማያውቋቸው አዳዲስ ቃላት ሲየጋጥሟቸው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ይጠቀሙ እንደሆን ለማወቅ ለቀረበው መጠይቅ 28(47በመቶ)(%) ተጠኚዎች ይህን ብልሃት ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 23(38በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ የአማርኛ ጽሑፎችን ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሟቸው ከአማርኛ መዝገበ ቃላት አንዳንድ ጊዜ እንደሚመለከቱ ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በአንጻሩም 6(10በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላትን ፍች ለማወቅ መዝገበ ቃላት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ 3(5በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ አዳዲስ ቃላትን በጭራሽ እንደማይመለከቱ አመልክተዋል፡፡

በጥያቄ 11.2 ተማሪዎች የአማርኛ ጽሑፎችን ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ ፍቻቸውን የማያውቋቸው አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሟቸው ሌሎች ሰዎችን ማለትም መምህሮቻቸውን ፣ የክፍል ጓደኞቻቸውን ጠይቀው ለመረዳት ስለ ሚያደርጉት ጥረት ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠርዥ 4.2 እንደሚታየው 23( 38በመቶ)(%) ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላትን ፍች ሌሎች ሰዎችን / መምህራንን ፣ የክፍል ጓደኞችን ወዘተ./ የመጠየቅ ብልሃትን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገላጹ 22(37በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 11(18በመቶ)(%) ፍቻቸውን የማያውቋቸው አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሟቸው ሌሎች ሰዎችን አልፎ አልፎ እንደሚጠይቁና 4(7በመቶ)(%) ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡

ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ከሚያግዙ አዕምሮታዊ ብልሃቶች መካከል አንዱ በታላሚው ቋንቋ የቀረበን በአዲስ ጽንሰ ሃሳብ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎም ነው፡፡ ቃላትን ለመማር ከሚያግዙ አዕምሮታዊ ብልሃቶች መካከል አንዱ የታላሚውን ቋንቋ ቃል ፍች ተመሳሳይ ፍች ወዳለው አፍ መፍቻ ቋንቋ ቃል መተርጎም ነው፡፡

ጥያቄ 12 ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ ቃል ፍች ተመሳሳይ ፍች ወዳለው ኦሮምኛ ቃል የመተርጎም ብልሃት አጠቃቀማቸውን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው 23(38በመቶ)(%) ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ፍች በደንብ ለመረዳት ተመሳሳይ ፍች ወዳላቸው ኦሮምኛ ቃላት ሁልጊዜ የሚተረጉሙ ሲሆን፣ 16(27በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 15(25በመቶ)(%) ተጠኚዎች የታላሚውን ቋንቋ አዳዲስ ቃላት ፍች(ተመሳሳይ) አቻ ፍች ወዳላቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቃላት የመተርጎም ብልሃት አንዳንድ ጊዜ ሲገለገሉ፣ 6(10በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ የተማሪዎቹን መልሶች አስተማማኝነት ለማረጋገጥ 10 ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍች በቀላሉ ለመረዳት ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ ተርጉመው ለማገናዘብ ሞክረው ያውቁ እንደሆን እንዲገልጹ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ 7 ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመተርጎም ብልሃትን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ በሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃ አብዛኞቹ ተማሪዎች የመተርጎም ብልሃትን እንደሚጠቀሙ ያሳያል፡፡

በጥያቄ 13 ተማሪዎች ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚገምቷቸውን አዳዲስ ቃላት በማስታወሻ ደብተራቸው አደረጅተው ይይዙ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ ለጽሁፍ መጠይቁም 32(53በመቶ)(%) ተጠኚዎች ሁልጊዜ እጠቀማለሁ የሚል መልስ ሲሰጡ ፣ 15(25በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩም 4(7በመቶ)(%) ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉ ሲገልጹ፣ 3(5በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ማስታወሻ የመያዝ ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል፡፡

ጥያቄ 14 በንባብ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን ከግርጌያቸው በማስመር ወይም በመክበብ ወይም በማቅለም ፍቻቸውን የመፈለግ ብልሃት አጠቃቀማቸውን ደግሞ የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ4. 2 እንደሚታየው 33(55በመቶ)(%) ተማሪዎች ጽሁፎችን ሲያነቡ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ከስራቸው በማስመር ወይም በመክበብ ከዚያም ፍቻቸውን የመፈለግ ብልሃት በጭራሽ አንጠቀምም በማለት ሲመልሱ፣ 19(32በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአንጻሩም 5(8በመቶ)(%) ተጠኚዎች አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ ሲሉ፣ 3(5በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ሁል ጊዜ እጠቀማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ይህም መረጃ ተጠኚ ተማሪዎች በንባብ ሂደት የሚያጋጥሙ

አዳዲስ ቃላትን ልዩ ምልክት በማድረግ ፍቻቸውን የመፈለግ ብልሃት አብዛኞቹ ተማሪዎች እንደማይገለገሉበት ያሳያል፡፡

በጥያቄ 15 ተማሪዎች የተማሯቸውን ቃላት እርስ በርሳቸው ወይም በተለየና በአዲስ መንገድ በማቀናበር ትርጉም ያላቸው ዓረፍተ ነገሮችን በመመስረት ይለማመዱ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው 33(55በመቶ)(%) ተጠኚዎች የተማሯቸውን ቃላት በአዲስ መንገድ በማቀናበር ትርጉም ያላቸው ዓረፍተ ነገሮችን እየመሰረቱ አንዳንድ ጊዜ እንደሚለማመዱ ሲገልጹ፣ 16(27በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 6(10በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ቀደም ሲል የተማሯቸውን ቃላት እንደገና በአዲስ መንገድ በማቀናበር ትርጉም ያላቸው ዓረፍተነገሮችን በመመስረት የመለማመድ ብልሃትን ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገለጹ፣ 5(8በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይገለገሉ አመልክተዋል፡፡

ጥያቄ 16.1 ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ ጽሁፎችን ለምሳሌ/ መጽሔት፣ ጋዜጣ/ ለማንበብ ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው 21(35በመቶ)(%) ተጠኚዎች መጽሐፍ ፣መጽሔት፣ ጋዜጣ በማንበብ የቃላት እውቀታቸውን ለማዳበር አንዳንድ ጊዜ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 19(32በመቶ)(%) ደግሞ የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ ጽሁፎችን አልፎ አልፎ እንደሚያነቡ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 9(15በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር መጽሔት፣ ጋዜጣ ሁል ጊዜ እንደሚያነቡ ሲገልጹ፣ 11(18በመቶ)(%) ደግሞ ጽሁፎችን ማለትም መጽሔት፣ ጋዜጣ . . . በጭራሽ እንደማያነቡ አመልክተዋል፡፡ በመሆኑም ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት እንደሚያሳየው ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ መጽሔት፣ ጋዜጣ . . . የማንበብ ልምዳቸው የዳበረ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ከጽሁፍ መረጃዎቹ የተገኙ መረጃዎችን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ለ10 ተማሪዎች ተመሳሳይ ቃለ መጠይቅ ቀርቦላቸው በሰጡት ምላሽ አብዛኞቹ ተማሪዎች መጽሔቶችን ፣ ጋዜጦችን አልፎ አልፎ ብቻ እንደሚያነቡ የገለጹ ሲሆን ፣ለምን እንደማያነቡ ተጠይቀው 7 ተማሪዎች እንደነዚህ ዓይነት ጽሁፎችን በማንበብ የጥናት ጊዜያቸውን ማባከን እንደማይፈልጉ ሲገልጹ 3 ተማሪዎች ደግሞ መጽሔት፣ ጋዜጣ የማንበብ ልምድ እና ፍላጎት እንደሌላቸው አመልክተዋል፡፡ ለቋንቋ

ትምህርት ዓላማዎች መሳካት የንባብ ልምድ መዳበር ወሳኝነት እንዳለው ካለማጤንና የሚነበቡ ቁሳቁሶች አለመገኘትም የራሳቸው አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳላቸው ይታሰባል፡፡

ጥያቄ 16.2 ተማሪዎች ሬዲዮ፣ ቴፕ በማዳመጥ፣ ቴሌቪዥን ፕሮግራም በመከታተል የሚያገኟቸውን አዳዲስ ቃላት ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ ልምምድ ያደርጉ እንደሆነ ለማወቅ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው 27(45በመቶ)(%) ተጠኚዎች የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም አልፎ አልፎ እንደሚከታተሉ የገለጹ ሲሆን ፣ 16(27በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም አንዳንድ ጊዜ እንደሚከታተሉ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 14(23በመቶ)(%) ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሳደግ በሚል ዓላማ እነዚህን የመገናኛ ብዙሃን በጭራሽ እንደማይከታተሉ ሲገልጹ 3(5በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ሁል ጊዜ እንደሚከታተሉ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን በመከታተል የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ የመለማመድ ብልሃትን እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ተጠኚዎቹ የሰጡትን ምላሽ ለማረጋገጥ 10 ተማሪዎች ተመሳሳይ ቃለ መጠይቅ ተጠይቀዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል 8 ተማሪዎች የሬዲዮ ፕሮግራም ለጊዜ ማሳለፊያ ፣ ለመዝናናት እንደሚከታተሉ ሲገልጹ፣ 2 ተማሪዎች በጭራሽ እንደማይከታተሉ አመልክተዋል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ለመማር ወይም የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ የሬዲዮም ሆነ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እንደማይከታተሉ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ንግግሮችን በማዳመጥ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ትኩረት ሰጥተው ካልተከታተሉ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ለይተው ልምምድ ያደርጋሉ ማለት ያስቸግራል፡፡

የሁለተኛ ቋንቋን ቃላት በቀላሉ ለመማር የሚያግዙ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን አስመልክቶ ከቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች እና ቃለ መጠይቆች አማካይነት የተገኘው መረጃ ተማሪዎች አዕምሮታዊ ብልሃቶችን በጥሩ ሁኔታ እንደሚገለገሉ ያመለክታል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.2 እንደሚታየው ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ ምንጭ መጠቀም፣ ደጋግሞ መለማመድ ፣ መተርጎም ፣ ማስታወሻ መያዝ ፣ የንበት ልምምድን ማድረግ የሚሉትን አዕምሮታዊ ብልሃቶች በስፋት እንደሚጠቀሙ የሰጡት ምላሽ ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን አስመልክቶ በተገኙ መረጃዎች መሠረት ተማሪዎች ይህን ብልሃት አዘወትረው ይጠቀማሉ ማለት ይቻላል፡፡

አዕምሮታዊ ብልሃቶች የቋንቋ ተማሪዎች በዋናነት የሚያተኩሩባቸው ናቸው፡፡ የዚህም ጥናት ግኝትም በእኚሁ ምሁር ከተጠቀሱት ነጥቦች ጋር የሚስማማ ነው፡፡ ይኸውም ከተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ የቃላት ተግባራት ደጋግመው በመለማመድ የአዳዲስ ቃላትን ፍች በደንብ ለመረዳት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አቻ ትርጉም ወዳለው ቃል ተርጉመው የማገናዘብ ብልሃቶችን ፣ እንደዚሁም የቃላትን ንበትና በአንድ ዓይነት ፊደል የተጻፉ ነገር ግን በመጥበቅና በመላላት ሲነበቡ የተለያየ ትርጉም የሚሰጡ ቃላትን ፍች ለመረዳት የመረጃ ምንጮችንም እንደሚጠቀሙ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

### 4.1.3. የአካካሽ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

አካካሽ ብልሃቶች በቋንቋ ዕውቀት ማነስ የተነሳ የተግባቦት ሂደቱ እንዳይቋረጥ የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው፡፡ አካካሽ ብልሃቶች ተማሪዎች በቂ የሰዋስው ዕውቀት በተለይም የቃላት ዕውቀት ክምችት ማነስ የተነሳ በተግባቦት ሂደት ወቅት የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመቋቋም የሚገለገሉባቸው ለቃላት ትምህርት ይበልጥ ተገቢነት ያላቸው አካካሽ ብልሃቶች የመገመት (guessing) ወይም የመፈልፈል (inferencing ) ብልሃቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪዎች የአዳዲስ ቃላትን ፍች ለመገመት የሚረዷቸው ናቸው፡፡ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ጽሁፎችን ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሟቸው ብልህነትን የተላበሰና ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ግምት ይሰጣሉ፡፡ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በንባብ ሂደት ወይም በፈተና ወቅት ወይም በማንኛውም ሁኔታ ለሚያጋጥሟቸው ከባድ ቃላት ወደ መዝገበ ቃላት ወይም ሰው ለመጠየቅ መሮጥ ተገቢ አይደለም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው ይገምታሉ ፡፡ ከተ.ቁ. 17-18 የቀረቡ መጠይቆች በአካካሽ ብልሃቶች ላይ በማተኮር ተማሪዎች በደመጣ ወይም በንባብ ሂደት የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ፍቺ የተለያዩ ፍንጮችን በመጠቀም የመገመትና አካካሽ ብልሃት አጠቃቀማቸውን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት ታልመው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በመጠይቆቹም አማካይነት በተጠኑ ተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 3 ተደራጅተው ይተነተናሉ፡፡

ሠንጠረዥ 4.3. የአካካሽ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ

| ተ/ቁ. | ብልሃቶች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁ. | በ % | በቁ. | በ % | በቁ. | በ % | በቁ. | በ % |
| 17 | ከአገባብ መገመት | 35 | 58 | 15 | 25 | 7 | 12 | 3 | 5 |
| 18 | ከአካል እንቅስቃሴ መገመት | 22 | 37 | 19 | 32 | 13 | 21 | 6 | 10 |

በጥያቄ 17 ተጠኚዎች በንባብ ሂደት የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለመረዳት የገቡበትን አውድ በመመርመር፣ ፍቻቸውን ከአገባባቸው የመገመት ብልሃት አጠቃቀማቸውን ተጠይቀዋል፡፡ 35( 58በመቶ)(%) ተጠኚዎች በንባብ ሂደት የሚያጋጥሟቸውን እንግዳ ቃላት ፍቺ ከአገባባቸው ለመገመት ሁል ጊዜ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 15( 25በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ የቃላትን ፍቺ አንዳንድ ጊዜ ከአገባባቸው ለመገመት እንደሚሞክሩ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 7(12በመቶ)(%) ተጠኚዎች በንባብ ሂደት ፍቻቸውን የማያውቋቸው ቃላት ሲያጋጥሟቸው አልፎ አልፎ ከአገባባቸው በመነሳት ፍቻቸውን የሚገምቱ ሲሆን ፣ 3(5በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው የመገመት ብልሃትን በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት የቃላት ፍቺ ለመረዳት አገባባቸውን በመመርመር ፍቻቸውን የመገመት ብልሃትን ተማሪዎች በተደጋጋሚ የሚገለገሉበት ብልሃት ነው፡፡

ጥያቄ 18 ተማሪዎች የፊት ለፊት ንግግር ሲያዳምጡ የቃላትን ፍቺ ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ (እጅ ማወራጨት፣ ፊት ማኮሳተር ) የመገመት ብልሃት አጠቃቀማቸውን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ቀርቧል፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 4.3 እንደሚታየው 22( 37በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ፍቺ ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ ሁል ጊዜ እንደሚገምቱ ሲገልጹ፣ 19(32በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ ብቻ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 13(21በመቶ)(%) ተማሪዎች የፊት ለፊት ንግግር ሲያዳምጡ ፍቻቸውን የማያውቋቸው ቃላት ሲያጋጥሟቸው ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ የመገመተት ብልሃትን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ሲገለጹ

6(10በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ የቃላትን ፍቺ ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ ለመገመት በጭራሽ እንደማይሞክሩ በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፡፡ በጽሁፍ መጠይቆቹ የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ይበልጥ ለማረጋገጥ ተመሳሳይ ቃለ መጠይቅ ለተጠኚዎች ቀርቦ ተማሪዎቹ በንባብ ወይም በማዳመጥ ሂደት ፍቺያቸውን የማያውቋቸው ቃላት ሲያጋጥሟቸው መዝገበ ቃላት ከመጠቀም ወይም ሌሎች ሰዎችን ከመጠየቅ ይልቅ ከአገባባቸውና ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ ለመገመት እንደሚሞክሩ ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በጽሁፍ መጠይቆችም ሆነ በቃለ መጠይቆች መሳሪያነት በተገኙ መረጃዎች መሰረት ተማሪዎቹ ጽሁፎችን ሲያነቡ ወይም ንግግሮችን ሲያዳምጡ ሰዎችን ከመጠየቃቸው ወይም ከመዝገበ ቃላት ከማየታቸው በፊት የገቡበትን አውድ በመመርመር ወይም ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ ፍቻቸውን ለመገመት ጥረት እንደሚያደርጉ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

## 4.2 የኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

ኢ-ርቱዕ ብልሃቶች የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት በቀጥታ መስራትን የሚጠይቁ ሳይሆኑ የትምህርቱን ሂደት ቀና በማድረግ ምቹ የመማር ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያግዙ ፣ ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት በተቃና መንገድ እንዴት ማስኬድ እንዳለበት የሚጠቁሙ ልዩ ልዩ መንገዶች ናቸው፡፡ በኢ-ርቱዕ ብልሃቶች ስር ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ፣ ስሜት ነኪ ቁጥጥር እና ማህበራዊ ብልሃቶች ይካተታሉ፡፡

### 4.2.1 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ፣ ተማሪዎች የሚማሩትን የቋንቋ ትምህርት ይዘት በማቀድ ፣ የትምህርታቸውንም ሆነ የሚሰሩትን ስራ ሂደት በመቆጣጠር ፣ የራሳቸውን ንግግርና ጽሁፍ በራሳቸው በመገምገም ቋንቋን ለመማር የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ፣ ተማሪው ትምህርቱን በዕቅድ ለመምራት ፣ በትምህርቱ ሂደት የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመለየት እና ለመቋቋም ፣ በአጠቃላይ ስራውን ለመቆጣጠር ፣ ያሳየውን ለውጥና መሻሻል ወይም የትምህርቱን ውጽአት(out come) ለመገምገም የሚገለገልባቸው ናቸው፡፡ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በማቀድ፣ በመቆጣጠርና በራስ መር ለመማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

ከጥያቄ 19-25 ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ቀርበዋል፡፡ በእነዚሁ የጽሁፍ መጠይቆች አማካይነት ከተጠኚዎቹ የተገኙ መረጃዎችም ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ4. 4 ተጠቃልለው በመቅረብ ይተነተናሉ ፡፡

**ሠንጠረዥ 4.4 የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ**

| ተ/ቁ. | ብልሃቶች | በተጠኚዎች የተሰጡ መልሶች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 19 | በቀጥታ ማትኮር | 11 | 18 | 14 | 23 | 28 | 47 | 7 | 12 |
| 20 | መርጦ ማትኮር | 6 | 10 | 16 | 27 | 25 | 42 | 13 | 21 |
| 21 | ማቀድ | 3 | 5 | 18 | 30 | 32 | 53 | 7 | 12 |
| 22 | ዓላማና ግብ ማስቀመጥ | 2 | 3 | 4 | 7 | 21 | 35 | 33 | 55 |
| 23 | መቆጣጠር | 8 | 13 | 11 | 18 | 28 | 47 | 13 | 22 |
| 24 | ግምገማ | 5 | 8 | 9 | 15 | 27 | 45 | 19 | 32 |
| 25 | የልምምድ አጋጣሚዎችን መሻት | 13 | 21 | 24 | 40 | 16 | 27 | 7 | 12 |

ጥያቄ 19 ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሳደግ በሚል ዓላማ የአማርኛን ቋንቋ የቃላት ትምህርት ትኩረት ሰጥተው ለመማርና ለመለማመድ አስቀድመው በመወሰን ቅድመ ዝግጅት ያደርጉ እንደሆን ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው ፣ 28 (47በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሳደግ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ትኩረት ሰጥተው ለመማርና ለመለማመድ አስቀድመው በመወሰን ራሳቸውን የሚያዘጋጁት አልፎ አልፎ ሲሆን ፣ 14 (23በመቶ)(%)ተማሪዎች ደግሞ ይህንን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 11 (18በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሳደግ በሚል ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ትኩረት ሰጥተው ለመማር አስቀድመው ወስነው ራሳቸውን ለማዘጋጀት ሁል ጊዜ ጥረት

የሚያደርጉ ሲሆኑ ፣ 7(12በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው።

ጥያቄ 20 ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ የቃላት ተግባራት መካከል በራሳቸው ግምጋሜ ይበልጥ የሚያስፈልጋቸውን እየለዩ ትኩረት ይሰጡ እንደሆነ ለመፈተሽ ቀርቧል። ለዚህም የጽሁፍ መጠይቅ 25(42በመቶ)(%) ተጠኚዎች ቅድሚያ የሚሹ የቃላት ተግባራትን እየለዩ አልፎ አልፎ ትኩረት እንደሚሰጡ ሲገልጹ፣ 16(27በመቶ)(%) ተማሪዎች ከቃላት ተግባራት መካከል በራሳቸው ግምጋሜ ይበልጥ የሚያስፈልጋቸውን የቃላት ተግባራት እየመረጡ አንዳንድ ጊዜ ትኩረት እንደሚሰጡ ሲገልጹ፣ 13(21በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ሲያመለክቱ ፣ 6(10በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ጥያቄ 21 ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ በቃላት ትምህርት ሂደት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በማቀድ ፣ የጥናትና የልምምድ ፕሮግራም በማዘጋጀት ለትምህርታቸው ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ ለመፈተሽ ቀርቧል። ከላይ በሠንጠረዥ 4.4 እንደሚታየው 32(53በመቶ)(%) ተጠኚዎች ለቃላት ትምህርት ዕቅድና ፕሮግራም የማዘጋጀት ብልሃትን አልፎ አልፎ ሲጠቀሙ፣ 7(12በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ትምህርታቸውን ሂደት በዕቅድና በፕሮግራም ለመምራት በጭራሽ ጥረት የማያደርጉ ሲሆኑ፣ 3(5በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ የሚገለገሉ ናቸው። ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎችን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ 10 ተማሪዎች ተመሳሳይ ይዘት ያለው የቃለ መጠይቅ ጥያቄ ተጠይቀዋል። ለቃለ መጠይቁም 6 ተማሪዎች ለቃላት ትምህርት የተለየ የክንውን ዕቅድና ፕሮግራም እንደማያዘጋጁና እንደ አመቺነቱ እንደሚያጠኑ ሲገልጹ 4 ተማሪዎች ደግሞ ፈተና ሲደርስ ብቻ ቃላትን እንደሚያጠኑ አመልክተዋል።

ጥያቄ 22 ተጠኚዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ለምን እንደሚማሩ ፣ ከቃላት ትምህርት ምን እንደሚጠብቁ ወይም የቃላት ትምህርታቸውን ዓላማና ግብ ለይተው ይነድፉ እንደሆን ተጠይቀዋል። ከላይ በሠንጠረዥ4. 4 እንደሚታየው ለጽሁፍ መጠይቁ 33(55በመቶ)(%) በጭራሽ አልጠቀምም የሚል መልስ ሲሰጡ፣ 21(35በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። በአንጻሩም 4(7በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ትምህርት ዓላማና ግብ የማዘጋጀት ብልሃት አንዳንድ

ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ ፣ 2(3በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 23 ተማሪው በቃላት ትምህርት ሂደት ስህተቱን በራሱ የመለየት፣ ትምህርቱን በትክክለኛው መንገድ እየተከታተለ መሆኑን ስራውን በራሱ የመቆጣጠር ብልሃት አጠቃቀሙን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ተጠይቋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.4 እንደሚታየው ተማሪዎች በልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ስር መተግበር ከሚጠቀምባቸው ዝርዝር ብልሃቶች መካከል አንዱ የሆነውን ራስን የመቆጣጠር ብልሃት አጠቃቀማቸውን አስመልክተው በሰጡት ምላሽ መሰረት 28(47በመቶ)(%) ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የተከተሉት መንገድ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለመለየትና ስህተታቸውን በራሳቸው ለማረም አልፎ አልፎ ብቻ ጥረት የሚያደርጉ ሲሆኑ፣ 13(22በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ራስን የመቆጣጠር ብልሃት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 11(18በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ፍቺ ለመረዳት የተከተሉት መንገድ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለመለየትና ስህተታቸውን በራሳቸው ለማረም አንዳንድ ጊዜ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 8(13በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚገለገሉ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 24 ተጠኚዎች በቃላት ትምህርታቸው ለውጥ ማሳየት አለማሳየታቸውን ለማረጋገጥ ግምገማ ያካሄዱ እንደሆን ተጠይቀዋል፡፡ 27(45በመቶ)(%) ተጠኚዎች በቃላት ትምህርታቸው ለውጥ ማሳየት አለማሳየታቸውን አልፎ አልፎ ስራቸውን በመመርመር ለማረጋገጥ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 19(32በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ 9(15በመቶ)(%) ተማሪዎች ይህንን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ፣ በአንጻሩም 5(8በመቶ)(%) ተማሪዎች ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የቃላት እውቀታችሁ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሄድ አለመሄዱን ለማረጋገጥ ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? እንዴትስ ነው ለማረጋገጥ የምትሞክሩት? የሚል ቃለ መጠይቅ ለተተኳሪ ተጠኚዎች ቀርቧል፡፡ ለቃለ መጠይቁም 8 ተማሪዎች በፈተና ወቅት ከሚያመጡት ውጤት አንጻር በቃላት ትምህርታቸው ለውጥ ወይም መሻሻል ማሳየት አለማሳየታቸውን እንደሚገመግሙ ገልጸዋል፡፡

ጥያቄ 25 ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ለመማርና ለመለማመድ ፣ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ምን ያህል ጥረት

እንደሚያደርጉ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.4 እንደሚታየው ለጽሁፍ መጠይቁ 24(40በመቶ)(%) ተጠኚዎች ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ለመማርና ለመለማመድ አንዳንድ ጊዜ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 16(27በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 13(21በመቶ)(%) ተጠኚዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ለመማርና ለመለማመድ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ብልሃት ሁል ጊዜ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 7(12በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የተጠኚዎችን የልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች አጠቃቀም ለመፈተሽ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ውጤት እንደሚያመለክተው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ ይኸውም እያንዳንዱ ተጠኚ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃት አጠቃቀሙን አስመልክቶ የሰጠው ምላሽ / ለምሳሌ ትኩረት የመስጠት ፣ የማቀድ፣ ዓላማና ግብ መንደፍ ፣ ራስን መቆጣጠር ፣ ራስን መገምገም/ ለሚሉት ዝርዝር ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች አብዛኛው ተጠኚ አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ የሚል ወይም በጭራሽ አልጠቀምም የሚል ነው፡፡ የተማሪው እነዚህን ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች በብቃት አለመጠቀም አንዱ ምክንያት የብልሃቶቹ ባህሪ በራሱ ሊሆን ይችላል፡፡ ይኸውም ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው፡-

- የሚያከናውናቸውን ተግባራት እንዲያቅድ ፣
- ለውጥ /መሻሻል/ ማሳየት አለማሳየቱን በራሱ እንዲገመግም ፣
- ለለመዳው እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ለይቶ መፍትሔ እንዲፈልግ ፣
- ሥራውን በራሱ የመቆጣጠር ብልሃት እንዲጠቀም የሚያግዙ ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት የተማሪውን የግል ጥረት የሚጠይቁና ራስ መር ተማሪ ይሆን ዘንድ የሚመሩት ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪው የቃላት ዕውቀቱን ለማሻሻል ምቹ የመማር ሁኔታ በመፍጠር ራሱን ዝግጁ እንዲያደርግ የሚያግዙት ናቸው፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች ተማሪው በቃላት ትምህርቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የጎላ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

### 4.2.2. የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ከተማሪው ስሜት ፣ ዝንባሌና መነቃቃት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው ታላሚውን ቋንቋ ሲማር የሚሰማውን የፍርሃት፣ የጭንቀት፣ አሉታዊ አመለካከትና ዝንባሌ ለመቆጣጠር የሚያግዙት ብልሃቶች ናቸው፡፡

Stem (1983 ፣ 411 ) እንደገለጹት ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የሚገጥሟቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግሮች ለመቋቋም የሚረዷቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ሁለተኛን ቋንቋ ሲማሩ የሚገጥሟቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግር በብቃት ይቋቋማሉ ፤ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ከቋንቋው ተናጋሪዎች ጋር በሚያደርጉት ተራክቦ የቋንቋ ዕውቀት ማነስና ለህብረተሰቡ ባህል እንግዳ መሆን በፍላጎታቸውና በንቁ ተሳትፎአቸው ላይ የተወሰነ ጫና እና የስሜት መረበሽ ማሳደራቸው አይቀሬ ቢሆንም ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በውስጣቸው ያደረውን የፍርሃት ስሜት ለመቋቋም አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋሉ፡፡

Oxford (1990 ፣ 140 ) እንደገለጹት ደግሞ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የሚሰማቸውን ስሜት በመቆጣጠርና ራሳቸውን በራሳቸው በማበረታታት በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ የሚያግዟቸው ናቸው፡፡ Oxford አያይዘው እንደገለጹት ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት የሚሰማቸውን ስሜትና አሉታዊ አመለካከት እንዴት መቆጣጠር እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡ መጥፎ ስሜት ለውጥን ያደናቅፋል ፣ ጥሩ ስሜት ደግሞ የትምህርቱን ሂደት አስደሳች እና ውጤታማ ያደርጋል፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች መካከል ምናልባትም በጣም ትልቁ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ነው፡፡

ጥያቄ 26-30 ተተኳሪ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ቃላት ሲማሩ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችን በብቃት ይጠቀሙ እንደሆን ለመፈተሽ የሚያግዙ መረጃዎችን ለማግኘት ቀርበዋል፡፡ የእነዚህንም ብልሃቶች አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ከተጠኚ ተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 5 ተጠቃለው በመቅረብ ይተነተናሉ፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ጥቅል መረጃ

| ተ/ቁ. | ብልሃቶች | በተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | ሁል ጊዜ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 26 | ራስን ማዝናናት | 12 | 20 | 27 | 45 | 11 | 18 | 10 | 17 |
| 27 | ራስን ማድነቅ | 19 | 32 | 27 | 45 | 6 | 10 | 8 | 13 |
| 28 | ራስን መሸለም | 27 | 45 | 2 | 3 | 28 | 47 | 3 | 5 |
| 29 | በንቃት መሳተፍ | 9 | 15 | 11 | 18 | 32 | 53 | 8 | 13 |
| 30 | ስሜትን ማጋራት | 11 | 18 | 15 | 25 | 25 | 42 | 9 | 15 |

በጥያቄ 26 ተማሪዎች የቃላት ተግባራትን ከመስራታቸው በፊት አወንታዊ በሆነ መንገድ /ቀልድ ፈጥሮ ሊሆን ይችላል/ አካልና አዕምሮን የማዝናናት ብልሃት ይጠቀሙ ወይም አይጠቀሙ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.5 እንደሚታየው 27(45በመቶ )(%) ተጠኚዎች የቃላት መልመጃዎችን ከመስራታቸው በፊት የድካም ስሜት ለመቀነስ ሲባል አወንታዊ በሆነ መንገድ አዕምሮና አካልን የማዝናናት ብልሃቶችን አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልፁ፣ 12(20በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 11(18 በመቶ)(%) ተጠኚዎች ከቃላት ተግባራት በፊት የድካም ስሜታቸውን ለመቀነስ አካልና አዕምሮን የማዝናናት ብልሃት አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 10(17በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በጥያቄ 27 ተጠኚዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሟቸውን ከባድ የቃላት መልመጃዎች ከመሰራታቸው በፊት ችሎታቸውን በማድነቅ ራሳቸውን አዳዲስ ቃላትን የመማር ፍላጎትና ችሎታ ያላቸው ጎበዝ ተማሪዎች አድርገው ይቆጥሩ እንደሆነ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.5 እንደሚታየው 27(45በመቶ)(%) ተማሪዎች አንዳንድ ጊዜ የራሳቸውን ችሎታና ጠንካራነት በሙገሳ ቃላት በመግለጽ ራሳቸውን እንደሚያበረታቱ ሲገልጹ ፣ 19(32በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ የራስን ችሎታ የማድነቅ ብልሃትን ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 8(13በመቶ)(%)

ተጠኚዎች የራስ ችሎታን የማድነቅ ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ሲገለጹ ፣ 6(10በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 28 ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ / ለምሳሌ የቃላት እውቀታቸው መሻሻሉን ሲያውቁ፣ወይም በቃላት ፈተና ፣ ሙከራ ጥሩ ውጤት ሲያስመዘግቡ / ራሳቸውን በራሳቸው የሚያደንቁ እንደሆነ ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ ከተጠኚዎች በተገኘው መረጃ መሰረትም 2(3በመቶ)(%) ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን የሚያደንቁ ሲሆን ፣ 27(45በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 3(5በመቶ)(%) ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ ራሳቸውን በራሳቸው በጭራሽ እንደማያደንቁ ሲገልጹ 28(47በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ በቃላት ትምህርት ውጤታማ ሲሆኑ የቃላት ችሎታቸውን አልፎ አልፎ እንደሚያደንቁ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ጥያቄ 29 ተማሪዎች የታላሚውን  ቋንቋ ቃላት ሲማሩ እንሳሳታለን የሚል ስጋት ሳያግዳቸው በትምህርቱ ሂደት ያለፍርሃት ይሳተፉ እንደሆነ ለመፈተሽ ቀርቧል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.5 እንደሚታየው 32(53በመቶ)(%) ተማሪዎች በቃላት ትምህርት ሂደት አልፎ አልፎ ብቻ ለመሳተፍ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ ፣ 11(18በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ አንዳንድ ጊዜ በንቃት እንደሚሳተፉ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በአንጻሩም 9(15በመቶ)(%) ተጠኚዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ እንሳሳታለን የሚል ስጋት ሳያግዳቸው በትምህርቱ ሂደት ሁል ጊዜ በንቃት ለመሳተፍ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 8(13በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ በቃላት ትምህርት ሂደት በንቃት የመሳተፍ ብልሃትን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 30 በቃላት ትምህርት ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለሌሎች / ለመምህራን፣ ለክፍል ጓደኞች / የማጋራት ብልሃትን የሚመለከት መረጃ ለማግኘት ቀርቧል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.5 እንደሚታየው 25(42በመቶ)(%) ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ የሚሰማቸውን ስሜት /ደስተኛ መሆን አለመሆናቸውን / አልፎ አልፎ ለመምህራቸው ወይም ለክፍል ጓደኞቻቸው እንደሚያካፍሉ ሲገለጹ፣ 15(25በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ ብቻ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በአንጻሩም 11(18በመቶ)(%) ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ የገጠማቸውን ችግር ፣

የተሰማቸውን ስሜት ለመምህሮቻቸው ወይም ለክፍል ጓደኞቻቸው የማጋራት ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚጠቀሙ ሲገልጹ ፣ 9(15በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ስሜትን ለሌላ የማጋራት ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶችን (Affective strategies ) አስመልክቶ ለተጠኚ ተማሪዎች በቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆች በተገኘው መረጃ መሠረት ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ሲማሩ የሚሰማቸውን የፍርሃት፣ የጭንቀት፣ አሉታዊ አመለካከትና ዝንባሌ ለመቆጣጠር የሚያግዙ ብልሃቶችን የመጠቀም ብቃታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 5 እንደሚታየው ተማሪው የቃላት ትምህርቱን ሂደት የሚያደናቅፉ ስሜቶችን ለመቆጣጠር የሚያግዙ አካልና አዕምሮን ማዝናናት፣ በንቃት መሳተፍና ስሜትን ለሌሎች ማጋራት ብልሃቶችን አብዛኞቹ ተማሪዎች አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ የተሰበሰበው መረጃ ትንተና ውጤት ያመለክታል፡፡

### 4.2.3 የማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ውጤት

እነዚህ ብልሃቶች ቋንቋን ለመማር የሚያግዙ ማህበራዊ ተራክቦዎችን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ ቋንቋን መማር የሌላ ሰው ተሳትፎ እስከ ጠየቀ ድረስ ተማሪዎችም ቋንቋን ሲማሩ ሁሌም በግል አይሰሩም ፤ እርስ በርሳቸው ለመረዳዳት ከብጤዎቻቸው ጋር ይሰራሉ፣ ግለጽ ያልሆኑላቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን የአዳዲስ ቃላት ፍቺ መምህሮቻቸውን እና ሌሎች ሰዎችን ይጠይቃሉ፡፡ Oxford (1990 ) እንደገለጹት ማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ቃላትን ሲማሩ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እርስ በርሳቸው እየተረዳዱ ፣ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ መምህሮቻቸውንና በቋንቋው ብቃት ያላቸውን ሰዎች እየጠየቁ እንደሚማሩ የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡

Rubin (1987፣27) በበኩላቸው እንደገለጹት ደግሞ ማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ዕውቀታቸውን በተግባር ለመለማመድ ዕድል የሚሰጧቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባቦታዊ ግንኙነት በማድረግ ታላሚውን ቋንቋ በተለያየ መንገድ እንዲለማመዱ ያግዛቸዋል፡፡ በማህበራዊ ብልሃቶች ስር ማብራሪያ መጠየቅ፣ ከብጤ ጋር መተባበር ፣ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ መምህራንን ወይም ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ ፣ የታላሚውን ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና አኗኗር ዕውቀት ማሳደግ ይካተታሉ፡፡

በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ ከጥያቄ 31- 34 ተማሪዎች ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ማህበራዊ ብልሃቶችን በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን

ለመፈተሽ ቀርበዋል፡፡ በጽሁፍ መጠይቆቹም የተገኙ መረጃዎች ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ 4.6 ተደራጅተው በመቅረብ ይተነተናሉ፡፡

**ሠንጠረዥ 4.6 የማህበራዊ ብልሃቶች ጥቅል መረጃ**

| ተ/ቁ. | ብልሃቶች | ከተጠኚዎች የተሰጡ ምላሾች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በጭራሽ | |
| | | በቁ. | በ % | በቁ. | በ % | በቁ. | በ % | በቁ. | በ % |
| 31 | መጠየቅ | 22 | 37 | 15 | 25 | 15 | 25 | 8 | 13 |
| 32 | መተባበር | 20 | 33 | 27 | 45 | 9 | 15 | 4 | 7 |
| 33 | ጥሩ ችሎታ ካላቸው ጋር ግንባር መፍጠር | 9 | 15 | 5 | 8 | 27 | 45 | 19 | 32 |
| 34 | ባህላዊ ዕውቀት ማዳበር | 6 | 10 | 12 | 20 | 27 | 45 | 15 | 25 |

ጥያቄ 31 ተማሪዎች ያልገባቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን ቃል ፍች መምህሮቻቸውን ወይም የክፍል ጓደኞቻቸውን ወይም ሌሎች ሰዎችን ጠይቀው ለመረዳት ጥረት ያደርጉ እንደሆን ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.6 እንደሚታየው 22(37በመቶ)(%) ተጠኚዎች ያልገባቸውን ወይም እርግጠኛ ያልሆኑበትን ቃል ፍቺ ሌሎች ሰዎችን ጠይቀው ለመረዳት ሁል ጊዜ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 15(25በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ሌሎች ሰዎችን አንዳንድ ጊዜ ብቻ እንደሚጠይቁ በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 15(25በመቶ)(%) ተጠኚዎች ሌሎች ሰዎችን ገለጻ ፣ ማብራሪያ የመጠየቅ ብልሃትን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ 8(13በመቶ)(%) ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ከጽሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 32 ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የቃላት እውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ የቃላት መልመጃዎችን በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በቡድንም ሆነ በጥንድ ለመለማመድ/ለመስራት/ ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ ተጠይቀዋል፡፡ ለጽሁፍ መጠይቁም 27(45በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት መልመጃዎችን ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በመተባበር አንዳንድ ጊዜ እንደሚሰሩ ሲገልጹ፣ 20(33በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ ይህን ብልሃት ሁል ጊዜ እንደሚገለገሉ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 9(15በመቶ)(%) ተጠኚዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር

በመተባበር የመስራት ብልሃትን አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ የሚል መልስ ሲሰጡ፣ 4(7በመቶ)(%) ተጠኚዎች ደግሞ በጭራሽ አልጠቀምም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በጥያቄ 33 ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሳደግ በአማርኛ ቋንቋ ጥሩ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት ፈጥረው ለመለማመድ ምን ያህል ጥረት እንደሚየደርጉ ተጠይቀዋል፡፡ ከላይ በሠንጠረዥ 4.6 እንደሚታየው 27(45በመቶ)(%) ተጠኚዎች በታላሚው ቋንቋ የመገልገል ብቃት ካላቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት ፈጥረው አልፎ አልፎ እንደሚለማመዱ ሲገልጹ፣ 19(32በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ጥሩ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት ፈጥሮ የመለማመድ ብልሃትን በጭራሽ እንደማይጠቀሙ አመልክተዋል፡፡ በአንጻሩም 9(15በመቶ)(%) ተጠኚዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በሚል ዓላማ በታላሚው ቋንቋ ጥሩ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት ፈጥረው ለመለማመድ ሁልጊዜ ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገለጹ፣ 5(8በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት አንዳንድ ጊዜ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 34 ተማሪዎች ስለ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና የአኗኗር ስርዓት ለማወቅ ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት ቀርቧል፡፡ በተገኘው መረጃ መሠረት 27(45በመቶ)(%) ተጠኚዎች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ባህልና የአኗኗር ስርዓት ለማወቅ ፣ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ወይም መጽሔት፣ መጽሐፍ፣ ጋዜጣ አልፎ አልፎ የሚከታተሉ ወይም የሚያነቡ ሲሆን ፣ 15(25በመቶ)(%) ተማሪዎች ደግሞ ይህን ብልሃት በጭራሽ የማይጠቀሙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም 12(20በመቶ)(%) ተጠኚዎች ስለ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና አኗኗር ስርዓት የሚገልጹ ጽሑፎችን ወይም የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን አንዳንድ ጊዜ እንደሚከታተሉ ሲገልጹ፣ 6(10በመቶ)(%) ደግሞ ሁልጊዜ እንደሚከታተሉ ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በቃላት ትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ማህበራዊ ብልሃቶች የጎላ ሚና እንዳላቸው ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡ Stem (1983 ) እንደገለጹት ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ተጠቃሚዎችና ህብረተሰብ ጋር በግልም ሆነ በጋራ ተግባቦታዊ ግንኙነት ለማድረግ ይጥራሉ፡፡ ጥሩ የቋንቋ ተማሪዎች የችሎታ መለኪያ አሊያም የብቃት ደረጃ መለኪያ ፈተና መጥቶ ካልገታቸው በስተቀር በሁለተኛ ቋንቋ እንደ ቋንቋው ተናጋሪ በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ ይህም የቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ይረዳቸዋል፡፡ ማህበራዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እርስ

በርሳቸው እየተረዳዱ እንዲሰሩ ፣ ግልጽ ያልሆነላቸውን መምህሮቻቸውንና በቋንቋው ብቃት ያላቸውን ሰዎች እየጠየቁ እንዲማሩ የሚያግዟቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ በዚህም ብልሃት ስር ተማሪው ገለጻ፣ ማብራሪያ፣ በማስረጃ የተደገፈ የአሰራር መንገድ፣ ስህተትን ማስተካከያ የእርምት ትብብር . . . የሚያመላክቱ ጥያቄዎች መጠየቅ፣ ከክፍል ጓደኛ፣ ይረዱኛል ብሎ ከሚገምታቸው ሰዎች ጋር ህብረት ፈጥሮ መስራት ይካተታሉ (Oxford 1990 )፡፡ መሆኑም ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ማህበራዊ የመማር ብልሃቶችን መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ በጽሁፍ መጠይቆች መሳሪያነት የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ቃላት የሚማሩበት መንገድ ማህበራዊ ብልሃቶችን በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ምናልባት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ብቃት ካላቸው ሰዎች ጋር ህብረት በመፍጠርና የታላሚውን ቋንቋ ህብረተሰብ ባህልና የአኗኗር ስርዓት መማር ስላላቸው ሚና ዕውቀቱም ሆነ ልምዱ ስለሌላቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ ስለ ማህበራዊ ብልሃቶች ያላቸው ዕውቀትና ልምድ አለመዳበር ከመማር ማስተማሩ ሂደት የመነጨም ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ሲማሩ የትምህርቱ ሂደት ዋና ተዋናይ ሆነው በጥንድ፣ በቡድን ስራዎች ውስጥ ራሳቸውን እያሳተፉ ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ጀምረው ደረጃ በደረጃ ማህበራዊ የመማር ብልሃቶችን በስፋት የመጠቀም/ የመለማመድ / ዕድል ማጣታቸው ሊሆን ይችላል፡፡ የጥናቱም ውጤት ማህበራዊ ብልሃቶች በስፋት በተማሪዎቹ አገልግሎት ላይ እንደማይውሉ ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና አስተያየት

## 5.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን በመማርያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ የሚማሩበት ወይም የሚለማመዱበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት በመገልገል ላይ የተመሰረተ መሆን አለመሆኑን መፈተሽ ነበር፡፡ በመሆኑም ለቃላት ትምህርት ውጤታማነት በተለያየ መንገድ ዕገዛ የሚያደርጉ ርቱዕ የመማር ብልሃቶችን (የትውስታ፣ አዕምሮታዊ እና አካካሽ) እና ኢ-ርቱዕ የመማር ብልሃቶች (ልዕለ አዕምሮታዊ፣ ስሜት ነኪ ቁጥጥር እና ማህበራዊ) የመማር ብልሃቶችን መሠረት በማድረግ ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ ወይም ሲለማመዱ እነዚህን ብልሃቶች የመጠቀም ብልሃታቸውን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የጽሁፍ መጠይቅ በዋናነት አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን በጽሁፍ መጠይቆቹ አማካይነት የተገኙ መረጃዎችን አስተማማኝነት ለማረጋገጥም ቃለ መጠይቅ በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት አገልግሏል፡፡ እያንዳንዱን የመማር ብልሃት የሚመለከቱ የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎችም በመልክ በመልካቸው በሠንጠረዥ ተደራጅተው እንዲታዩ በማድረግ በቃለ መጠይቅ ከተገኙ መረጃዎች ጋር እርስ በርሳቸው እየተደጋገፉ በዓይነታዊ የመረጃ አተናተን ሂደትና በገለፃ ዘዴ ትንተና ተካሂዷል፡፡

በሁለቱም መሳሪያዎች በተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ውጤት መሠረትም ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት ወይም የሚለማመዱበት መንገድ ቃላትን የመማር ብልሃቶች መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ለቃላት ትምህርት ውጤታማነት በተለያየ መንገድ ዕገዛ የሚያደርጉ በርካታ ብልሃቶችን አብዛኞቹ ተጠኚዎች አልፎ አልፎ እንደሚገለገሉባቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ይህም ተማሪዎች የብዙዎቹ ብልሃቶች የዳበረ ዕውቀትና ልምድ እንደሌላቸው ያመለክታል፡፡ ከእነዚህም ብልሃቶች መካከል አንዱ የትውስታ ብልሃት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ Oxford (1990 ፣ 39) እንደገለጹት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከሚያጋጥሟቸው መሠረታዊ ችግሮች መካከል አንዱ በአንድ ወቅት የተማሯቸውንና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚገለገሉባቸውን ቃላት በሌላ ጊዜ አስታውሰው መጠቀም አለመቻል ነው፡፡ የትውስታ ብልሃቶች ተማሪው እነዚህን ችግሮች በብቃት እንዲቋቋም ያግዙታል፡፡ ተማሪው አዳዲስ ቃላትን በአዕምሮው መዝግቦ ለመያዝና የረጅም

ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር የሚያግዙት ብልሃቶችንም መቦደን፣ በአዕምሮ ውስጥ ድምፅን መወከል፣ ቃሉን ከተጨባጭ ነገሮች ጋር ማገናኘት፣ የቃሉን ፍቺ በድርጊት ማሳየትና ክለሳ ማድረግ ናቸው።

እነዚህን ዝርዝር ብልሃቶች አስመልክቶ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ በቃል ክፍላቸውና በርዕስ ጉዳይ ግንኙነታቸው መሠረት የመቦደን ብልሃት፣ በአዕምሮ ውስጥ ድምፅን መወከል፣ አዕምሮአዊ ስዕል መፍጠር እና የቃሉን ፍቺ በድርጊት ማሳየት አብዛኛው ተማሪ አልፎ አልፎ እንደሚገለገልባቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ከመቦደን ብልሃቶች ቃላትን በፍቺ ተመሳሳይነታቸውና ተቃራኒነታቸው መሠረት የመቦደን ብልሃት አብዛኛው ተማሪ ሁል ጊዜ የሚጠቀምባቸው ብልሃቶች መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል። ተማሪዎቹ እነዚህን ብልሃቶች አዝወትረው መጠቀማቸው የትምህርት ልምዳቸው ከዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ጀምሮ ቃላትን በዚህ ዓይነት መንገድ መቦደን ልምድ በማካበታቸው ይመስላል።

በአጠቃላይ የትውስታ ብልሃቶችን አስመልክቶ ከተጠኚዎች የተሰበሰበው መረጃ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበትን መንገድ ብልሃቶቹን በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን ያሳያል። አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ ተግባራት በቀጥታ በመስራት፣ በቋንቋው በመጠቀምና ከራሱም አስልቶ በመለማመድ እንዲማር የሚያስችሉት ብልሃቶች (Oxford 1990 ፣ Tudor 1996 ፣ Richard and Lockhart 1996)። አዕምሮታዊ ብልሃቶች ተማሪው የታላሚውን ቋንቋ የቃላት ተግባራት በቀጥታ ሲሰራ የሚገለገልባቸው ልዩ ልዩ ብልሃቶች ናቸው። አዳዲስ ቃላትን ደጋግሞ የመጻፍ ፣ በአዕምሮ ውስጥ ማመላለስና ማዳመጥ ፣ ድምጾችን መለማመድ ፣ ምንጭ መጠቀም ፣ መተርጎም ፣ ማስታወሻ መያዝ ፣ ትኩረተ ቃል ድምቅታ ፣ ድግመ ቅንብር እና ተፈጥሮአዊ ልምምድ ማድረግ በአዕምሮታዊ ብልሃቶች ስር ይካተታሉ (Oxford 1990፣ 39)።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ዝርዝር አዕምሮታዊ ብልሃቶች መሠረት በማድረግ ፣ ተጠኚ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ ብልሃቶቹን መሠረት መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ጥረት ተደርጓል። በተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና ውጤት መሠረትም ተማሪዎቹ ቃላትን የሚማሩበት መንገድ አብዛኛዎቹ አዕምሮታዊ ብልሃቶቹ በብቃት በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ንዑስ ክፍል ስር በስምንት ዝርዝር አዕምሮታዊ ብልሃቶች ላይ ፍተሻ ተካሂዷል። ከእነዚህም መካከል ሁለቱ ማለትም በንባብ ሂደት የሚያጋጥሙ አዳዲስ ቃላትን ከግርጌአቸው በማስመር ወይም በመክበብ ወይም

በማቅለም ፍቻቸውን የመፈለግ ብልሃት /ትኩረተ ቃል ድምቀታ/ high lighting/ እና የቃላት ዕውቀትን ለማሻሻል በሚል ዓላማ መጽሔት፣ ጋዜጣ ማንበብ ፣ ወይም ሬዲ ፣ የቴሌተቪዥን ፕሮግራም በመከታተል / ተፈጥሯዊ ልምምድ የማድረግ ብልሃቶች ብቻ አብላጫው ተማሪ አልፎ አልፎ እንደሚገለገልባቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

Oxford (1990 ፣ 43) እንደገለጹት አዕምሮታዊ ብልሃቶች ከቋንቋ ተማሪዎች ጋር ይበልጥ እውቂያ ያላቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990) አካለው እንደገለጹት አዕምሮታዊ ብልሃቶች በቋንቋ ተማሪዎች በተደጋጋሚ አገልግሎት ላይ የሚውሉ ብልሃቶች ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ውጤትም በእኚሁ ምሁር ከቀረቡት ነጥቦች ጋር የሚስማማ ነው፡፡

በጥናቱ ውስጥ ፍተሻ የተካሄደባቸው አካካሽ ብልሃቶች የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው እና ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ የመገመት ብልሃቶች ነበሩ፡፡ በሁለቱም መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት አብዛኞቹ ተማሪዎች በንባብ ወይም በደመጣ ወቅት እንግዳ ቃላት ሲያጋጥሟቸው መዝገበ ቃላት ከመጠቀማቸው ወይም ሌሎች ሰዎችን ከመጠየቃቸው በፊት ፍቻቸውን ከአገባባቸው ወይም ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ መገመት ያለውን ጠቀሜታ የተረዱ ይመስላል፡፡ ከተጠኚ ተማሪዎች አብላጫው ድምፅ በንባብ ሂደት ወይም በደመጣ ወቅት ለሚያጋጥሟቸው እንግዳ ቃላት ፍቺ መዝገበ ቃላት ከመጠቀማቸው በፊት ከአገባባቸው ወይም ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ ለመገመት ጥረት እንደሚያደርጉ አመልክተዋል፡፡ ተማሪዎቹ የቃላትን ፍቺ ከአገባባቸው ወይም ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ መገመት ሲያቅታቸው ብቻ መዝገበ ቃላት እንደሚጠቀሙ ለቃለ መጠይቁ በሰጡት ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን አስመልክቶ በተካሄደው ፍተሻ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃለትን የሚማሩበት መንገድ እነዚህን ብልሃቶች መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠኚ ተማሪዎች በአብዛኛው ብልሃቶቹን አልፎ አልፎ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል ፡፡ ለቃላት ትምህርት የክንውን ዕቅድ ማዘጋጀት ፣ ዓላማና ግብ መንደፍ ፣ ራስን በራስ መቆጣጠር እና መገምገም ከልዕለ  አዕምሮታዊ ብልሃቶች መካከል አብላጫው ተማሪ አልፎ አልፎ እንደሚገለገልባቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት ተማሪዎቹ ለትምህርታቸው ኃላፊነት ወስደው በራስ መር የመማር ልምድ አለማዳበራቸውና ሁሉንም ነገር ከመምህሮቻቸው ስለሚጠብቁ ሊሆን ይችላል፡፡

ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች ተማሪው በትምህርቱ ሂደት የሚሰማውን የፍርሃት ፣ የጭንቀት ፣ አሉታዊ አመለካከትና ዝንባሌ ለመቆጣጠር የሚጠቀማቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ አወንታዊ መዝናናት ፣ ለራስ ችሎታ ጥሩ ግምት መስጠት ፣ ራስን መሸለም ፣ ስሜትን

ለሌላ ማጋራት የቃላት ትምህርቱን ሂደት የሚያደናቅፉ ስሜቶችን ለመቆጣጠር የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው፡፡ Oxford (1990 ፣ 140) በዚህ ጥናት ውስጥም የተማሪው የእነዚህን ብልሃቶች አጠቃቀም ተፈትሿል፡፡ ከተጠኚዎች በተገኘው መረጃ ትንተና መሠረትም የተማሪዎቹ ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃት አጠቃቀም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ብልሃት ስር ከተፈተሹት አምስት ዝርዝር ብልሃቶች መካከል ሦሥቱን /ራስን መሸለም ፣ በንቃት መሳተፍ እና ስሜትን ለሌላ ማጋራት/ ዝርዝር ብልሃቶችን አብላጫው ተማሪ አልፎ አልፎ እንደሚጠቀምባቸው የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

ውጤታማ የቋንቋ ትምህርት ሂደት የተማሪውን ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሰዎችንም ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አኳያ ቋንቋን መማር የሌላን ሰው ተሳትፎ እስከጠየቀ ድረስ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችም ለቃላት ትምህርታቸው ውጤታማነት ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እርስ በእርሳቸው እየተረዳዱ ፣ ግልፅ ያልሆነላቸውን መምህሮቻቸውንና በቋንቋው ብቃት ያላቸውን ሰዎች እየጠየቁ ሊማሩ ይገባል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም የተማሪዎቹን ማህበራዊ ብልሃቶች (ሌሎች ሰዎችን መጠየቅ ፣ ከብጤ ጋር መተባበር ፣ ብቁ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር ህብረት መፍጠር ፣ ባህላዊ ዕውቀት ማዳበር/ አጠቃቀም አስመልክቶ በተካሄደው ፍተሻ ማህበራዊ ብልሃቶችን አብዛኛው ተማሪ አልፎ አልፎ እንደሚገለገልባቸው ከተጠኚ ተማሪዎች በተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተለይም ተማሪዎቹ የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር በታላሚው ቋንቋ የመጠቀም ብቃት ካላቸው ሰዎች ጋር ግንባር ፈጥረው ለመለማመድና የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ባህልና የአኗኗር ስርዓት ዕውቀት ለማዳበር የሚያደርጉት ጥረት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤት መሠረት ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን የሚማሩበት ወይም የሚለማመዱበት መንገድ ብዙዎቹን የመማር ብልሃቶች በብቃት በመገልገል ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ስለ ብዙዎቹ ብልሁቶች ያላቸው ዕውቀትና ልምድ የዳበረ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

ከማጠቃለያው ግኝት በመነሳት አጥኚዋ የሚከተሉትን ደምድማለች፡፡

- በማጠቃለያው እንደተመለከትነው ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶችን አስመልክቶ ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ለመማር ብልሃቶቹን በብቃት ለመገልገል ኃላፊነት ወስደው በራስ መር የመማር ልምድ ማዳበር አለባቸው፡፡

- የስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃት አጠቃቀም ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት የሚሰማቸውን የፍርሃት ስሜት ፣ የጭንቀት ፣ አሉታዊ አመለካከት እና ዝንባሌ የሚቆጣጠሩ መሆን አለባቸው፡፡
- አካካሽ ብልሃቶችን በተገቢው መንገድ ለመጠቀም ተማሪዎቹ የቃላቱን ፍቺ ከአገባባቸው እና ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ በመገመት የመጠቀም ልምድ አለባቸው፡፡

## 5.3. አስተያየት

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ቋንቋን እንዴት መማር እንደሚቻል እንዲማሩ መርዳት የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡ Huttunen (1996 ፣ 87) እንደገለጹት መማርን በመማር ሂደት ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርታቸው ኃላፊነት ሊሰማቸው ፣ ከመምህሮቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር ተባብረው ፣ ሊሰሩ፣ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ሊንቀሳቀሱ፣ በትምህርቱ ሂደት ያሳዩትን ለውጥ በራሳቸው ሊገመግሙና እንደ አንድ የቋንቋ ተማሪ በታላሚው ቋንቋ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ዘወትር ሊገለገሉ ይገባል፡፡ ለእነዚህም ሁኔታዎች መሳካት የመጀመሪያው ተግባር በትምህርቱ ሂደት ተስማሚ የመማር ብልሃቶችን በተገቢው ቦታ ፣ ጊዜና ሁኔታ የመጠቀም ልምድን ማዳበር ነው፡፡

Wallace (1982 ፣ 9) እንደገለጹት ሁለተኛን ቋንቋ መማር የቋንቋውን ቃላት የመማር ጉዳይ ነው፡፡ ሌሎች ጉዳዮችን ትተን በታላሚው ቋንቋ ራስን መግለጫ ቃላት ማጣት በንግግር ሂደት የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላላ አይደለም፡፡ እንደ Mecarthy (1990) አባባል ደግሞ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር በጥሩ ሁኔታ የመማሩ ጉዳይ ምንም ማለት አየደለም ፤ የንግግር ድምጾችን በሚገባ በመናገሩ የሚፈይደው ነገር የለም ፤ ትርጉም ያለው ተግባቦት ለማከናወን ትልቁ ቁም ነገር የቃላት ዕውቀት መኖር ነው፡፡

ተማሪው የቃላት ዕውቀቱን ማሳደግ የሚችለው የትምህርት ሂደት ዋና ተዋናይ ሆኖ በንቃት ሲሳተፍ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያዩ ቃላትን ፍቺ ከማስተማር ይልቅ ተማሪው በራሱ ጥረት የታላሚውን ቋንቋ ቃላት የሚማርበትን መንገድ (ቃላትን የመማር ብልሃቶች) ዕውቀት እና ልምድ እንደሚያጎለብት ማድረግ ይበልጥ ጠቀሜታ እንዳለው ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡ Oxford እና Scarcella (1994፣236) እንደገለጹት የተማሪው ቃላትን የመማር ብልሃቶች ዕውቀትና ልምድ እየዳበረ በሄደ ጊዜ ከመምህሩ ቁጥጥር ተላቅቆ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሱ ጥረት ቃላትን እንዲማር ያግዙታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውጤት መሠረት ተማሪዎቹ ለቃላት

ትምህርት ውጤታማነት በተለያየ መንገድ ዕገዛ የሚያደርጉ ቃላትን የመማር ብልሃቶች በብቃት እንደማይገለገሉባቸው ፣ ስለመማር ብልሃቶቹም ያላቸው ዕውቀትና ልምድ የዳበረ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህን ክፍተት ለመሙላትም የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

ሀ. ተማሪዎች ቃላትን የመማር ብልሃቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በብቃት እንዲገለገሉ መምህራን ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ መሆን አለባቸው፡፡ ስለዚህ በመምህራን ስልጠና ኮርሶች በተማሪው የመማር ብልሃት ላይ ያተኮረ ግብዓት ያስፈልጋል፡፡ መምህራን ስለመማር ብልሃቶች ለተማሪዎቻቸው በቂ መረጃ ከሰጧቸው ተማሪዎቹ ከተለያዩ ብልሃቶች ጋር እንዲተዋወቁና ይበልጥ የሚስማማቸውን ለይተው እንዲገለገሉ ከማገዙም በላይ በራሳቸው ጥረት በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ ቃላትን እንዲማሩ ያነሳሳቸዋል፡፡ Wallace (1982 ፣ 33) እንደገለጹት ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ በትክክለኛው መንገድ ከተማሩ የራሳቸው ምርጥ አስተማሪዎች ናቸው፡፡

ለ. መምህራን ፣ የተማሪዎቻቸውን ቃላትን የመማር ብልሃቶች ዕውቀትና ልምድ ከፍ ማድረግ ፣ የቃላት ዕውቀታቸውን ለማሻሻል በሚል ዓላማ መጽሔት ፣ ጋዜጣ እንዲያነቡ ፣ ሬዲዮ እንዲያዳምጡ ማበረታት

ሐ. ተማሪዎች የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበር ለትምህርታቸው ኃላፊነትን ወስደው በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በራሳቸው ጥረት ቃላትን የሚማሩበት ሁኔታ ቢመቻች ፣ በዚህም ሂደት በርካታ የመማር ብልሃቶችን የመጠቀም ፣ የራሳቸውን ልዩ ልዩ ብልሃቶች ወደ መፍጠር ደረጃም ያመራቸዋለል፡፡

መ. በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚካተቱ የቃላት ተግባራት ተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ቃላትን የመማር ብልሃቶች እንዲገለገሉ የሚያግዙ ሆነው በዘጋጁ ፣ የተማሪዎቹን የመማር ብልሃት ዕውቀትና ልምድ ለማዳበር የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል ፡፡

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ ተማሪዎቹ ቃላትን የመማር ብልሃቶች ለመለማመድ ፣ ዕውቀትና ልምድ ለማዳበር ፣ በቃላት ትምህርታቸውም ውጤታማ ለመሆን የጎላ ድረሻ ይኖረዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

# ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| Acting out physically | አካላዊ ምላሽ መስጠት |
| Affective strategies | ስሜት ነኪ ቁጥጥር ብልሃቶች |
| Cognitive strategies | አዕምሮታዊ ብልሃቶች |
| Compensation strategies | አካካሽ ብልሃቶች |
| Gussing | መገመት |
| Highlighting | ትኩረተ ቃል ድምቅታ |
| Inferencing | መፈልፈል |
| Intonation | የድምፅ ጥብቀት |
| Memory strategies | የትውስታ ብልሃቶች |
| Meta cognitive strategies | ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች |
| Pronunciation | ንበት |
| Purposive sampling | ተመጣጣኝ ናሙና ዘዴ |
| Qualitative | ፍትነታዊ |
| Quantitative | አይነታዊ |
| Social strategies | ማህበራዊ ብልሃቶች |
| Target Language | ታላሚ ቋንቋ |

## ዋቢ ጽሑፎች

ንጋቱ አሰፋ (2000) በሲዳምኛ ቋንቋአፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች የአማርኛን ቃላት ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላትን የመማር ብልሃቶች አተገባበር ፍተሻ፡፡ ያልታተመ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አለም እሸቱ (1997) መሠረታዊ የምርምርና የዘገባ አጻጻፍ ፡፡ አዲስ አበባ ፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ያለው እንዳወቀ (1998) የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር ፡፡ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

Atikins, J. et.al. ( 1995 ) skills Development Methdoiogy. Part 1 .Addis Ababa University printing prees.

Carter,R. and McCarthy,M. (eds) 1988. Vocabulary and language teaching. London: Longman

Channell, J. ( 1988 ) psycho linguistic considertation ni the study of L2 vocabulary acquisition in carter, R. and M. Mccarthy (eds) . Vocabulary and language Teaching . London. Longman.

Ethiopian Language Research center(2005 ) the Ethiopian Languages, Addis Ababa University.Unpublished.

Gairns, R. and Redman (1986 ) working with words : A guide to Teaching and learning Vocabulary. Cambridge: cup.

Harmer , Jermy (1995 ) The practice of Engilish Language Teaching . London: Longman.

Huttenen , Irma (1996 ) Learning to learn an overview LANGUAGE TEACHING : An International Abstracting Journal for language Teachers , Educators , And Researchers Cambridge : Cambridge University press. Vol. 29. No: 2-4 pp. 86-98

Lawson, M. and Hogben, D. (1996 ) The Vocabulary learning strategies of foreign Language students Language Learning Vol. 45, No. 1, 101-135.

McCarthy (1994 ) Engilish Vocabulary in use Cambrige: Cambrige University press.

Mc Carthy, M. (1990 ) Vocabulary. Oxford. OUP.

Mezynski , k . (1983 ) . Issues Concerning the Acquisition of knowledge: Effects of Vocabulary Training on Reading Comprehensive: Review of Educational Research , Vol. 53, No.2

Naiman , N , Frohlich , M , Stern , H. H. and Todesso , A. (1995 ) The good Language learner . Toronto , Ontario : Ontario Institiute for studies in Education.

Nation , P. and J. Coady (1998 ) Vocabulary and Reading ; in carter , R . and M. McCarthy (eds ) , Vocabulary and Language Teaching. London: Longman.

Omalley , J . M. and Chamot A.U. ( 1990 ) Learning strategies in second Language Acquisition. New York : CUP.

Oxford , R. (1998 ) Use of Language strategies . A Synthesis of studies with Implication strategy Training . SYSTEM : An International Jornal of Educational Technology and Applied Lingustics. London: Bergman Press, ltd.

Oxford , R. (1990 ) Language learning strategies . What Every Teacher should know . New York : Newburg House publishers.

Oxford , R. and Scarcella , R.C. (1994 ) A second Language vocabulary learning Among Adults State of the Art in vocabulary instruction; System , Vol. 22, No. 2 ( pp. 213-214 ).

Richards Jack L . and Charles Lockhart (1996 ) Reflecting Teaching in second language classroom . Cambridge: Cambridge University press.

Rubin, J. (1987) learner strategies : Theoretical Assumption , Research History and Typlogy in Wenden, A and J. Rubin (eds ) Learner strategies in language learning . UK. Pentice Hall International.

Rudzaka, B. and Channel, J. (1986 ) The Words you Need : More Words you Need. Engilish language Teaching , Vol. 40. No. 1 (pp. 75-76).

Stem ( 1983 ) Fundamental concept of language Teaching. Oxford: Oxford University press.

Thompson, I ( 1987 ) Memory in language ; in wenden, A. and J. Rubin (eds) .Learning strategies in language learning New York : prentice Hall.

Tonjes, M. I. (1991 ) Secondary Reading, Writing, and learning. Boston: Allyn and Bacon.

Tudor Ian ( 1996 ) Learning –Centerdness as Language Education. Cambridge. Cambridge University press.

Wallance, M ( 1982 ) Teaching Vocabulary. London: Heineman Educational Books.

Warton Glenn ( 2000 ) Language learning strategy of Bilingual language learner in sign.LANGUAGE LEARNING : A Journal of Research In language studies . University of Michingan. Blackwell Publishers, Vol, 50 No s.1-3 pp. 203-243.

Wenden, A. ( 1987 ) Conceptual Background and utility. In Wenden, A. and Rubin, J. (eds). Learning strategies in language learning. New York : prentice Hall.

Wenden, A. (1991 ) learner strategies for learner Autonomy. New York : prentice Hall.

Wilkins, D.A. ( 1972 ) linguistics in language Teaching. Edward Arnold , London.

## አባሪ 1

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና የኮምዩኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት**

**ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

ማሳሰቢያ፡-

ውድ ተማሪዎች፣ የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ስትማሩ የምትጠቀሙባቸውን ቃላትን የመማር ብልሃቶች ለማወቅ ነው። ጥናቱን ስኬታማ ለማድረግ የምትሰጡትእውነተኛ መረጃ ወሳኝነት አለው።ስለዚህ ለመጠይቆቹ ትክክለኛና እውነተኛ መልስ በመስጠት ለጥናቱ ስኬታማነት የድርሻችሁን እንድታበረክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ። በመጠይቁ ላይ ስማችሁን መጻፍ አያስፈልግም።

ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ መጠይቁን በመሙላት ስለተባበራችሁኝ አስቀድሜ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ።

ክፍል አንድ፡- የግል ሁኔታ

- ክፍል--------------ዕድሜ-------------------ጾታ------------
- የትምህርት ቤቱ ስም--------------------------------የአፍ መፍቻ ቋንቋ---------------------

ክፍል ሁለት፡- ቃላትን የመማር ብልሃቶች አስመልክቶ የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

መመሪያ

ከዚህ በታች አዳዲስ ቃላትን ለመማር ወይም ለማጥናት የሚረዱ ብልሃቶችን የሚገልጹ ሃሳቦች ቀርበዋል። እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር በጥሞና አንብበህ (ሽ) የተጠቀሰውን ብልሃት አጠቃቀምህን(ሽን) አስመልክቶ ከቀረቡት ሁልጊዜ ፣ አንዳንድ ጊዜ፣ አልፎ አልፎ እና በጭራሽ መልሶች መካከል አንዱን ብቻ መርጠህ(ሽ) ከምርጫዎቹ ፊት ለፊት ወይም ስር በሚገኘው ሳጥን ውስጥ የ"√" ምልክት በማድረግ መልስ(ሽ)። ለእያንዳንዱ ሀሳብ ትክክል ወይም ስህተት መልስ የለውም ። እያንዳንዳችሁ በታማኝነት መርጣችሁ የምትመልሱት መልስ ነው ትክክለኛ መልስ። ስለዚህ ይህ ፈተና ስላልሆነ እውነተኛ አጠቃቀምህን (ሽን) የሚገልጸውን መርጠህ (ሽ) መለስ (ሽ)።

በሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ምርጫዎች የሚወክሉት፡-

4 ማለት ሁልጊዜ እጠቀማለሁ ማለት ነው።

3 ማለት አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ ማለት ነው።

2 ማለት አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ ማለት ነው፡፡

1 ማለት በጭራሽ አልጠቀምም ማለት ነው፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| | | ሁል ጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | አልፎ አልፎ | በጭራሽ |
| 1 | የተማርኳቸውን ቃላት በቀላሉ ለማስታወስ ፣<br>1.1.በቃል ክፍላቸው (ለምሳሌ፣ ስሞችን በአንድ ወገን ፣ቅጽሎችን በሌላ ወገን፣ግሶችን ደግሞ በሌላ ወገን ) እከፍላቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| | 1.2. ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን አንድ ላይ እመድባቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| | 1.3.በፍቺ ተቃራኒነታቸው እለያቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| | 1.4. እንደየርዕሰ ጉዳይ ግንኙነታቸውግንኙነታቸው(ለሚሳሌ የቢሮ እቃዎች ከሚለው ጋር ሊሄዱ የሚችሉትን እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ)በአንድ ላይ እመድባቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| 2 | ከአዲሱ ቃል ጋር በንበት የሚቀራረብ ቃል ከኦሮምኛ ወይም ከሌላ ቋንቋ ፈልጌ በማጣመር በአዕምሮዬ እቀርጻለሁ፡፡(ለምሳሌ ገንፎ)የሚለውን የአማርኛ ቃል በኦሮምኛ “ጎንፎ” አክሊል ጋር በማጣመር አዕምሮዬ ውስጥ እንደ መቅረጽ ማለት ነው፡፡ | | | | |
| 3 | አዳዲሶቹን ቃላት ካየኋቸው ቦታ ( | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በመጽሐፍ ገጽ፣ በጥቁር ሰሌዳ፣ በመንገድ ማስታወቂያ ወዘተ. . .) ጋር አያይዤ ለማስታወስ እሞክራለሁ። | | | | |
| 4 | ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ለማስታወስ 4.1.በንግግር ውስጥ በመጠቀም እለማመዳለሁ | | | | |
| | 4.2. ትርጉም የሚሰጡ ዓረፍተ ነገሮች እየመሰረትኩ እለማመዳለሁ። | | | | |
| 5 | አዳዲስ ቃላትን ከስዕሎች ወይም ከተጨባጭ ነገሮች ጋር አያይዤ ለማስታወስ እሞክራለሁ። | | | | |
| 6 | አዲሱን ቃል በቀላሉ ለማስታወስ በኦሮምኛ ወይም በሌላ ቋንቋ በንበት(በድምጽ) የሚቀራረብ ቃል እፈልግና ሁለቱን ቃላት ከሌላ ነገር ጋር አያይዛቸውና በአዕምሮዬ እቀርጻለሁ | | | | |
| 7 | የተማርኳቸውን ቃላት በተለያዩ ጊዜያት ውስጥ እከልሳቸዋለሁ | | | | |
| 8 | የአዲሱን ቃል ፍቺ በድርጊት አሳያለሁ(እለማመዳለሁ) ለምሳሌ መዝለል የሚለውን ቃል ፍቺ ወደ ላይ እየዘለሉ ማጥናት ማለት ነው። | | | | |
| 9 | አዳዲስ ቃላትን እየደጋገምኩ አጠናለሁ፤የማጠናውም፡- 9.1. ቃላቱን ደጋግሜ በመጻፍና በማለት ነው | | | | |
| | 9.2. በአዕምሮዬ ውስጥ ደጋግሜ በማመላለስ ነው | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 9.3. በቴፕ ቀድቼ ደጋግሜ በማዳመጥነው | | | | |
| 10 | በአጻጻፍ አንድ ሆነው በንበት በሚለያዩ ቃላት ለምሳሌ፣ ጠብቀውና ሳልተው በሚነበቡ) ላይ ልምምድ አደርጋለሁ | | | | |
| 11 | ንግግር ሳዳምጥ ወይም ጽሑፍ ሳነብ ያጋጠሙኝን አዳዲስ ቃላት ፍቺ ለማወቅ<br>11.1. የአማርኛ መዝገበ ቃላት እጠቀማለሁ | | | | |
| | 11.2. መምህሮቼን ወይም ጓደኞቼን ወይም ሌሎች ሰዎችን ጠይቄ እረዳለሁ | | | | |
| 12 | የአማርኛን ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ወዳለሁ ኦሮምኛ ቃል በቀጥታ ተርጉሜ አገናዝባለሁ። (ለምሳሌ አንበሳ የሚለውን ቃል ሌንጫ ብሎ መተርጎም) | | | | |
| 13 | ጠቃሚ ናቸው ብዬ የምገምታቸውን አዳዲስ ቃላትን በማስታወሻ ደብተሬ አደራጅቼ እይዛለሁ | | | | |
| 14 | ጽሑፎችን ሳነብ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ከስራቸው በማስመር፣ ወይም በመክበብ ወይም ምልክት በማድረግ፣ ከዚያም ፍቻቸውን እፈልጋለሁ | | | | |
| 15 | የተማርኳቸውን ቃላት እርስ በርሳቸው በማቀናጀት ወይም በአዲስ መንገድ እንደገና በማቀናበር ዓረፍተ ነገሮችን እየመሰረትኩ እለማመዳለሁ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 16 | የቃላት ዕውቀቴን ለማዳበር በሚል ዓላማ 16.1.መጽሔት፣ ጋዜጣ አነባለሁ | | | | |
| | 16.2. የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እከታተላለሁ | | | | |
| 17 | በንባብ ሂደት ( ለምሳሌ መጽሐፍ፣ መጽሔት፣ጋዜጣ) ሳነብ የሚያጋጥሙኝን አዳዲስ ቃላት ፍች ከመዝገበ ቃላት ከመፈለጌ ወይም ሌላ ሰው ከመጠየቁ በፊት ከአገባባቸው እገምታለሁ | | | | |
| 18 | የፊት ለፊት ንግግር ሳዳምጥ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሙኝ ፍቻቸውን ከተናጋሪው የአካል እንቅስቃሴ (ለምሳሌ የእጅ ማወራጨት፣ የፊት ማኮሳተር. . . ) እገምታለሁ | | | | |
| 19 | የቃላት ዕውቀቴን ለማሳደግ በሚል ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ትኩረት ሰጥቼ ለመማር እና ለመለማመድ አስቀድሜ ወስኜ ዝግጅት አደርጋለሁ | | | | |
| 20 | በራሴ ግምጋሜ ይበልጥ የሚያስፈልጉኝን ቃላት ወይም የቃላት ተግባራት እየለየሁ ትኩረት እሰጣለሁ | | | | |
| 21 | የቃላት ዕውቀቴን ለማዳበር በሚል ዓላማ በቃላት ትምህርት ሂደት የማከናውናቸውን ተግባራት በማቀድ የማጥናትና የልምምድ ፕሮግራም አዘጋጅቼ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ | | | | |
| 22 | የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | የምማርበትን (ከቃላት ትምህርቴ የምጠብቀውን) የራሴን ዓላማና ግብ አዘጋጃለሁ | | | | |
| 23 | የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ ለመረዳት የተከተልኩት መንገድ ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ መሆኑን በማረጋገጥ ስህተቴን በራሴ እለያለሁ | | | | |
| 24 | በቃላት ትምህርት ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ( መሻሻል) ማሳየት አለማሳየቴን ለማረጋገጥ እራሴን በራሴ እገመግማለሁ | | | | |
| 25 | የቃላት እውቀቴን ለማዳበር በሚል አላማ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ቃላትን ለመማርና ለመለማመድ ሁኔታዎችን አመቻቻለሁ | | | | |
| 26 | የቃላት ትምህርት ከመጀመሬ በፊት አወንታዊ በሆነ መንገድ ( ቀልድ በመፍጠር ሊሆን ይችላል) አካልና አዕምሮዬን አዝናናለሁ | | | | |
| 27 | እራሴን አዳዲስ ቃላት ለመማር ፍላጎት ያለኝና ለመማርም የምችል ጎበዝ ተማሪ አድርጌ እቆጥራለሁ | | | | |
| 28 | በቃላት ትምህርት ውጤታማ ስሆን ( ለምሳሌ የቃላት ዕውቀቴ መሻሻሉን ሳውቅ፣ ወይም በቃላት ፈተና ጥሩ ውጤት ሳመጣ) እራሴን በራሴ አደንቃለሁ | | | | |
| 29 | የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ስማር ለአዳዲስ ቃላት የሚሰጣቸው ፍቺዎች ትክክል ላይሆኑ ቢችሉም በትምህርት ሂደት መሳሳት ያለ በመሆኑ ያለ ፍርሃት ሙከራዬን | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | እቀጥላለሁ | | | | |
| 30 | ቃላት ስማር የተሰማኝን ውስጣዊ ስሜት ( ደስተኛ መሆን አለመሆኔን ) ከመምህሮቼ ወይም ከክፍል ጓደኞቼ ጋር እወያያለሁ | | | | |
| 31 | ያልገባኝን ወይም እርግጠኛ ያልሆንኩበትን ቃል ፍቺ መምህሬን ወይም ጓደኞቼን ወይም ሌሎች ሰዎችን ጠይቄ እረዳለሁ | | | | |
| 32 | የቃላት ችሎታዬን ለማዳበር ከጓደኞቼ ጋር በመተባበር ( በጥንድ፣ በቡድን ) እሰራለሁ | | | | |
| 33 | የቃላት ዕውቀቴን ለማሳደግ በአማርኛ ቋንቋ ጥሩ ችሎታ ካላቸው ሰዎች ጋር ጓደኝነት ፈጥሬ እለማመዳለሁ | | | | |
| 34 | ስለ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል እና አኗኗር ስርዓት ለማወቅ የሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን ፕሮግራም እከታተላለሁ ወይም መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ መጽሔቶች አነባለሁ | | | | |

## አባሪ 2

*ቃለ መጠይቅ*

1. በቅርቡ የተማራችሁትን ቃላት አስቡ፤ ቃላቱን ለመማርና ለማስታወስ ይረዳችሁ ዘንድ የተጠቀማችኂቸው ዘዴዎች አሉ?ለምሳሌ በቃል ክፍላቸው፣ በርዕሰ ጉዳይ ግንኙነት ፣ በፍቺ ተመሳሳይነት ወይም ተቃራኒ ማደራጀት፣ ሊሆን ይችላል፤ ካሉ እንዴት አደራጃችሁ? ለምን?
2. ቀደም ብላችሁ የተማራችሁትን ቃላት በቀላሉ ለማስታወስ ክለሳ ታደርጋላችሁ? እንዴትስ ነው የምትከልሱት?
3. የአማርኛ ቃላትን በቀላሉ ለመማርና ለማስታወስ በኦሮምኛ ወይም በሌላ ቋንቋ ውስጥ ከምታውቁት ቃል ጋር አያይዛችሁ ለመማርና ለማስታወስ ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? ለምሳሌ፦ ከቃሉ ጋር በንበት(በአጠራር) የሚቀራረብ ቃል ከኦሮምኛ ወይም ከሌላ ቋንቋ ፈልጋችሁ በማያያዝ ፤ ወይም ቃሉን በቀጥታ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመተርጎም፤ ካሉ የትኞቹ ናቸው?
4. የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ዕውቀታችሁን ለማዳበር ጥረት ታደርጋላችሁ? መልሳችሁ አዎን ከሆነ ምን ዓይነት ተግባራትን አከናወናችሁ?
5. የቃላት ዕውቀታችሁን ለማዳበር በሚል ዓላማ ከመማሪያ ክፍል ውጭ የአማርኛ ጽሑፎችን ( ለምሳሌ፦ ልቦለዶች፣ ግጥሞች፣ መጽሔቶች . . . ታነባላችሁ? የምታነቡት አልፎ አልፎ ነው ወይስ ሁል ጊዜ ነው? በይበልጥ የምታተኩሩት በየትኛው ላይ ነው? ለምን?
6. የቃላት ዕውቀታችሁን ለማሳደግ ይረዳችሁ ዘንድ የአማርኛ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ በቴፕ የተቀረጹ ንግግሮች ታዳምጣላችሁ? የምታዳምጡት በየዕለቱ ነው ወይስ አልፎ አልፎ ነው?
7. ጽሑፎችን ስታነቡ፣ ንግግሮችን ስታዳምጡ ፍቻቸውን የማታውቋቸው አዳዲስ ቃላት ስታገኙ ምን ታደርጋላችሁ? ቃላቱን ይዛችሁ ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ታያላችሁ? ወይስ ከአገባባቸው ለመገመት ትሞክራላችሁ? ወይስ ሌሎች ሰዎችን ለምሳሌ መምህራንን ወይም ጓደኞቻችሁን ትጠይቃላችሁ? ወይስ ትተዋቸዋላችሁ?
8. ጽሑፎችን ስታነቡ ወይም ስታዳምጡ፤ በአጠቃላይ ከማንኛውም ምንጭ የምታገኟቸውን አዳዲስ ቃላት በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግባችሁ ትይዛላችሁ? እንዴትስ ነው የምትመዘግቡት ?
9. የቃላት ዕውቀታችሁን ለማሳደግ አዳዲስ ቃላትን የምታጠኑበት ዕለታዊ ወይም ሳምንታዊ፣ ወይም ሌላ ፕሮግራም አላችሁ ?
10. የቃላት ዕውቀታችሁን ለማዳበር ከላይ ከተዘረዘሩት አጋዥ ቃላትን የማመር ብልሃቶች በተጨማሪ የተጠቀማችሁባቸው ብልሃቶች አሉን ? ካሉ የትኞቹ ናቸው ?
11. የቃላት እውቀታችሁ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መሄድ አለመሄዱንለማረጋገጥ ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? እንዴትስ ነው ለማረጋገጥ የምትሞክሩት ?
12. የቃላት ዕውቀታችሁን ለማሳደግ ይረዳችሁ ዘንድ ስለ ቃላት አጠናን የሚገልጽ መጽሐፍ አንብባችሁ ወይም መምህራችሁን ወይም ጓደኞቻችሁን ምክር ወይም ሀሳብ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ ?
13. የአማርኛ ቋንቋ ቃላትን ስትማሩ ለትምህርታችሁ ዕቅድ፣ ዓላማና ግብ ታዘጋጃላችሁ?እንዴትስ ነው የምታዘጋጁት?
14. በንባብ ሂደት የምታገኟቸውን አዳዲስ ቃላት ትርጉም በሚሰጡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማስገባት ጭውውት፣ ወይም ንግግር፣ ወይም ምልልስ እያደረጋችሁ ትለማመዳላችሁ ? ይህን ማድረጋችሁ ለምንድን ነው ?

# አባሪ 3

**ተተኳሪ ተማሪዎችን ለመለየት የተዘጋጀ ቅጽ**

**የትምህርት ቤቱ ስም------------------------------------ክፍል------------------**

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ጾታ | አፍ መፍቻ ቋንቋ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

# አባሪ 4

**የተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ አስመልክቶ የተገኘ ጥቅል መረጃ**

<table>
<tr><th rowspan="3">የት/ቤቱ ስም</th><th rowspan="3">ክፍል</th><th colspan="15">የአፍ መፍቻ ቋንቋ</th></tr>
<tr><th colspan="3">ኦሮምኛ</th><th colspan="3">አማርኛ</th><th colspan="3">ትግሪኛ</th><th colspan="3">ጉራግኛ</th><th colspan="3">ጠቅላላ ድምር</th></tr>
<tr><th>ወ</th><th>ሴ</th><th>ድ</th><th>ወ</th><th>ሴ</th><th>ድ</th><th>ወ</th><th>ሴ</th><th>ድ</th><th>ወ</th><th>ሴ</th><th>ድ</th><th>ወ</th><th>ሴ</th><th>ድ</th></tr>
<tr><td rowspan="2">አዋሮ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት</td><td>9ኛ ሐ</td><td>20</td><td>44</td><td>64</td><td>3</td><td>2</td><td>5</td><td>2</td><td>1</td><td>3</td><td>4</td><td>4</td><td>8</td><td>29</td><td>51</td><td>80</td></tr>
<tr><td>9ኛሠ</td><td>22</td><td>38</td><td>60</td><td>4</td><td>6</td><td>10</td><td>3</td><td>5</td><td>8</td><td>4</td><td>6</td><td>10</td><td>33</td><td>55</td><td>88</td></tr>
<tr><td>ጠቅላላ ድምር</td><td></td><td>42</td><td>82</td><td>124</td><td>7</td><td>8</td><td>15</td><td>5</td><td>6</td><td>11</td><td>8</td><td>10</td><td>18</td><td>62</td><td>106</td><td>168</td></tr>
</table>